

"አና ጎሜዝ-
የእውነትና የፍትህ ጠበቃ"

ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ

ታታሪዋ ዲፕሎማት
ማዳም አና ጎሜዝ

መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ኢሳት ልዩ እትም

ግዮን ቅጽ **1** ቁጥር 44 የካቲት **2011** ዓ.ም ዋጋ 14.99

# ኢሳት-"አሸባሪው ሚዲያ"
## በኢትዮጵያ ምድር !



"የምርጫ 97 ሰቆቃ
ከውስጤ አልጠፋም"

ጋዜጠኛ አፈወርቅ አግደው

"በጋዜጠኝነት ቅንጦት ውስጥ
አይደለም ያለሁት"

ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና

"ሀገሬ የምገባው በሥጋት
ሳይሆን በኩራት ነው"

ጋዜጠኛ አበበ ገላው

"ኢሳት የኢትዮጵያውያን ስቃይ
በተከሰተበት ሁሉ ቀድሞ
ይደርሳል"

ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን

"ኢሳት በአገሪቱ ያለው የሰብዓዊ
መብት ረገጣ እንዲጋለጥ ከፍተኛ
ሥራ ሠርቷል"

ጋዜጠኛ ወንድማገኝ ጋሹ

ልዩ ዕትም




9

“ሀገሬ የምገባው በሥጋት ሳይሆን በኩራት ነው“

ጋዜጠኛ አበበ ገላው



13

"የምርጫ 97 ሰቆቃ ከውስጤ አልጠፋም"


ጋዜጠኛ አፈወርቅ አግደው



14

“በጋዜጠኝነት ቅንጦት ውስጥ አይደለም ያለሁት”


ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና



18

“ኢሳት የኢትዮጵያውያን ስቃይ በተከሰተበት ሁሉ ቀድሞ ይደርሳል”

ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን



23

“ኢሳት በአገሪቱ ያለው የሰብዓዊ መብት ረገጣ እንዲጋለጥ ከፍተኛ ሥራ ሠርቷል”

ጋዜጠኛ ወንድማገኝ ጋሹ




28

"እና ጎሜዝ- የእውነትና የፍትህ ጠበቃ"

ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ


## ቀጣይ ዕትም
## ቁ.45 ቅዳሜ
## የካቲት 16 ይጠብቁን!




ቁጥር 43 ዕትም


2 ኢሳት ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥሪውን ያቀርባል

4 ኢሳት ሊያጤናቸው የሚገቡ የነገ ፈተናዎች

5 ለኢትዮጵያ ሚዲያ ለውጡ ምን ነው?
መለክ ቢ.

11 <<እዚህ ጋ አንድ ኢሳት ስፔሻል አምጪልኝ!>>
በኃይሉ ገ/እግዚአብሄር

16 ቤት ለእምቦሳ! የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን
ጌታቸው ወርቁ

21 ኢሳት በፍርሃትና ተስፋ መካከል
ሁሴን ከድር

2 ዳግማዊትዋ ሲልቪያ ፓንክረስትታታሪዋ ዲፕሎማት ማዳም እና ጎሜዝ

# ኢሳት ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ጥሪውን ያቀርባል



ሕወሓት መራሹ የኢሕአዴግ መንግስት አገሪቱን ለ27 ዓመታት ተቆጣጥሮ በስልጣን ላይ በቆየባቸው ዓመታት የብሔር ፖለቲካን በማቀንቀን ሕዝቦች ልዩነቶቻቸውን በማጉላት በግጭት አዙሪት ውስጥ እንዲገቡ መንገድ ጠራጊ ሆኖ ቆይቷል። የብሔርና የጎሳ ፖለቲካው ሥር ሰዶ ከኢትዮጵያውያን ይልቅ የተወለዱበትን ብሔር እና ጎሳ አጥንት በመቁጠር ኢትዮጵያዊነትን በማኮሰስ ተጠምደው መቆየታቸው ይታወቃል። ይህ ለዓመታት ሰፍኖ የቆየው ከፋፋይና ዘረኛ አገዛዝ ዜጎችን በድህነት ዘፍቆ ከመጨቆኑ ባሻገር ኢትዮጵያውያን አብረው እንዳይኖሩ፤ ለጋራ ቤታቸው ለኢትዮጵያ በጋራ እንዳይቆሙ፤ ኢትዮጵያም እንደ ሀገር እንዳትቀጥል የሚያደርግ ሥራ ሲፈፀም ቆይቷል።

በዚህ የጨለማ ዘመን ኢትዮጵያውያን ድምፃቸውን የሚያሰማላቸው፤ ምሬታቸውን የሚናገርላቸው መገናኛ ብዙሃን በሚፈለገው ደረጃ ማግኘት አልተቻለም ነበር። በተወሰነ ደረጃ ብቅ ብቅ ብለው የሕዝቡን የመከራ ድምፅ ለማሰማት የሚጥሩት የኅትመት ውጤቶችን የተለያየ የሐሰት ክስ በመፈብረክ ጋዜጦቹን መዝጋትና ጋዜጠኞቹንም ለእስራትና ለስደት ሲዳርጋቸው ከርሟል።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያለው የኢትዮጵያ ነፃ ሚዲያ ከሕወሓት ኢሕአዴግ የሚወረወርበት ጦር በርትቶበት በተለይ ከ1997 ምርጫ ጋር በተያያዘ በተከሰተው የመንግስት አፈና ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ሊገባ ችሏል። በርግጥ ከዛ በኋላ ቢሆን አልፎ አልፎ ብልጭ ድርግም የሚለው ነፃው ፕሬስ በመጨረሻ ወደ መቃብር ወርዷል፡
፡

በዚህ የተስፋ መቁረጥና የጽልመት ጊዜ ነበር ለኢትዮጵያውያን ዓይንና ጆሮ የሆነው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን አገር ወዳድ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ተመስርቶ ከአገራቸው በግፍ በተሰደዱ ጋዜጠኞች ታጅቦ ከሰሜን አሜሪካ እና ከአውሮፓ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰው። የዛሬ ስምንት ዓመት ኢሳት ተመሰረተ።

የሕዝብ ድምፅ የማሰማት ሚና ይወጡ የነበሩ ጋዜጠኞችን እና ፖለቲከኞችን ጨካኝና ኋላቀር በሆነ መንገድ ሲገድል ሲያስርና ሲያሰድድ ቆይቷል። የዚህ ሂደት ውጤቱ ተያይዞ ማለቅ ነው ያሉ ብርቱዎች ፋና ወጊ በመሆን ከመላው አለም በመሰባሰብ ከስደት አገር ወደ አገር ቤት የሚሰራጭ ሕዝቡንም የሚያነቃና የሚያስተባብር የኢትዮጵያ ሳተላይት ጣቢያን ለመክፈት በቅተዋል።

ኢሣት በሕወሓት ኢሕአዴግ መንግስት ለ28 ጊዜ ያልህ ከአየር እንዲወርድ (ጃም) ቢደረግም ተስፋ ባለመቁረጥ ፈተናዎቹን በመቋቋም ዛሬ ላይ መድረስ ችሏል።

ኢሳት ወያኔ በሕዝቡ ላይ የሚያደርሰውን ሰብዓዊ ሰቆቃ አገራዊ ዝርፊያን ውንብድናን በማጋለጥ አገራዊ እና ወገናዊ አለኝታነቱን ያስመሰከረ የሚዲያ ተቋም ለመሆን ችሏል፡
፡ ኢሣት እንደ ወርቅ ተፈትኖ ችግሮቹን ተቋቁሞ ዛሬ ላይ ቢደርስም ፈተናው አልተጠናቀቀም። ፈተናው ዘርፈ ብዙ ነው፡
፡ የጎሳ ፖለቲካ አቀንቃሾች የዜግነት ፖለቲካ አስተሳሰብ ተፃራሪዎች ኢሣትን ለማዳከም የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። በፋይናስ ረገድ ያለበት ፈተናም ለነገ የሚባል አይደለም፡
፡ ፈተናው ምንም ቢጠጥርም ኢሣት ፈተናውን በለመደው ጥንካሬ ሊሻገር ተዘጋጅቷል ይላሉ ያነጋገርናቸው የኢሳት ጋዜጠኞች እና ባልደረቦች።

የተመሰረተበትን ስምንተኛ ዓመት ለማክበር በሚሊኒየም አዳራሽ ከፍተኛ በሆነ ዝግጅት እየተጠበቀ ነው።

ይህንኑ ዝግጅት አስመልክቶ ኢሳት ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ በዜጎች ድጋፍ የኢትዮጵያውያን ልሳን ሆኖ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ከአፋኙ ሥርዓት ጋር ግብግብ ገጥሞ የሕዝብ ድምፅ እንዲሰማ፤ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር እንዲተባበር፤ የፍትሕ ፀሐይ እንዲመጣ፤ አንባገነኖችና ዘራፊዎች እንዲጋለጡ፤ መጠነ ሰፊ ተግባር መፈፀሙን ጠቅሷል። ዛሬ በአንፃራዊነት የለውጥ አየር በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ መስፈኑን የጠቆመው የኢሳት መግለጫ በስደት አገር የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አንድ ምዕራፍ በማሻገር ከዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ በኢትዮጵያ ሕዝብ መሀል በይፋ መንቀሳቀስ መጀመሩን በይፋ አስታውቋል።

ሕዝባዊ መሰረቱን ለማስፋት እና ራሱን በጠንካራ መሰረት ላይ ለማቆም ከሃገር ውስጥ እድምተኞች ጋር ፊት ለፊት መገናኘት በማስፈለጉ ቅዳሜ የካቲት 9 ቀን 2011 ዓ.ም የኢሳት ጋዜጠኞች እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ሌሎችም ባልደረቦች ከመላው ዓለም ተሰባስበው በአዲስ አበባ ይገኛሉ።

በሚሊኒየም አዳራሽ ከሚከናወነው ከዚህ ዝግጅት አስቀድሞ የካቲት 8 ቀን 2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 12፡00 እስከ 3፡00 ሰዓት የሕዝቡ አንደበት በመሆን ታላቁን ገድል በድል የተወጡት የኢሳት ጋዜጠኞች ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ አቀባበል ይደረግላቸዋል። በአቀባበል ሥነ ስርዓቱ ላይ የመንግሥት ኃላፊዎችን ጨምሮ የሃይማኖት መሪዎች፤ ወዳጅ ዘመዶቻቸው ፤አክቲቪስቶች እና ጋዜጠኞች ፤ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፤ በርካታ ታዋቂ ግለሰቦች አቀባበል ያደርጉላቸዋል።

ከረጅም ዓመት ስደትና የመናገር የመፃፍ ነፃነት ትግል በኋላ ወደ አገራቸው የሚገቡት ጋዜጠኞች ፣ለአገር ውስጥና ለውጪ አገር የመገናኛ ብዙኃን በልዩ ሁኔታ በሚዘጋጅ መድረክ ላይ ከጋዜጠኞች ጋር ቆይታ እንደሚያደርጉ ታውቋል።

ቅዳሜ የካቲት 9 ቀን 2011 ዓ.ም ሚሊኒየም አዳራሽ በሚደረገው ዝግጅት ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ይገኛሉ ተብሎ ይታሰባል። እንዲሁም ታዋቂ እና አንጋፋ የሙዚቃና የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች ለኢሳት አጋርነታቸውን የሚያሳዩበት እና በገቢም እንዲጠናከር ድጋፍ የሚያደርጉበት እንደሆነ ኢሳት በመግለጫው ዘርዝሯል።

የአንድነትና የነጻነት ድምፅ የሆነው ኢሳትን ለመደገፍ እንዲሁም ታላቅ ተጋድሎ እና መስዋዕትነት የከፈሉትን የሕዝብ ልጆች ለማመስገን በዕለቱ በሚሊኒየም አዳራሽ የምስጋና እና የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ላይ ሁሉም ኢትዮጵያውያን እንዲታደሙ ኢሳት በመግለጫው ጥሪውን አቅር□ል።

# ስምንቱ የኢሳት ክብረ በዓል

የኢሳት የመጀመሪያው ክብረበዓል የተከበረው ቅዳሜ እ.ኤ.አ በሰኔ 11 2011 ቦስተን ከተማ ሲሆን በዕለቱ በዓሉን ለማክበር የተገኘው ታዳሚ ቁጥሩ በጣም ብዙ ነበር፡፡በቦስተን አካባቢ የሚኖሩ የቢዝነስ ተቋማት አንደኛውን የኢሳት ክብረ ባእል በማድመቁ ረገድ የተጫወቱት ሚና የሚዘነጋ አይደለም፡፡

በበዓሉ ላይ ከተስተዋሉ ትኩረት የሳቡ ክስተቶች መካከል የሽልማት አሰጣጥ ሥነ ሥርዓቱ ነበር፡፡ በወቅቱ የኢሳት አስተባባሪ ኮሚቴ የመጀመሪያው እና የታሪካዊው በዓል ልዩ ተሸላሚ አድርጎ የመረጣት ታዋቂዋን የኪነ ጥበብ ሰው አለምፀሐይ ወዳጆን ሲሆን ለአርቲስቷ የተበረከተላት ሽልማት በኢሳት አርማ ቅርጽ የተሰራ ሠርተፍኬት ነበር ፡፡ በዕለቱም "አርቲስቷ እኛ ኢትዮጵያዊያን በየቀኑ አብዝተን የምንባትትለትን ዴሞክራሲ እና ነጻነትን እውን ለማድረግ ያለንን አቅም በተሻለ መልኩ ማደራጀት ይኖርብናል፤ለሀገራችን ሕዝብ የነጻ ሚዲያን አንገብጋቢነት ከመቼውም ጊዜ በላይ የምንረዳበት ሰዓት ላይ ደርሰናል፤ በአንድ ኢሳት ሚዲያ ብቻ ሳንገታ ተጨማሪ ሚዲያዎችን ለማቋቋም ሁሉም ትውለደ ኢትዮጵያዊ ድርሻውን እንዲወጣ ጥሪዋን ያቀረበች ሲሆን ታዳሚውም ምላሹን የሰጠው በጋለ ስሜት ተውጦ ነበር፡፡ በዕለቱ ጡዕም ሙዚቃቸውን ያቀረቡት አቀንቃኞች ማሪቱ ለገሰ፣ሰጠኝ አጥናው እና ቤቲ መላኩ ነበሩ፡፡ በባዓሉ ማሳረጊያም የኢሳት ቀጣይ ጉዞን የተቃና ለማድረግ ታዳሚው በአንድ ድምጽ ቃል ኪዳን በመግባት ነበር የተጠናቀቀው፡፡

ኢሳት ከዚህ በኋላ በየአመቱ በተለያየ ከተሞች ለሳባት ዓመታት በዓሉን አክብሯል፡፡

**2ኛው ክብር በዓል ሰኔ 21 2011 በዋሸንግተን ዲሲ**

**3ኛው ሐምሌ 2013 በዋሸንግትን ዲሲ**

**4ኛው ግንቦት 17 2014 ዋሸንግተን ዲሲ**

**5ኛው ጥምቅት 24 2015 ለንደን**

**6ኛው ሕዳር 4 2016 በፊላፊልዲያ**

**7ኛው ጥቅመት 4 2017 ሲዲኒ**



## ስዩም ተሾመ

የኢትዮጵያ መንግስት በቀደመው ጊዜ የተለያየ የፖለቲካ ሀሳብ ያላቸውን የፖለቲካ ሰዎች የመብት ተሟጋቾችን የሃይማኖት መሪዎችን ጋዜጠኞችን ለብዙ እንግልትና ስደት የዳረገ መንግስት ሲሆን ማህበረሰቡ ምንም አይነት የተለያየ የፖለቲካ ሀሳቦችን እንዳይሰማ ፣እንዳያውቅ ያደርግ ነበር፡፡በተለይም የመንግስት የፕሮፓጋንዳ ማሽን የነበሩት ኢቢሲ፣ ፋና እና ዋልታን ጨምሮ የዜጋን ፖለቲካዊ አመለካከት ልሙጥና አንድ ዓይነት ብቻ እንዲሆን ለማድረግ ይሰሩ ነበር፡፡

በእንደዚህ አይነት የጨለማ ወቅት ኢሳት ልክ በጨለማ እንደሚበራ ሻማ ሆኖ ይሰራ የነበረ የቴሌቭዥን ጣቢያ ነው፡፡በሌላ በኩል ደግሞ በመረጃ እጥረት ዜጎች በኢሳት በኩል ምንም አይነት መረጃ እንዳይደርሳቸው ለማድረግ መንግስት ሳተላይት ዲሾችን በሚነቅልበት ወቅት ጣቢያው ከሀገር ውጭ የሚሰራ በመሆኑ የመረጃ እጥረትና ክፍተት ሲያጋጥመው ነበር፡፡ከዚህም የተነሳ አንዳንድ የሐሰት መረጃዎችን ያቀርብም ነበር፡፡ሆኖም ግን እነዚህ ጥቃቅን ችግሮች ኢሳት በጨለማው ዘመን ካበረከታቸው አስተዋፅኦ ጋር ሲተያይ ፈፅሞ ሊነፃፀር የማይችል ነው ብዬ አስባለሁ፡፡



## ዶ/ር አረጋዊ በርሄ

ኢሳት የተባለው የቴሌቭዥን ጣቢያ አልፎ አልፎ የሚያስተላልፋቸው መልዕክቶች ጠባብ አመላካከት ያለው ሆኖ ነው ፤ለምሳሌ በትግራይ ህዝብ ላይ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ አስተላልፈዋል፡፡5 ሚሊዮን የሚሆነው የትግራይ ህዝብ የቀረውን 95 ሚሊዮን የሚሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ አፍኖ ይዞታል፤ ስለዚህ ይህንን ታግለን መጣል አለብን ‹‹ አሳን ለማጥፋት ውሃውን መድፋት ነው›› የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ይህም ህዝብ ለህዝብ የሚያጋጭ፣ የህዝብ ወገንተኛነት የሌለው ርካሽ ብሎም አደገኛ መልዕክት ነው፡፡እኛም ይህንን ፕሮግራም ካየን በኋላ ለዳይሬክተሩ እንዲያርም ነግረነው ነበር፤ እሱም የሰጠን መልስ አዎ ስህተት ነበር ወድያው ቪዲዮውን አውጥነዋል (አጥፍተነዋል) ብሎናል፡፡እኛም ይህ መልዕክት የህዝብ ጆሮ ላይ ስለደረሰ ቪዲዮውን ማውረድ ብቻ ሳይሆን ለህዝቡ በይፋ ይቅርታ መጠየቅ አለበት ብለናቸው ነበር፡፡ይህንን እነሱም አልተቀበሉትም፡፡ስለዚህ በኔ አመለካከት ኢሳት ጠባብ አመለካከት ያለውና ፀረ ትግራይ ህዝብ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡



## አቶ የሺዋስ አሰፋ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን በኢትዮጵያ ላይ የሥርዓት ለውጥ እንዲኖር ወይም አሁን ለመጣው ለውጥ ከፍተኛ የሆነውን አስተዋፅኦ ያበረከተ ጣቢያ ነው፡፡ጋዜጠኞቹም በዚ ትግል ከፍተኛ መስዋዕትነትን የከፈሉ ናቸው፡፡የህዝብ ባለውለታ ናቸው፡፡በርግጥ ህዝብም የገንዘብ ድጋፍና መረጃ በመስጠትም ጉልህ ሚና ተጫውቷል፡፡በአጠቃላይ ስናየው የኢትዮጵያ ህዝብ ውለታ ከፋይ መሆን አለበት፡፡አንዱን እየካደ ወደ ሌላኛው ወገን የሚዘዋወር፣ ለድል አጥቢያ አርበኞች የሚያጨበጭብ መሆን የለበትም፡፡ለዚህ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ሰዎች ሌላ ነገር ባይፈልጉም ክብርና ምስጋና መስጠት ያስፈልጋል፡፡



## አግባው ሰጠኝ

ባለፈው አስርት አመታት ውስጥ የኢሳት ቴሌቭዥን የኢትዮጵያ ህዝብ አይንና ጆሮ ሆኖ ነው ሲሰራ የነበረው፡፡ለዚ ደግሞ እኔ ምስክር ነኝ፡፡እንዲሁም የኢትዮጵ መሬት ለሱዳን መሰጠቱን ያጋለጠው ይኸው ሚዲያ ነበር፡፡ዛሬ የኢትዮጵያ መንግስትም ጉዳዩ ስህተት እንደነበር ብሎ እንዲያምን ማድረጉ ትልቅ አስተዋፅኦ ነው፡፡ከዚ በተጨማሪ የሰብኣዊ መብት ጥሰት ዙሪያ ይደረጉ የነበሩትን እንቅስቃሴዎች በማጋለጥ ከመጣው ለውጥ ጀርባ ያበረከተውም አስተዋፅኦን አደንቃለሁ፡፡

ልዩ ዕትም

ርዕስ አንቀጽ

# ኢሳት ሊያጤናቸው የሚገቡ የነገ ፈተናዎች

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚታወቅበት አግድም የሥልጣን ክፍፍልን በማጽናቱ ረገድ  አራተኛ የመንግሥት ቅርንጫፍ ተብሎ የሚወደሰው ሚዲያ ተጠቃሽ እንደሆነ የሥነ መንግሥት ልኂቃን ያስረዳሉ፡፡በአሜሪካ የዴሞክራሲ ዝግመተለውጥ ውስጥ የአባትነት ድርሻ ያለው ቶማስ ጀፈርሰን ሚዲያን በተመለከተ ያለው አቋም ጽኑ ነበር፡፡ ከመንግሥት ወይም ከጋዜጦች አንዱን ምረጥ የሚል አጣብቂኝ ምርጫ ቢቀርብልኝ፤ጋዜጦች የሚናኙበት፤ መንግሥት የሚያከትምበት አውድ ገሀድ ቢሆን እመርጣለሁ ብሏል፡፡ Were it left to me to decide whether we should have a government without newspapers, or newspapers without a government, I should not hesitate a moment to prefer the latter. ሕዝብን የፍትሐዊ አስተዳደር ተጠቃሚ በማድረግ ሒደት ውስጥ የሚዲያ ደርሻ እንደ ቅጥያ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ሥርዓቱን በማይናወጥ መሠረት ላይ የሚያቆመው ካስማ ይኸው ተቋም ነው፡፡

በሕግ አውጪው፣አስፈጻሚው እና ተርጓሚው መካከል ያለው መስተጋብር ሚዛናዊ እና ጤናማ እንዲሆን ሚዲያ የማይተካ ሚና አለው፡፡ይህ ምህዋሩን የጠበቀ የሥልጣን ክፍፍል በአንባገነናዊ አስተዳደር ውስጥ ሲሆን ግን ሌላ መልክ እና ቅርጽን ይይዛል፡፡ከላይ ወደ ታች በአውራ እና ጭፍራ የእዝ ሰንሰለት የተጠረነፈ፣ምንም የማያፈናፍን የግለሰብ አልያም የአንድ ፓለቲካ ፓርቲ የበላይነት የነገሠበት ሥርዓት ይሆናል፡፡በተለይ በእዚህ አፋኝ ሥርዓት ውስጥ ዋነኛ ሰለባ የሚሆነው የመገናኛ ብዙኃኑ ነው፡፡ በሕዝብ ጫንቃ ላይ የተጫነውን የባርነት ቀምበር ለመስበር በሚደረገው ትግል ውስጥ የሚኖራቸው ድርሻቸው ስለሚታወቅ የጨቋኞች በትር የከፋ ይሆናል፡፡

ላለፉት ሁለት ዐሥርተ ዓመታት እንደ ሕዝብ ስንታዘብ የኖርነው መሪር ሐቅ ይህ ነበር፡፡በታሪክ አጋጣሚ ሥልጣን ከእጁ የገባው ሕዳጣኑ ሕወሓት የዘረጋውን የአሻጥር አገዛዝ እድሜ ለማራዝም፤ የሕዝብ ድምጽ ይሆናሉ ብሎ የገመታቸውን ሚዲያዎችን ለማሽመድመድ አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ ብሎ አያውቅም፡፡ አብዛኞዎቹ ሀገር ቤት ያሉ እውነተኛ የሕዝብ አጋር የሆኑ ጋዜጠኞች ሰብኣዊ ፍጡር ሊሸከመው የማይችለውን መከራን ለመቀበል ተገድደው ነበር፡፡ሌሎች ከፊሎቹ በለስ ቀንቷቸው ባሕር ማዶ ተሻግረው ተባራሪ ስድተኛ ለመሆን ተዳርገዋል፡፡ ይህንን የመከራ ዘመን እጅግ ያከፋው ደግሞ በሕዝብ ቁስል ላይ እንጨት የሚሰዱ የሕወሓት ምስለኔዎች በሚዲያ ስም ሰርክ ደፋ ቀና ማለታቸው ነበር፡፡

በዚህ የመከራ ዘመን የተሰፋ ጠል ሆኖ የሰፊውን ሕዝብ ልብ ሲያወረዛ የኖረው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) እንደነበር ከማንም የተሰወረ ሐቅ አይደለም፡፡ሕዝባችን ሲባትትበት በነበረው ድቅድቅ የጨለማ ዘመን እንደ ሻማ ጭል ጭል እያለ የነጻነቱን ፈለግ በማመላከቱ ረገድ ድርሻው የላቀ ነው፡፡አዲሱ የለውጥ አስተዳደር ኀላዌ ኡደቱን በጠበቀ፣ጤናማ በሆነ መንገድ ከውስጥ ስብሮ እንዲወጣ ትልቅ የኃይል ቋት ሆኖ አገልግሏል ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ተቋሙ “የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐይን እና ጆሮ” የሚለውን መሪ መፈክሩን በገቢር ሲገልጽ እንደኖረ ራሱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምስክር ሊሆን ይችላል፡፡

ሕወሓት ወደፊት የሚፈጥራትን ተምኔታዊ ሀገር ታሳቢ አድርጎ ከአማራ ክልል በወሰዳቸው የወልቃይት እና የራያ ሕዝብ ግዛት ላይ የሚያደርሰውን የሰብኣዊ መብት ረገጣ ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ይፋ በማድረግ ከየትኛውም ሚዲያም ሆነ የፓለቲካ ድርጅት የላቀ ድርሻውን ሲወጣ ኖሯል፡፡በሌሎች የሀገራችን ክልሎችም ቢሆን የዘውጌ ፌዴራሊዝሙ በሚወልደው ግጭቶች ምክንያት የሚደርሰውን ግድያ እና መፈናቀል በቅርበት ሲዘግብ የኖረው ይኸው ሚዲያ ነው፡፡ገዢው መንግሥት ሥልጣኑን ለማጠናከር በምስጢር የሚያጠነጥናቸውን ሴራ በማጋለጥ በሀገር እና በሕዝብ ላይ ሊደርስ ከነበረው መከራ መታደግ ችሏል፡፡

ኢሳት ሲገዳደረው የነበረው ሕወሓት በዚህ ሰዐት ከፌዴራል የሥልጣን መንበሩ ተገፍቶ የዳር ተመልካች ለመሆን ተገዷል፡፡ አሁን ያለው ግብግብ የተገኘውን አዲስ የለውጥ ሥርዓትን ለመቀልበስ ግምባር ከሚፈጥሩት ከዘውግ ድርጅቶች ጋር ይሆናል፡፡ በአዲሱ የለውጥ አስተዳደር ዘመን የኢሳት ባላንጣዎች ቆዳቸውን ቀይረው በሌላ ጽንፍ ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል፡፡ ከወደቀው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ጋር በግብር የሚመሳሰሉት እነዚህ ኃይሎች ከተቋሙ ጋር ዐይን እና ናጫ መሆን የጀመሩት በለውጡ ማግሥት ነበር፡ ፡በርግጥ ሃያ ሰባት ዓመት ሙሉ ከተዘራው የጥፋት ፓለቲካ አንጻር የእነዚህ ኃይሎች በምህዳሩ ላይ መፈንጨት የሚደንቅ አይሆንም፡፡ስለዚህ ለዜግነት ፓለቲካ ጠፍ የሚመስለውን ምህዳር ማልማት እና የዘውግ ፓለቲካ ቀስ በቀስ የሚከስምበትን ኹነት ማጠናከር የመጪ ዘመናት ተጠባቂ የቤት ሥራ ነው ፡ ፡ ከል የለበሰው ኢትዮጵያዊ ማንነትን በማጉላት ሀገሪቱን ወደ ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማሸጋገር የሚረዳውን የዜግነት ፓለቲካ ለማፍካት  እንደ ኢሳት ያሉ ተቋማት ድርሻቸው ከፍተኛ እንደሚሆን እሙን ነው፡፡በዚህ ሂደት ውስጥ በአራቱም አቅጣጫ የተሰባሰቡት የዘውግ ኃይሎች የሚያስወነጭፉትን የጥቃት ቀስትን ለማክሸፍ የሚደረገው ትግል ከወትሮው ጠንከር ያለ ስለሚሆን ተቋሙ ከዚህ ቀደም ከነበረው ቁመና የተሻለ ጥንካሬን መላበስ ይኖርበታል፡፡ የኢሳት ፈተና የዘውግ ድርጅቶች የሚሰነዝሩት ጅምላ ክስ ብቻ አይደለም፡፡በፋይናንስም እና በአደረጃጀቱም ረገድ ራሱን የበለጠ በማጠናከር፣መጪ ዘመናትን በአስተማማኝ መደላደል የሚሻገርበትን ውጤታማ ስትራቴጂ መቀየስ ካልቻለ የነገው ፈተና ከባድ ይሆናል፡፡

ከዚህ ቀደም ከላይ በቀጭን ትእዛዝ የሚወርድላቸውን አጀንዳ እየተቀበሉ እንደ ገደል ማሚቶ ሲያስተጋቡ የኖሩ ሚዲያዎች፣ ለውጡ ባመጣው አንጻራዊ ነጻነት የተነሳ የሕዝብን ጆሮ የሚይዙ አይነኬ ርዕሰ ጉዳዮችን በማቅረብ የተሻለ ቅርጽ መያዝ ጀምረዋል፡፡ ስለዚህ ኢሳት ባለፉት ስምንት ዓመታት ከነበረው አሰራር ሁለንተናዊ በሆነ መልክ የሚቀየርበትን አደረጃጀት መለስ ብሎ ማጤን ከተሳነው በፋይናንስም ሆነ በሰው ኃይል ጠንካራ ቁመና ካላቸው ሌሎች የሀገር ውስጥ ሚዲያዎች ጋር የሚገጥመው ፉክክር በዋዛ የሚታይ አይሆንም፡፡


ግዮን መጽሔት

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**

**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

**በየ 15 ቀኑ ለኅትመት**

**የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**

ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ማኔጂንግ ኤዲተር**

ዘኤልያስ ወልደ ሚካኤል

**ዋና አዘጋጅ**

ፍቅር ሠይድ

አድራሻ፡- አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 7

የቤት ቁጥር 314

**አዘጋጆች**

ሮቤል ምትኩ

ብሩክ መኮንን

**አምደኞች**

አበባው አያሌው

ቴዎድሮስ ተ/አረጋይ

ተረፈ ወርቁ

መስፍን ጌታቸው

ሁሴን ከድር

በሀይሉ ገ/እግዚአብሔር

ሠሎሞን ለማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**

ሀብታሙ መኮንን

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**

አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09

የቤት ቁጥር 552/1

አምባቸው ህንፃ 5ተኛ

ፎቅ ቢሮ ቁ. 501

ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029

ስልክ ፡ +251 911 227661

+251 912 165606

+251 118 12 2333

ኢ-ሜይል፡

Gihon2010meg@gmail.com

enqu2013@ gmail.com

Facebook

Gihon-meg Fekadu

**አታሚ**

ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤

አራዳ ክፍለ ከተማ

ወረዳ 10

የቤ.ቁ. 066/ሀ

# ለኢትዮጵያ ሚዲያ ለውጡ ምኑ ነው?

## መላክ ቢ.

### ከኋላ ስንጀምር

የኢትዮጵያ የህትመት እና ብሮድካስት ሚዲያ ከ1983 ዓ.ም በፊት የነበራቸው "የነጻ ሚዲያነት" ታሪክ ለወሬ የሚበቃ ባለመሆኑ እዚህ ላይ ባይነሳ መልካም ነው። በቀዳሚነት በአጼውም ይሁን በደርግ ዘመን የነበረው የቅድመ ህትመት ምርመራ (ሴንሰርሺፕ) ልጓም ሊያንቀሳቅስ የማይችል ብቻ ሳይሆን እግር ከወርች ያሰረ ጭምር በመሆኑ በባለቤትነት የሚመራቸው አካል ከሚሰጣቸው መመሪያ ውጪ እንዲንቀሳቀሱም አይጠበቅባቸውም። በጊዜው ሚዲያው ከፕሮፓጋንዳ መሳሪያነት ባለፈ ለህዝብ የማወቅ መብት ጥብቅና የሚቆም ሆኖ አልተደራጀም። ስርዓቶቹም ይህንን አይፈቅዱምና የዚያ ዘመን የሚዲያ ታሪክ የመገናኛ ብዙሃን ጨለማ ዘመን ነበር ለማለት ያስደፍራል። በመሰረቱ በጊዜው የነበሩትና በጣት የሚቆጠሩ ንብረትነታቸው የመንግሥት የሆኑ ጋዜጦች እንዲሁም አንድ ለእናቱ የሆነ ቴሌቪዥንና ራዲዮ ጣቢያ ነበር። ይህ ቁጥር የሃገሪቱን የሚዲያ ታሪክ በሰፊ አትሮንስ ላይ ዘርግቶ ለመከራከር በራሱ አቃቢ ምክንያት ነው።

ከ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ በኋላ የነበረው ጊዜ የኢትዮጵያ ሚዲያ ኢንደስትሪ ያንሰራራበት ነው ይላሉ ብዙዎች። የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ግን ወትሮም ያልነበረና ያልወደቀ ነገር 'አንሰራራ' አይባልምና ዘመኑን "ሚዲያው እንደ አዲስ ማቆጥቆጥ የጀመረበት ወቅት" በሚለው ሃረግ ቢተካ ይመርጣል።

የኢሕአዴግ መንግሥት በግንቦት 1983 ዓ.ም ወደ ሥልጣን ሲመጣ አስቀድሞ ከተገበራቸውና ሊጠቀሱለት ከሚችሉ በጎ ተግባራቱ አንዱ በሐምሌ ወር የሽግግር ቻርተር በማውጣት ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ቢያንስ በሕግ ደረጃ ማስከበሩ ነው። ይህንን ተከትሎ የቅድመ ምርመራ (ሴንሰርሺፕ) እቀባ ተነስቷል። እዚህ ላይ ብስራት ወልደገብርዔል ሃንዲሶ "censorship in Ethiopia" በሚለው መጽሐፉ ቅድመ ህትመት ምርመራን የሃሳብ ድራሽ ማጥፊያ "Genocide of thought" በማለት ይገልጸዋል።

የሃሳብ ነጻነት ሕግ አተገባበር ምንም እንኳን ቆሽት አድብን ይሁን እንጂ ቢያንስ ሕግ ኖሮ "መብቴ ተጣሰ" ለሚል አካል መከራከሪያ ምክንያት መፈጠሩ በበጎ ጎን ሊወሰድ ይችላል። ይህ አካሄድ የነጻ ፕሬስ መንፈስ ካደባበት መሬት እንዲቀሰቀስና ኢንደስትሪውም ብዛት ያላቸው ተዋናዮችን እንዲያሳትፍ መሰረት ጥሏል። አስተዳደሩ ሕግ ቀርጾም ቢሆን በብሮድካስት ኢንደስትሪው ዘርፍ ጋት አላላውስ ማለቱ እንዳለ ሆኖ ይህንን ቻርተር ተከትሎ ወደ ገበያው ብቅ ያሉ እንደ ጋዜጣና መጽሔት ያሉ የፕሬስ ውጤቶች ለአንባቢው ግን በምርጫ ቀርበውለት ነበር።

የኢትዮጵያ ሕገመንግሥት በ1987 ዓ.ም የሃሳብ ነጻነትን የሚደነግገውን አንቀጽ ይዞ ብቅ ከማለቱ አስቀድሞ በ1985 ዓ.ም የፕሬስ አዋጅ ቁጥር 34/85 ሲደነገግ ለሚዲያ ኢንደስትሪው መጎልበት የተሻለ ዘመን መጣ ተብሎም ነበር። በርግጥም በጊዜው የፕሬስ አብዮት የፈነዳ እስኪመስል ድረስ ጋዜጦችና መጽሔቶች ተበራክተው ነበር።

የነበረውን አንጻራዊ ነጻነት ተነፍጎ ወደ ነበረበት የዘቀጠ ደረጃ እንዲወርድ ተገድዷል። ሚዲያውን ላለፉት 13 ዓመታት በከባድ አፈና ውስጥ ያኖረው መሰረታዊ ምክንያት ምን ይሆን ተብሎ ቢጠየቅ ቀዳሚው ምክንያት እንዲህ እንዲሆን ተፈልጎ በተሰራ የማዋከብ፣ የመክሰስ፣ የማስፈራራት፣ የማጥፋት እና የማሳደድ ተደጋጋሚ ሴራ ሳቢያ መሆኑን ማንም አያጣውም።



በተለይ ገና ሕገመንግሥቱ ሳይረቀቅ አስቀድሞ በዚህ አዋጅ ብቻ በኢትዮጵያ ታሪክ ቀድሞም ያልነበረ ኋላም ያልተደገመ የህትመት ውጤት ቁጥር ተመዝግቧል። ለምሳሌም 1985 ዓ.ም ብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ 28 ጋዜጣና 65 መጽሄቶች በህትመትና ስርጭት ላይ ነበሩ። በ1986 ዓ.ም ደግሞ ይህ ቁጥር ወደ 79 ጋዜጣና 38 መጽሔት ከፍ ብሎ ነበር። በድምሩ በሁለቱ ዓመት ብቻ 117 የህትመት ውጤቶች ገበያው ውስጥ ነበሩ። ያም ሆኖ ስርጭቱ ከአዲስ አበባና ጥቂት ከተሞች ፈቀቅ ያላለ በመሆኑ የብዛቱን ያህል ተደራሽነቱ የሰፋ አልነበረም።

ኢሕአዴግ መንግሥትነቱን አምኖበት የሃሳብ ነጻነትን በሕገመንግሥት ደረጃ ካረጋገጠ በኋላ (ተግዳሮቱን ያሰበበት አይመስልም) በአዋጅ እና ተባራሪ ሕጎች ሲያስተዳድረው የነበረው የኢትዮጵያ ሚዲያ የበለጠ ይጎመራል ተብሎ በሚጠበቅበት ድህረ ሕገመንግሥት ዘመን (ከ 1996 ዓ.ም በኋላ) ሚዲያው ሲያጣጥመው

ታምራት ገብረጊዮርጊስ Power, media and the Ethiopian public በሚለው አጭር ዳሰሳው ኃይል በበዛበት ሥርዓት ሚዲያ የሚኖረውን ባህሪ ሲያስቀምጠው አንድም መሳሪያ መሆን ሌላም የጋራ እሴትን መናድ ውጤት ይሆናል ብሎ ነበር።

Regrettably, in a landscape where power plays significant role and intervention, the media churns out products that is more of partisan political commentaries than providing dispassionate information, news and analysis. Such a culture of instrumentalist and in part militant media has created a public that is loyal to widely varying ideologies, thereby disapproving of a common good in as much as agreed values, norms and principles

▶

"በሚያስቆጭ መልኩ ኃይል ዋናውን ሚና በሚጫወትበትና ጣልቃ ገብነት በሰፈነበት ከባቢ ውስጥ ሚዲያው የሚያመርታቸው ውጤቶች ከስሜት ነጻ የሆነ መረጃ፣ ዜናና ትንተና ከማቀበል ይልቅ ወደ አንድ ወገን ያደሉ የፖለቲካ ነቀሳዎች ላይ ያተኩራል። ይህ ለአንድ አካል / ሃሳብ መሳሪያ የሆነ አጥቂ ሚዲያ በአንድ ሃሳብ የሚሰባሰብ ሳይሆን በተለያዩ አመለካከቶች የሚጓተት ሕዝብ ይፈጥራል። ይህም የጋራ ስምምነት ያረፈባቸውን እሴቶችን ፣ ልማዶችንና መርሆችን ከሥራ ውጪ ያደርጋቸዋል" ።

በዚህ ወቅት ታዲያ መንግሥት ዐይኑን ሳያነሳ የሚከታተላቸውን ጋዜጦችና መጽሔቶች ሰበባ ሰበብ ፈልጎ ከመስመሩ ገለል አድርጓቸዋል። በነዚህ ጋዜጦች ላይ የሚሰሩ ጋዜጠኞችንም 'በጋዜጠኝታቸውና በጻፉት ጉዳይ አልከሰስኳቸውም' እያለ በአሸባሪነት አንቀጽ ጠቅሶና መዝገብ አደራጅቶ ክስ በመመስረት አንድም በየእስር ቤቱ አጉሯቸዋል፣ በሌላም በኩል ከሃገር እንዲሰደዱ አድርጓቸዋል። በዚህ በግልጽ በታወጀ ሚዲያውን "ልክ" የማስገባት እርምጃ የኢትዮጵያ ፕሬስ አከርካሪውን ተመትቶ በመውደቁ አሁን ድረስ በእንፉቅቅ እየተጓዘ እዚህ ደርሷል። 2010 ዓ.ም ።

## የአሁኑ ዘመን

የዶክተር ዐቢይ አስተዳደር የቀድሞውን የኢሕአዴግ አስተዳደር ወደጎን አድርጎ መንበሩን ከተቆጣጠረ በኋላ ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ መገናኛ ብዙኃንን እና ጋዜጠኞችን ከተመሰረተባቸው ክስ እና ቅጣት ነጻ በማድረግ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ማድረግና የሚዲያውን ኢንደስትሪ ከ "እግር ከወርች" ማላቀቅ ነበር። በዚህ መነሳሳት ሳቢያ በሃገር ውስጥ ተዳክሞ የነበረው የፕሬስ ህትመት ሲነቃቃ በአንጻሩ በውጭ ሃገር የነበሩ የብሮድካስት ሚዲያ ተቋማትም ሃገር ቤት ገብተዋል። የተሰደዱ ጋዜጠኞች ወደሃገራቸው ተመልሰው ዳግም በቀድሞ ሥራቸው ላይ ተመልሰዋል። ለዘመነ ኢሕአዴግ አስተዳደር የጎን ውጋት ሆኖ የኖረው እና በአስተዳደሩም ቀንደኛ አሸባሪ ሚዲያ ተብሎ የተፈረጀውን ኢሳትን ጨምሮ ተደራሲውን በዋናነት አንድ ብሄር ላይ አድርጎ እስከሚሰራው ኦኤምኤን እና ድምጸ ወያኔ ድረስ በኢትዮጵያ የሚዲያ ኢንደስትሪ ሜዳ ውስጥ ለመጫወት መድረኩን ተቀላቅለዋል። በሃገር ውስጥም ኢቢኤስ ላይ ቁልፍ ሰርቶ ታግቶ የነበረው የግል ቴሌቪዥንና ራዲዮ ጣቢያ ፍቃድ መለቀቁ ብዙዎች ሞገድ እየገዙ አየር ላይ እንዲውሉ ምክንያት ሆኗል። ከዚህ ባሻገርም ከታገዱት ጋዜጦችና መጽሔቶች ወደ ህትመት መመለስ ጀምሮ በርካታ መጽሔቶች እና ጋዜጦች ለንባብ በቅተዋል። እዚህ ላይ የሚዲያ ኢንደስትሪው ዳግም ማንሰራራቱን ማመን ይቻላል። ባለፉት አስር ወራት በኢትዮጵያ የሚዲያ ዝርዝር ውስጥ ተደማሪ የሆኑ ወደ አምስት የሚጠጉ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች አየር ላይ መዋል የጀመሩ ሲሆን ከአራት በላይ አዳዲስ ጋዜጦችም መታተም ጀምረዋል። መጽሔቶች ቁጥርም አቆልቁሎ ከነበረበት ቀና ብሎ እያሻቀበ ነው። ይህንን ስናይ ለውጡ ለኢትዮጵያ ሚዲያ ምን ፈጠረለት የሚለውን ጥያቄ ለመጠየቅ እንገደዳለን።

## ለውጡ ለሚዲያው መጣለት ወይስ መጣበት ?

ከእገዳ መነሳት እና ቢያንስ በጻፉትና በተናገሩት ለመታሰር ያለው ፍርሃት ቆፈን ከመላቀቁ ጋር ተያይዞ ካየነው በማያጠራጥር ሁኔታ የኢትዮጵያ ሚዲያ ከለውጡ አትራፊ ሆኗል።ዛሬ የጋዜጠኝነት ሥነምግባር ቁልቁል እየተንሸራተተ በየቴሌቪዥኑ የውይይት ሾው ላይ ማፋጠጥ እና ማንጓጠጥ መርህ እየሆነ ቢመጣም በአንጻራዊ መልኩ ያለውን የመናገርና ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት ያለገደብ መሆን እየተገበርንበት በመሆኑ የሥራ ነጻነት ምቹነትን ያመለክት ይሆናል። ጋዜጠኞች 'ምቹ ቀጠና' ብለው ከሚጠሩት የስፖርት እና መዝናኛ ነክ ወሬዎች እየወጡ ጠንከር ባለ ሃገራዊ ጉዳይ ላይ መዘገብ መጀመራቸውም ለዚሁ ማሳያ መሆን ይችላል። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ከለውጡ በኋላ የኢትዮጵያ ሚዲያ በስርጭት፣ በይዘት፣ በሥርዓት፣ በከባቢ ፣ በመረጃ እና በቅቡልነት ምን ያህል ምቹ ሁኔታ ተፈጠረለት የሚለውን ካየን ግን የምንነቅሰው አናጣም።

## "እስር ቀረ ሚዲያው ሰነፈ"

በተገኘው አጋጣሚ ለመጠቀም እና የተሻለ ሙያዊ ነጻነት ተፈጥሮ ሚዲያው በራሱ አጀንዳ ፈጣሪ ተቋምነቱን ለማረጋገጥ ያለመቻሉ ቀዳሚ ድክመት የሚወድቀው በማንም ላይ ሳይሆን በራሱ በሚዲያው ነው። ከዚህ ቀደም በነበረው አስተዳደር ጋዜጠኞች በጻፉት ሲከሰሱ እና ጥቃት ሲደርስባቸው ያንን ሽሽት ራሳቸውን ወደማያነካካ ቀጣና ሸጉጠው ኖረዋል። በዚህ ምናልባትም አደጋን አምልጠዋል። በሌላ በኩል ሚዲያ ተቋማት በሚሰሩት ሥራ ሳቢያ የመንግሥት ድፍርስ ዐይኖች እንዳያተኩሩባቸው ሲሉ በራስ ቅድመ ስርጭት እቀባ (self-censorship) ላይ አትኩረው ክፉ እንዳይወጣቸውና ክፉ እንዳይደርስባቸው ሲሰጉም ኖረዋል። ከዚህ ቀደም የተዘጉ እና የተሰደዱ ሚዲያዎችን ያዩ ባለሃብቶች በሚዲያ ኢንደስትሪ ዘርፍ ላይ ለመሳተፍ ስለማይበረታቱ ዘርፉ ከመቀጨጭ ሌላ ዕድል አልነበረውም።

ከለውጡ ወዲህ የታየው
ሌላው የሚዲያ ኢንደስትሪ
እና አስተዳደር ድክመት
የፖለቲካ ፓርቲ የሚዲያ
ባለቤት ሆኖ የሚቀጥልበት
ሁኔታ መኖሩ ነው። በ11ኛው
የኢሕአዴግ ድርጅታዊ
ጉባዔ ይነሳል ተብሎ ተነግሮ
የነበረው አንድ አጀንዳ
በኢሕአዴግ ፓርቲዎች
የተደራጁት ሶስት የሚዲያ
ተቋማት . . .

አሁን ነጻነት አለ ካልን እና ከላይ የዘረዘርናቸው ችግሮች ተቀርፈዋል ብለን ከሞገትን ሚዲያው ግን ይህንን ተጠቅሞበታል ወይ ብለን ብንጠይቅ መልሱ 'ባለበት እየሄደ ነው' ወደ ሚለው ይንደረደርብናል። አሁንም እስር ሲቀር ስንፍና ነው የተተካው። ሞጋችነት ቀርቶ አፋሽ አጎንባሽነት ነው የሰፈነው። በጣት ከሚቆጠሩ ጥቂት ሚዲያዎች በቀር ከጊዜው እና ከንፋሱ ጋር የሚነፍስ ሚዲያ ነው አየሩን የተቆጣጠረው። ሚዲያው በለውጡ ኃይሎች እየተካሄደ ያለውን ተግባር መደገፉ የሚያስወቅሰው ባይሆንም ጭልጥ ያለ ድጋፍ ውስጥ ገብቶ ታምራት ወልደጊዮርጊስ በጥናቱ እንዳለው መሳሪያ (Instrumentalist) ሥነልቦና ውስጥ መዘፈቁ ግን ስህተት ነው።

ቢቻል ከዳር ተመልክቶ የሚነቅስ እና ስህተቶችን ዕያሳየ የሚመራ ፣ ካልሆነም በጭፍን ድጋፍ ሌሎች ደጋፊዎችን ጠሪ ሳይሆን ከዘርፉ ቢወጣ ነው የሚመረጠው። እየሆነ ያለው ግን ሚዲያው አሁንም ከወገንተኝነት እና ከፍርሃት ያለመላቀቅ አባዜ አለመውጣቱ ነው። የብዙዎቹ ሚዲያዎች መገለጫ የሆነው ለውጡን ያለጥያቄ እና ያለትችት መደገፍ እና ከዚህ ቢጋጩ የሚመጣውን የአንባቢ/ተመልካች ወቀሳ በመፍራት በእጃቸው ያለውን መረጃ ጭምር ለመጠቀም የመፍራት አባዜ ነው። ይህ በሚዲያ ቲየሪ ወዳጅ ውሻ (love dog) አዝማሚያ እንዳይፈጠር ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራሳቸው Guide dog "መሪ ውሻ" ይሁንልን ያሉት። አልሆነም። እንደሚወራውም የኢትዮጵያ ሚዲያ ጠንካራ ሆኖ መንግሥትን የሚተች እና ስህተትን የሚነቅስ (watch dog) ሚናውን መወጣት ላይ ብዙ ይቀረዋል ሳይሆን መንገዱንም አልጀመረውም። ይህ ደግሞ ከቀድሞ ድባብ ያለመውጣት እና መንግሥትን መቃወም ዋጋ ያስከፍላል ወደሚል አጀንዳ የመሳብ ውጤት ነው።

ለዚህም ይመስላል ዓለም አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተከላካይ ተቋም (ሲፒጄ) እና አምነስቲ ኢንተርናሽናል ስለኢትዮጵያ ሚዲያ ባወጡት ዘገባ "በኢትዮጵያ በሚዲያ ላይ ያለው ጭቆና ቀርቷል ፣ ነገር ግን ሚዲያው የምርመራ ጋዜጠኝነት ገና ይቀረዋል" ነው ያሉት።

## በሕግ ያልተገራ ሚዲያ

ከለውጡ ወዲህ የታየው ሌላው የሚዲያ ኢንደስትሪ እና አስተዳደር ድክመት የፖለቲካ ፓርቲ የሚዲያ ባለቤት ሆኖ የሚቀጥልበት ሁኔታ መኖሩ ነው። በ11ኛው የኢሕአዴግ ድርጅታዊ ጉባዔ ይነሳል ተብሎ ተነግሮ የነበረው አንድ አጀንዳ በኢሕአዴግ ፓርቲዎች የተደራጁት ሶስት የሚዲያ ተቋማት ወደህዝብ ሚዲያ እንዲቀላቀሉ ይደረጋል የሚል ቢሆንም እስካሁን ግን በጉዳዩ ላይ የተወሰደ እርምጃ ቀርቶ የሰረቀ ትንፋሽ የለም። ይህ ብቻ ሳይሆን ብሄር ተኮር ሚዲያዎች ማቆጥቆጣቸውም በራሱ ለመጪው የሚዲያ ጤናማ ከባቢ ችግር ሊሆን እንደሚችል ብዙዎች ይስማሙበታል። ለምሳሌም በኢትዮጵያ ቢሮውን

የከፈተው የኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ (ኦኤምኤን) ብሄር ተኮር ሚዲያ ነው፡፡ በተመሳሳይም ድምጸ ወያኔን (DW) እዚህ ካታጎሪ ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ የክልሎች ሚዲያ ወደብሄር አጀንዳ ማዘመማቸው እንዳለ ሆኖ እንዲህ ያሉ የብሄር ሚዲያ ተቋማት መስፋፋት ከጀመሩ ሕዝቡ በተበታተነ አመለካከት ላይ ተጠምዶ አንድ ሃገራዊ እሴት ላይ ለማትኮር የማይችልበት እድል ይፈጠራል ፡፡

## ጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ሚዲያ - ያልተጠጋጋ ርቀት

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እስካሁን ድረስ የመገናኛ ብዙኃንን ለብቻ ጠርተው አላነጋገሩም፡፡ ለውጡ እንዳለ ሆኖ ከለውጡ ጋር መገናኛ ብዙኃን ምን መምሰል እንዳለባቸው ግን በተለያዩ መድረኮች ላይ ተናግረውታል፡፡ ነገር ግን መገናኛ ብዙኃኑን ሰብስበው ባለው ችግር እና በመፍትሄዎቹ ላይ አልተወያዩም፡፡ በብዙ ጉትጎታ አንድ ጊዜ ብቻ ጋዜጣዊ መግለጫ ቢጠሩም በዘርፉ አጠቃላይ ሁኔታ እና በመንግሥት ምልከታ ላይ ግን የተነፈሱት ቃል የለም፡፡ አርቲስት እና መሰል አካላትን ማነጋገራቸው ሲታይ ለምን ሚዲያውን አራቁት የሚለው ጥያቄ ወደ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች እንዲመጣ ምክንያት ሆኗል፡፡በርግጥ በጠቅላይ አቃቢ ሕግ ጽህፈት ቤት በተደራጀው የሕግ ማሻሻያ ምክር ቤት ውስጥ የሚዲያ ሕግ ማሻሻያ የሥራ ቡድን አለ፡፡

ከ1997 ዓ.ም በፊት የነበሩና አሁንም ስራ ላይ ያሉ ለፕሬስ ነጻነት የማይመቹ ሕጎች አሉ፡፡ ከ1997 በፊት ፕሬሱ አንጻራዊ ነጻነት የነበረው አፋኝ ሕጎች ስላልነበሩ ሳይሆን የወቅቱ አስተዳደር ስላልተጠቀመባቸው ነው የሚባልላቸው ሃሳብን ከመግለጽ ሕገመንግስታዊ ነጻነት (አንቀጽ 29) ጋር የሚጋፉ በተለያዩ አዋጆች ውስጥ የተሰገሰጉ 33 ህጎች እንዳሉ ባለሙያዎቹ አይተው አንጥረው እያወጧቸው ነው፡፡ ሚዲያው በሚፈልገው ነባራዊ ሁኔታ ይሻሻሉ ወይ የሚለው ግን አሁንም ያልተመለሰ ጥያቄ ነው ፡፡

ያም ሆኖ ሥራው እየተሰራ ቢሆንም በጠቅላላ አነጋገር ሚዲያው ስለራሱ ጉዳይ የሚሰራ ስራ ላይ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግበት አውድ አልተፈጠረለትም ማለት ይቻላል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩም በተለያዩ መድረኮች "ጠንካራ ሥራ ይጠበቅበታል" የሚሉትን ሚዲያ በግልጽ ሰብስበው ሊያናግሩት አልቻሉም፡፡

በሌላ በኩል የዶክተር ዐቢይ ሚዲያው እንዲለወጥ መፈለግ በዋናነት ሚዲያው እንዲለወጥ ካላስቻለ ትርጉም አይኖረውም፡፡"የዶክተር አብይ ሚዲያው እንዲለወጥ መፈለግ ሚዲያው ራሱን ለመለወጥ ካለው ዝግጁነት ጋር አልተጣጣመም" የሚለው ሃሳብ ሚዛን መድፋት ጀምሯል፡፡ በርግጥም ሚዲያው በራሱ ተነሳሽነት ጠንካራ ሆኖ መውጣት ስለሚገባው ከዚህም ባሻገር የወደፊት መሰረቱን የሚጥልበት ዕድል እንዳያመልጠው ሚዲያው እግሩ ሲፈታ መራመድ መጀመር መቻል አለበት፡፡

ብዙዎች እንደሚስማሙበት ሚዲያ ራሱን ለማስከበር የሚበቃ ኃይል ያለው ተቋም ነው፡፡ በብዙዎች ዘንድ የሚሰጠው ደረጃ የችላ ባይነት ቢሆንም በራሱ በሚፈጥረው ተጽዕኖ ግን የየትኛውም ሃላፊ ባለሥልጣንም ይሁን ተቋም አጀንዳ መሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር አሁን ያለበትን ችግር በግልጽ በማውጣት ራሱን ለማስተካከል እንዲሁም ያለፈ ችግሩን ለአሁኑ መማሪያ በማድረግ በአዲስ መስመር ላይ ለመገኘት የጋራ ውይይት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በተባበረ ኃይል ጠንካራ አቋም በመያዝ የመገናኛ ብዙሃን ማኅበር ወይም ካውንስል በማቋቋም ሙያው በተሻለ ደረጃ ላይ እንዲገኝ ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

## በማኅበራዊ ሚዲያ የሚመራ ሚዲያ

ከለውጡ በኋላ ባለው ጊዜ የኢትዮጵያ ሚዲያ አቅም ይፈተሽ ከተባለ የማኅበራዊ ትስስር ድረገጾች እጅግ አስጊ በሆነ ሁኔታ የኢትዮጵያን ዋና ሚዲያ ዘርፍ (MAINSTREAM MEDIA) እየመሩት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ያለንበት ዘመን የዲጂታል ዘመን ቢሆንም በዚያው መጠን ደግሞ ተዓማኒ እና በሥነምግባርና በሕግ የሚመሩ ዋና ሚዲያዎች የዚያኑ ያህል ተቀባይነታቸው አልቀነሰም፡፡ ያም ሆኖ በሃገራችን ያለው የዋና ሚዲያ አቅም እየተዳከመ በምትኩ ማኅበራዊ ሚዲያ የሚያመጣውን ንፋስ ተቀብሎ የሚያራግብ እና በዚያ አጀንዳ ብቻ ራሱን ያነጸ ሆኖ ተፈጥሯል፡፡ ይህ አደጋ አለው፡፡

በቀዳሚነት ሚዲያው ተዓማኒነቱን ያጣል፡፡ በኅብረተሰቡ ተሰምቶና ተነግሮ የተተፋ ጉዳይ ላይ ስለሚራኮትም በዚያው መጠን የተከታታዩ ቁጥር ይቀንሳል፡፡ ለተደራሲ ድርቅም ሊዳርገው ይችላል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ሚዲያው በግሉ አስተያየት ከጭብጥ፣ አስፈላጊነትን ከመዘዝ መለየት የማይችል ተሳቢ ሚዲያ ይሆናል፡፡ ዋና ሚዲያ አጀንዳ ፈጥሮ ተደራሲን የሚያስከትል ሊሆን ሲገባ በተፈጠረለት አጀንዳ እና በተሰጠው ቦይ ብቻ የሚፈስስ ይሆንና ግርማውን ያጣል፡፡

ሚዲያ በየትኛውም ዓለም የአጀንዳ ፈጣሪነት ሚና እንጂ አጀንዳ ተከታይነት እድል ላይ ሲወድቅ ከወዲሁ ካልተገራ መጨረሻው ያማረ አይሆንም፡፡ የራሱ አጀንዳ የሌለው ሚዲያ ሁሌም ሙያዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት አቅም ያንሰዋል፡፡ ሚዲያው ሁሌም የማኅበራዊ ሚዲያው ለሚነጋገርበት ጉዳይ አጀንዳ መፍጠር የሚችል አቅም አለው፡፡ አሁን ባለው ሂደት ግን የሶሻል ሚዲያ ተጎታች መሆንና የፍረጃ ፍራቻ ተጠቂነት ላይ ያለ ይመስላል፡፡ በተለይ ሕዝብ የሚፈልገው ምንድነው በሚል ስሜት ብቻ ተጎትቶ በርሱ ላይ ያጠነጠነ ሥራ ብቻ መስራትና "እንዳልጠላ እና እንዳልገፈተር" የሚል አቋም ይዞ በዚሁ ላይ መስራት የሚዲያው መለያ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡

## "የድበቃ ፖለቲካ የለም"

ዶክተር ዐቢይ ወደ ሥልጣን እንደመጡ ሰሞን በቀደመው የምክር ቤት ውሏቸው "የድበቃ ፖለቲካ የለም" ብለው ነበር፡፡ በሚዲያው ማኅበረሰብ ዘንድ ይህ የተተረጎመው ከዚህ በኋላ የመንግሥት አሰራሮች በሙሉ ግልጽ እንደሚሆኑና ሚዲያው ከነበረበት የመረጃ እቀባ ችግር ተላቅቆ የሚፈልጋቸውን መረጃዎች የማግኘት እድል እንደሚፈጠርለት ነበር፡፡ ያ ግን አልሆነም፡፡ መንግሥት አሁንም መረጃ እያቀበ ነው፡፡

ከሚዲያው ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ አስተባባሪነት ሚና ይጫወት የነበረው የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ፈርሶ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሲቋቋም ግልጽ የሆነ የሚዲያ መለየት ተግባር ውስጥ ተገብቷል፡፡ ሚዲያው በጠቅላይ ሚኒስትሩ እንቅስቃዎች እና መግለጫዎች ላይ በአካል ተገኝቶ ለመዘገብ የሚያስችለውን ፍቃድ ማግኘት የሚችለው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ፕሬስ ሰክሬተሪያት ከተመዘገበ እና 'የደንበኛ ሊስት' ውስጥ ከገባ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ጽህፈት ቤቱ አስቀድሞ የመዘገበው ስላለ ከዚያ ውጪ እንደማያስተናግድ ተናግሯል፡፡ በዚህም ብዙ የመገናኛ ብዙኃን የሩቅ ተመልካች ሆነው ቅሬታ እያቀረቡ ነው፡፡

የቀድሞው መንግሥት ኮሙኒኬሽን ጽህፈት ቤት ያለአንዳች ልዩነት ሚዲያው የሚያስፈልገውን መረጃ እያቀበለ እና በየሳምንቱ በሚሰጠው መግለጫም የሃገሪቱንም ሆነ ሌሎች ጉዳዮችን በወቅታዊ መረጃ እያዳረሰ መቆየቱ ብቻ ሳይሆን በማናቸውም የሚዲያው ድጋፍ ጥያቄ ላይ ትብብር ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ መፍረሱ የራሱ የሆነ ምክንያት ቢኖረውም (የሥራ መደራረብን ለማስቀረት መሆኑ ተነግሯል) ነገር ገን ሲፈርስ ይህንን ሥራ ተክቶ በአግባቡ እና በልምድ የሚሰራ ተቋም ማደራጀት ይቀድም ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት በፕሬስ ሰክረተሪያት ሚዲያው ድጋፍ እና ጥያቄ ይዞ ቢደውል የሚያስተናግደው አካል የለም፡፡ የፕሬስ መግለጫ አንድ ጊዜ ቢዘጋጅም ያም ለጥያቄዎች ምንም አይነት ምላሽ ሳያሰጥ ቀርቷል፡፡ ይህ ሲታይ ሚዲያውን ያለሰብሳቢ እና ተወካይ የቀረ አካል አስመስሎታል፡፡ ይህ ችግር ካልተስተካከለ አስቸጋሪ ያለመናበብ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችል የብዙዎች ስጋት ነው፡፡

በሌላ በኩል የመንግሥት ተቋማት ለመገናኛ ብዙኃን መረጃ እየሰጡ አይደለም፡፡ ከዚህ ቀደም የነበረው ብልጭ ድርግም የሚል የመረጃ ፍሰት አሁን ከነጭራሹ ጠፍቷል፡፡ ማዕከላዊነት ኖሮት ምልልስ ቢበዛውም ከዚህ ቀደም አንጻራዊ በሆነ መልኩ ሚዲያ ለመገናኛ ብዙኃን ይደርስ ነበር፡፡ አሁን ግን ተጠሪ እና ተጠያቂ አካላት በሚገባ ስላልተለዩ መገናኛ ብዙኃን በተለይ ከለውጡ ጋር ተያይዞ በወጣው ስትራክቸር መሰረት መረጃ እየተሰጣቸው አይደለም የሚልም ወቀሳ እየተደመጠ ነው፡፡ ለምሳሌም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በ100 ቀን የእቅድ አፈጻጸማቸው ላይ መረጃ ከጠየቃቸው ሰባት መስሪያ ቤቶች መረጃ ያገኘው ከአንዱ ብቻ መሆኑን በመግለጽ ቅሬታውን አቅርቦ ነበር፡፡

በአጠቃላይ የፓርቲም ይሁን ማናቸውም ከፍተኛ ስብሰባዎች በዝግ መካሄዳቸው፣ ከሃገራት ጋር የተደረጉ ስምምነቶች በምስጢር መያዛቸው፣ ወደሃገር ውስጥ የገቡ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር የተካሄዱ ድርድሮች ጭብጥ እና ዝርዝር አለመታወቁ ወዘተ የሚዲያ መረጃ እቀባ መገለጫዎች ሆነው ቀርበዋል፡፡

ይህም ሁኔታ የዶክተር ዐቢይ ለውጥ ከግለሰብ ወደ ተቋምነት አልወረደም የሚል ቅሬታ አስነስቷል፡፡ ቀጣዩ ጉዞ ሚዲያው ከለውጡ የሚያተርፍበት እንጂ ለውጡ ሚዲያውን የሚበድለው እንዳይሆን ያለውን ሥጋት መቀነስ ግድ ይሆናል፡፡

# ኢሳት
# “አሸባሪው ሚዲያ”
## በ ኢ ት ዮ ጵ ያ ም ድ ር !







በኢትዮጵያ ውስጥ ላለፉት 27 ዓመታት በአንባገነንነት ስልጣን ላይ የቆየው የሕወሓት/ ኢሕአዴግ መራሹ መንግስት በህዝብ ላይ ያደርስ የነበረውን አስከፊ በደልና ጭቆና በማጋለጥ ረገድ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዘውና አሁን ለተገኘው ለውጥ አይነተኛ ሚና የተጫወተው ኢሳት ለመሆኑ ማንም የሚክደው ሐቅ አይደለም።

በተለይም እጅግ አስከፊ በነበሩት ባለፉት ስምንት ዓመታት ውስጥ፣ ሥርዓቱ በዜጎች ላይ የሚፈፀመውን ዘግናኝ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ የወያኔ ቱባ ባለሥልጣናት ቅጥ ያጣ ዘረፋ፣ በሙስና የተጨመላለቀ አሰራርና በግልፅ የሚስተዋለውን ፅንፍ የያዘ የዘረኛ አገዛዝን በተጨባጭ ማስረጃ በማጋለጥ፣ በፍርሃት ውስጥ የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍርሃት ቆፈኑ እንዲላቀቅ፣ ለመብቱ የሚያደርገውንም ትግል ከዳር እሰከ ዳር እንዲያቀጣጥል በማነሳሳቱ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል - ኢሳት።

የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐይንና ጆሮ የሆነው ኢሳትን በርካታ መዋለ ንዋይን በማፍሰስ፣የተለያዩ ማዳከሚያ መንገዶችን በመጠቀም፣ ሃያ ስምንት ጊዜ ሥርጭቱን የማቋረጥ ሙከራ አድርጓል።በመለስ ዜናዊም ሆነ በኃይለማሪያም ደሳለኝ የሥልጣን ዘመን ኢትዮጵያውያን ኢሳትን በመከታተላቸው ብዙ መከራ ደርሶባቸዋል። ዲሽ ገጣሚዎች ከጣራ ላይና ከቤታቸው እየተያዙ የታሰሩበትን አሳፋሪ አጋጣሚም ደጋግመን ለመታዘብ ችለን ነበር። የሕወሓት/ኢሕአዴግ በአሸባሪነት የተፈረጀው ኢሳት በጠ/ሚ/ር ዐቢይ አህመድ በተቃራኒው ተቋሙን በአደባባይ እውነተኛ የህዝብ ተቆርቋሪና ልሳን እንደነበር መስክረውለታል።

ኢሳት በሀገር ቤት ስቱዲዮውን ከፍቶ ሥራውን ከጀመረ ወራት ተቆጥረዋል።በስደት ሆነው ሀገር ውስጥ በሚገኙ ቤተሰቦቻቸው ላይ ከፍተኛ ጫና ይደርስባቸው የነበሩት የኢሳት ጋዜጠኞች፣ለሀገራቸውና ለወገናቸው ካላቸው ጥልቅ ፍቅር አኳያ ሁሉንም ጫና በመቋቋም አስከፊውን የጨለማ ዘመን አልፈው የዛሬው መልካም ቀን ላይ ለመድረስ በቅተዋል። ግዮን መጽሔት በኢትዮጵያ እውነተኛ ሚዲያ ታሪክ ውስጥ የሕዝብ ድምፅ የሆነው፣ የኢሳት ልዩ ፕሮግራም የምርጥ ጋዜጠኞቹን ከበርካታ ዓመታት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መምጣት አስመልክቶ ሙሉ ይዘቱን በኢሳት ላይ ያደረገ ልዩ ዕትም አዘጋጅተናል። በዚህም መሰረት “ኢሳት አሸባሪው ሚዲያ፤ በኢትዮጵያ ምድር” በሚል ርዕስ ልዩ ጥንቅር ይዘን የቀረብን ሲሆን፤ በዛሬው ዕለት (ቅዳሜ የካቲት 9 ቀን 2011 ዓ.ም) ከአድናቂዎቻቸውና ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚገናኙት የኢሳት ጋዜጠኞች አበበ ገላው፣ ሲሳይ አጌናና መሳይ መኮንን ከአሜሪካ፣ ወንድማገኝ ጋሹን ከለንደን፣ አፈወርቅ አግደውን ከሆላንድ በኢሳትና ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅና የግዮን ባልደረቦች በስልክ እንዲህ ባለ መልኩ አነጋግረዋቸዋል። መልካም ቆይታ።

▶



# “ “ሀገሬ የምገባው በሥጋት ሳይሆን በኩራት ነው”

## ጋዜጠኛ አበበ ገላው

**ግዮን፡- ከሀገር ቤት የወጣኸው መቼና እንዴት እንደሆነ በመግለፅ ውይይታችን ብንጀምር?**

አበበ፡- ከኢትዮጵያ የወጣሁት የዛሬ 20 ዓመት አካባቢ ነው፤ የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ጊዜ መጀመሪያ ለትምህርት ወደ አሜሪካን ሀገር ለመሄድ ፕሮሰስ ላይ ነበርኩኝ፤ በወቅቱ የመንግሥት ድጋፍ የሚያስፈልግበት ጊዜ ነበር። ይሄንን ዕድል ቢያሰናክሉብኝም ሌሎች ዕድሎችን በየቦታው እየፈለግሁ ነበር። ምክንያቱም ሀገር ቤት መኖር በተለይ ለጋዜጠኛ እጅግ አስቸጋሪ ጊዜ ነበርና በጥቂት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ የሮይተር የዜና ወኪል ሥልጠና ለንደን ጠራኝ፤ በዛው ነው ሹልክ ብዬ የወጣሁት።ለንደን ዘጠኝ ዓመት ያህል ኖሬያለሁ፤ ከዛም ወደ አሜሪካ አቅንቼ ኑሮዬን ከመሰረትኩ ዐሥር ዓመት አልፎኛል።

**ግዮን፡- ኢትዮጵያ ውስጥ እያለህ በጋዜጠኝነት ትሰራባቸው የነበሩ ሚዲያዎችን በዚህ አጋጣሚ ለአንባቢያን ብትገልጽልን?**

አበበ፡- ሀገር ቤት በነበርኩበት ወቅት በነጻው ፕሬስ ዘርፍ ከእነ እስክንድር ነጋ ጋር የተወሰነ ጊዜ ሠርቻለሁ። በኋላ በኢትዮጵያን ሄራልድ ላይ ለሁለት ዓመታት ከፍተኛ ሪፓርተርና አርታኢ ሆኜ ሰርቻለሁ። ግን እዛ የነበረው ሁኔታ በጣም አስቀያሚ ነው፤ የመንግሥት ሚዲያ ስትሠራ መብት የለህም፣ በዛ ላይ አትታመንም። እኔ ከማይታመኑት ጋዜጠኞች መሀል ነበርኩ።ተራ በሆነ ፕሬስ ኮንፍረንስ እንኳን ለመሳተፍ የእነርሱ ሰው የግድ መምረጥ አለበት፤ እኛ በቃ የእንጀራ ልጆች ነን። ይሄን መሰል አስከፊ ነገሮች ብዙ ናቸው። በዛ ላይ በደመወዝና በተለያየ መንገድ ይበድሉሃል። እኔ አሁን ያልኩህን የትምህርት ዕድል አግኝቼ ፕሮሰሱን ስጀምር ከመ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ያስፈልገኝ ነበር። በወቅቱ ከፍያለው አዘዘ የሚባል የፕሬስ ኃላፊ (አሁን አሜሪካን ሀገር ነው ያለው) አንድ ሰሞን ም/ከንቲባ ሆኖ የተመረጠ ሰው ነው፤ እሱን ሄጄ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲሰጠኝ ስጠይቀው በመገረም አየኝና እስኪብርቶውን ጣል አድርጎ ‹‹አበበ ገላው እንኳን አይደለም የድጋፍ ደብዳቤ ልንፅፍልህ አንተ እዚህም መሥራት አይገባህም ነበር፤ ስላንተ ብዙ እናውቃለን። አመለካከትህ ሁሉ ፀረ መንግሥት ነው፤ ›› በማለት ነበር ቃል በቃል የገለጸልኝ።

**ግዮን፡- ኢሳትን ከተቀላቀልክ ምን ያህል ጊዜ ሆነህ? ተቋሙን ለመቀላቀል መነሻ የሆነህ ምክንያትስ ምን ነበር?**

አበበ፡- ኢሳት ሲመሰረትና ዋሽንግተን ዲሲ ቢሮ ሲከፈት አካባቢ ነው ወደ እዚያ ያመራሁት። በወቅቱ አሜሪካን ሀገር ስታምፎርድ ዩኒቨርስቲ የነበረኝን ፕሮግራም ጨርሼ ስለነበር የዲሲ ቢሮው እና ስቱዲዮ ያደራጅ ከነበረው ነአምን ዘለቀ ጋር ተገናኘን። በወቅቱ አክቲቪስት ሆኜ በፖለቲካው ዙሪያ ብዙ ነገሮችን እሰራ ነበር፤ አዲስ ቮይስ የሚባል ድረ ገፅ ነበረኝ። ለአስር ዓመት ያህል ያንን ዌብሳይት አንቀሳቅሼዋለሁ።

ኢሳት ቢሮውን ሲከፍት ነአምን እኛ ጋር ብትመጣ ጥሩ ነው የሚል ሀሳብ አቀረበልኝ፤ እኔም በጣም ደስተኛ ሆንኩኝ፤ የሚዲያን ጉልበት ስለማውቅ ለውጥ ያመጣል ብዬ አምን ነበር። እንደዚህ ዓይነት የታፈነን ድምፅ ሊያወጣ የሚችል ሚዲያ ሲቋቋም አስተዋፅኦ ማድረግ አለብኝ ብዬ ነበር ወደ ኢሳት የመጣሁት። የራሴን ዕድሎች ትቼ ነው ኢሳትን የተቀላቀልኩት፤ እኔ በግሌ አገኝ ከነበረው ዕድል ይልቅ ህዝብን ሊጠቅም የሚችል ሥራ ልንሰራ እንችላለን የሚለው ነገር የበለጠ ሚዛን ስለደፋብኝ ነው ወደ ኢሳት የገባሁት።

**ግዮን፡- ኢሳት ውስጥ በምን ኃላፊነቶች ላይ ነው የሰራኸው?**

አበበ፡- ኢሳት ውስጥ በተለያየ ኃላፊነቶች ሠርቻለሁኝ። የእንግሊዝኛ ፕሮግራም አዘጋጅ ነበርኩ፤ ከዛ በተጨማሪ ማኔጅመንት ላይም እሰራ ነበር ፤የኢሳት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ሠርቻለሁ። የማኔጅመንት ስራና ጋዜጠኝነቱን አንድ ላይ ደርቤ ነበር ስሰራ የቆየሁት።

**ግዮን፡- ኢሳት ወደ ሀገር ቤት በመላ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ እንዳይደርስ ለተደጋጋሚ ጊዜ ሥርዓቱ ከፍተኛ ወጪ እያወጣ ጃም ያደርገው ነበር፤ ይሄ ጊዜ ተስፋ አላስቆረጣችሁም?**

አበበ፡- ስርጭቱን ቀጥታ የማወክ ስራ በመስራት ያቋርጡት ነበር፤ ከዛ በተረፈ ካምፓኒዎቹ ላይ ጫና ያደርጉ ነበር። “ይሄ የሽብርተኞች ሚዲያ ነው” እያሉ ስም ያጠፋሉ። ለአንዳንዶቹ ካምፓኒዎች ገንዘብ ይከፍሏቸው ነበር፤ለሳተላይት ካምፓኒዎቹ ማለት ነው። ይሄ አሁን የተገኘው ለውጥ እስኪመጣ ድረስ በኤምባሲዎች አካባቢ የሚሰሩ የእነሱ ዲፕሎማቶች ከአሜሪካን መንግሥት ጭምር ከተለያዩ መንግስታት ጋር በመሆን እኛ ላይ ከፍተኛ ግፊትና ጫና ያደርጉ ነበር፤

በአጠቃላይ ኢሳት በእነዚህ ምክንያቶች ለሃያ ስምንት ጊዜ ጃም ተደርጎ ስርጭታችን ተቋርጧል። ከጃሚንግ ባሻገር በዲፕሎማቲክ ጫናና ለካምፓኒዎቹ ከፍተኛ ክፍያ እየከፈሉ ይሄን ያህል ጊዜ ፕሮግራማችን እንዲቋረጥ አድርገዋል። ለምሳሌ ኢቴልሳት ለእኛ አገልግሎት እንዳይሰጥ አድርገውት ነበር። ከኢቴልሳት ጋር የዛሬ ሶስት ዓመታት አካባቢ ልዩ ኮንትራት ተፈራርመዋል። በዛ መንገድ ተጠቅመው የእኛ ሥርጭት ኢተልሳት ላይ እንዳይሰራጭ አድርገው ሁሉ ነበር።

**ግዮን፡-የአቶ መለስ ዜናዊ ሕልፈተ ሕይወት ሲታሰብ ኢሳትና አበበ ገላው በተለየ ሁኔታ ይነሳሉ፤ ለምን ይመስልሃል?**

አበበ፡- አቶ መለስ ወደ አሜሪካ በመጡ ጊዜ ተቃውሞዬን በዓለም ታላላቅ መሪዎች ፊት አሰምቼ ነበር፤ ይሄንን በኢሳት ነው የዘገብነው። እኔም ካሜራ ይዤ ከግርማ ደገፋ ጋር ነበር አብረን የሄድነው፤ ያኔ ተቃውሞዬን ሳሰማ የቀረፀኝ ግርማ ነው። በጊዜው አቶ መለስ ዜናዊ ከደረሰባቸው ተቃውሞ ጋር ኢሳት የቅርብ ቁርኝት አለው። ሞታቸውንም ያበሰረው ኢሳት ነው። በእዛ ዙሪያ ምርመራ ሥራ አድርገን ትልቅ ስራ በመሥራት ሞታቸውን በቅድሚያ የዘገብነው እኛ ነን። ▶

እነ በረከት ስምዖን በመንግሥት ሚዲያዎች ላይ እየወጡ ዜናው ሀሰት መሆኑን ያስተባብሉ ነበር፤ እኛ ግን በርግጠኛነት “አቶ መለስ ዜናዊ አልፈዋል” ያልነው እነሱ ይሄን ከመናገራቸው ከሶስት ሳምንት በፊት ቀደም ብለን ነው የገለፅነው። በእነዚህ ነገሮች ኢሳትና እኔ ከቀድሞው ጠ/ሚ/ር ጋር የምንቆራኝ ይመስለኛል።

**ግዮን፡- አቶ መለስ ዜናዊ በታደሙበት ስብሰባ ላይ ለመገኘት ያደረግከው ጥረት ነበር? መልዕክቱን ስታስተላልፍ የተጠቀምከው የድምፅ ጉልበት እንዴት በእዛ ደረጃ ሊጋነን ቻለ?**

አበበ፡- ጠ/ሚኒስትሩ ወደ አሜሪካ እንደሚመጡ ያወቅሁት ከአንድ ቀን በፊት ነው፤ ሳደርግ የፈለግሁት ነገር ከባድ ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ማመን ሙሉ በሙሉ መድፈር አለብህ ያለበለዚያ አይሳካም። ነገሩን ለራሴ ይገፄ አቅጄ ራሴን በሥነልቦና ማዘጋጀቱን የመረጥኩት። በማገኘው አጋጣሚ ተጠቅሜ ተፅዕኖ ሊፈጥር የሚችል ነገር ማድረግ አለብኝ ብዬ አቅጄ ነበር።

በወቅቱ እንደተባለው ሜይ ወር 2012 እ.ኤ.አ ላይ እርሳቸው ከጂ8 ጋር በተያያዘ የምግብ ዋስትናን በተመለከተ ነበር የሚናገሩት። በዛ መሀል ነው እኔ አቋርጫቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት እንደሚያስፈልገው፤ የተራበው ከዳቦና ከምግብ በላይ ነፃነት እንደሆነ፤እነ እስክንድር ነጋ እንዲፈቱ፤ አቶ መለስ ዜናዊም አምባገነን እንደሆኑ፣ በሰብዓዊ መብት ጥሰት በሰው ልጆች ላይ ከፍተኛ ወንጀል እንደሚፈፅሙ፤ ለማጋለጥ እግዚአብሔር ዕድሉንም ሀይሉንም ሰጥቶኝ ያንን በማድረጌና ተቃውሞዬን በማሰማቴ እስካሁን ድረስ ደስተኛ ነኝ።

**ግዮን፡- ከዚህ ጋር በተያያዘ ወደ ሀገር ቤት ስትመጣ የሚያሰጋህ ነገር ምንድን ነው?**

አበበ፡- ወደ ሀገር ቤት ስመጣ ከእኔ በላይ ብዙ ሰዎች ሥጋታቸውን ይገልፃሉ ። እኔ ግን በሥጋት አይደለም የምመጣው፣ ሀገሬ የምገባው በሥጋት ሳይሆን በኩራት ነው። እኛ የታገልነው በመጀመሪያ ደረጃ ፈርተን ለመደበቅ አይደለም፤ ሕዝባችን በነፃነት ተንፍሶ እንዲኖር የታገልን ሰዎች ነን። ይሄንን ራሱ ሄዶ ማየት በጣም ወሳኝ ነገር ነው።

ስለዚህ እኔ ከስጋቴ በላይ እድሉን ነው የማየው፤ ህዝቡን ወጥቶ ማየቱና መገናኘቱ ትልቅ እድል ነው። ህዝቡ ደግሞ ያ አፈና ቀርቶለት በየአደባባይ በጥይት መቆላት፤ ወጣቶች እጅግ በሚዘገንን ኢሰብዓዊ በሆነ መንገድ ይገደሉ ይገረፉ ይታሰሩ ነበር። ብዙ የፖለቲካ እስረኞች የአካልና የሥነልቦና ጉዳት ሰለባ ሆነዋል፤ ጥፍራቸው እየተነቀለ ሰቆቃ ደርሶባቸዋል። ይሄ ሁሉ ዛሬ ቀርቶ ያንን ስራ የሚሰሩት ሰዎች ደግሞ ሸሽተውና ተደብቀው አንዳንዶችም ታስረው፤ ከህዝባችን ጋር መገናኘቱ ለእኔ ትልቅ ትርጉም ነው የሚሰጠው።

በመሆኑም ስጋቶች ሁሌ ይኖራሉ፤ አሁን የመጣው ለውጥ ጠላቶች አሉበት፤ በእኛም ላይ ጠላቶች ሊኖሩ ይችላሉ። በምንሰራቸው ነገሮች ያልተደሰቱ፤ ባደረግነው ነገር ቂም የያዙ ሰዎች እንዳሉ እናውቃለን። ይሄ የእነርሱ ችግር ነው። እኛ ግን ሀገራችን ነው፤በሀገራችን ላይ እንደማንኛውም ዜጋ ገብተን የመውጣት መበት አለን። አሁንም እኔ ያንን መብቴን ከሃያ አመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሀገሬ ለመሄድና ህዝቤንም ለማግኘት እድል ሲገጥመኝ ስጋቱ ሳይሆን የሚታይ ትልቅ ታሪካዊ ዕድል መሆኑ ብቻ ነው።

ከዚህ በፊት እንደምታውቁት እኔ ራሴ በአሸባሪነት ተከስሼ የ15 ዓመት እስር ተፈርዶብኝ ነበር። ሩቅ ሆኜ በሰራሁት ስራ ይሄ ሁሉ ያከተመበት ዘመን ስለሆነ ለእኔ ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጥሩ ዕድል ነው። ሥጋቱ በእኔ ላይ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ሁከት የሚፈጥሩ ሀይሎች አሉ። የሰላማዊ ዜጎችን ህይወቱን የሚያመሳቅሉ ሰዎች አሁንም አሉ። በግሌ ግን ስጋትና ፍርሃት ሳይሆን ከህዝብ ጋር የመገናኘቱን ትልቅ ዕድል እግዚአብሔር መልሶ ስለሰጠኝ፣ ሀገሬ የምገባው በደስታና በኩራት ነው።

**ግዮን፡- ኢሳት በኢትዮጵያ ለተፈጠረው ለውጥ ምን ያህል አስተዋፅኦ አድርጓል ትላለህ?**

አበበ፡- ኢሳት በአሁኑ ሰዐት ለተፈጠረው ለውጥ የአንበሳውን ድርሻ ተጫውቷል ብንል ማጋነን አይሆንም። ምክንያቱም ኢሳት የተደረጉ እውነቶችን ፈልፍሎ ከማውጣት ባሻገር የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲነቃ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ሕዝቡ በፍርሃት ተጠፍንጎ የነበረ ህዝብ ነው። በተለያዩ ክልሎች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በስርዓቱ ላይ የሚደረጉ ትግሎችንም ህዝቡ

**አቶ መለስ ዜናዊም አምባገነን እንደሆኑ፣ በሰብዓዊ መብት ጥሰት በሰው ልጆች ላይ ከፍተኛ ወንጀል እንደሚፈፅሙ፤ ለማጋለጥ እግዚአብሔር ዕድሉንም ሀይሉንም ሰጥቶኝ ያንን በማድረጌና ተቃውሞዬን በማሰማቴ እስካሁን ድረስ ደስተኛ ነኝ**

አቅጣጫ እንዲኖረው፣ትግሉን እንዲያፋፍም ከፍርሃት ቆፈን እንዲወጣ የራሱ የሆነ ትልቅ አስተዋፅኦ ነው ያደረገው።

**ግዮን፡- ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ብዙ ጊዜ በንግግራቸው መሀል ኢሳትን ያነሳሳሉ። ይሄ ከምን የመነጨ ይመስልሃል?**

አበበ፡- ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ እስካሁን ከነበሩ የኢሕአዴግ መሪዎች የተለዩ ናቸው ። አንደኛ እርሳቸው የለውጥ ሰው ናቸው፤ ሀገራችን እንድትቀየር የህዝቦች መብት እንዲከበር ግለሰቦችም ነፃነታቸውና መብታቸው እንዲጠበቅ የሰብኣዊ መብት እንዲከበር ከፍተኛ ፍላጎትና ቁርጠኝነት ያላቸው ሰው ናቸው። በዚህ ምክንያት ደግሞ ኢሳት ትልቅ ስራ መስራቱን ከሚገነዘቡት መሀል አንዱ ናቸው ብዬ ነው የማምነው።

ይሄ ደግሞ ትልቅነታቸውን ያሳያል። ኢሳት ለኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት አይደለም። የኢሕአዴግ ቀደምት መሪዎች የነበሩት አቶ መለስንና አቶ ኃ/ማርያምን ጨምሮ ይሉት እንደነበረው የአሸባሪዎች ልሳን አይደለም የሕዝብ ልሳን ነው። ኢሳት በእውነት ላይ የተመሰረተ ትግል ነው ያደረገው። እውነትና ይዞ የታገለ ሚዲያ ነው። ለእዛ እውቅና መስጠቱ ራሱ የእሳቸውን ትልቅነት እንደሚያሳይ ነው እኔ የማምነው።

**ግዮን፡- ኢሳት ይሄን ያህል ጊዜ በትግል ውስጥ የቆየበት ጉልበት ምን ነበር?**

አበበ፡- ለኢሳት ትልቁ ጉልበቱ ህዝባችን ለነፃነቱ ያለው ቀናዒነትና ጉጉት ነው። ምክንያም ኢሳት ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ይሁን ከመቋቋሙ በፊት ህዝባችን በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ ግፍና በደል እየተፈፀመበት የሚኖር ህዝብ ነበር ። በእዚህ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን ግፍ ለመቀየር በቁርጠኝነት ስንሰራ የነበረው ነገር በጣም አስቸጋሪ ነው።

በቀጥታ በሳተላይት ጃም ከመደረጉ ባሻገር በትንሽና በጣም አነስተኛ በሆነ አቅም ነው ኢሳት የተጀመረው። በጥቂት ደጋፊዎችና በትንሽ አቅም የተጀመረ ሚዲያ ነው። ከዚህ የተነሳ አስቸጋሪ የሆኑ ጊዜዎችን ብናሳልፍም ግን ደግሞ ቅድም እንዳልኩት በአጠቃላይ ሕዝባችን ለነፃነቱና እንዲሁም ደግሞ በሀገሩ ላይ መብቱ ተጠብቆ እንዲኖር ያደርግ የነበረው ትግልና የነበረው ጉጉት ለእኛ ትልቅ ብርታት ነው የሰጠን።

**ግዮን፡- በጉጉት ለሚጠብቃችሁ የኢትዮጵያ ህዝብና ደጋፊዎቻቸው ምንድን ነው የምታስተላልፈው መልዕክት?**

አበበ፡- እኔ የማስተላልፈው መልዕክት ባለፉት 27 ዓመታት በርካታ የሆነ በደልና ግፍ ተፈፅሞበት ህዝባችን እዚህ ላይ ደርሷል። ዛሬ ነፃነቱን አውጇል ። ዛሬ የተሻለ ራዕይ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁላችንም ይታየናል። በርግጥ አስቸጋሪ ጊዜያት እንደምናሳልፍ ምንም ጥያቄ የለውም፤ ምክንያም ይሄን ለውጥ ለመቀልበስ የሚታገሉ ኃይሎ እንዳሉም መዘንጋት የለበትም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ደሙን አፍስሶ፣ ልጆቹን ገብሮ ነው ይሄን ለውጥ ያመጣው። ይሄ ብዙ መስዋዕትነት የተከፈለበት ለውጥ ተቀልብሶ አሁንም ወደ ኋላ እንዳንመለስ ሕዝብ መጠበቅ አለበት። ነፃነትን ሰው ስላገኘ አንዱ በአንዱ ላይ እየተነሳ በዘረኝነትም ይሁን ሌላውን በማንኳሰስ ይሁን በተለያየ መንገድ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በየአካባቢው ስላሉ ሁሉም የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት።

ከዚህ በተረፈ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ማለት የምፈልገው፣ እኔ በግሌ ከ20 ዓመት በላይ ሀገሬንና ህዝቤን ስናፍቅ የቆየሁ ነኝና በጣም ታላቅና ታጋሽ ድንቅ የሆነውን ህዝብ፣ የመከራው ጊዜ አልፎ አሁን የነፃነት እስትንፋስ ለመተንፈስ የበቃበት ስለሆነ ህዝቡንም ለማግኘት በጣም ጓጉቻለሁ፤ ስለዚህ ቹር ይግጠመን ነው የምለው።

**ግዮን፡- እናመሰግናለን።**

# «እዚህ ጋ አንድ ኢሳት ስፔሻል አምጪልኝ!»



በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

‹‹እዚህ ጋ አንድ ኖርማል ኢሳት!›› ብሎ ጮኸ አንድ ከጊላዬ የተቀመጠ ተመጋቢ። አዲስ አበባ መቼም፣ የማይሰማ ጉድ የለም። አንድ ሰሞን በየምግብ ቤቱ የምግብ ዝርዝር ውስጥ፣ ‹‹አርሰናል፤ ቼልሲ እና ማንችስተር›› የሚሉ የእንግሊዝ የእግር ኳስ ቡድኖችን ስም አይተን ስንገረም እንዳልነበር ሁሉ ዛሬ ደግሞ፣ ‹‹ኢሳት›› የሚባል የምግብ ዓይነት መጣ። ኢሳት ‹ኖርማል› እና ‹ኢሳት እስፔሻል›።

አይ ጊዜ። (ምግብ በኢሳት መጠራቱን በዐይናችን በብረቱ ባየን ጌዜ፣ ‹‹አይ ጊዜ!›› ብለን ከመደነቅ ውጪ ሌላ ምን ማለት እንችላለን!? …ምንም!) … ይገርማል።

‹‹እህቴ!›› አስተናጋጇን ጠራኂት።

‹‹አቤት!››

‹‹ኢሳት ምን ዓይነት ምግብ ነው?››

‹‹እስፔሻሉ ነው ኖርማሉ?››

‹‹እስፔሻሉ!››

ምግቡን ልታመጣልኝ ፊቷን ወደ ማብሰያ ክፍል አዞረች።

‹‹ኧረ! ኧረ! ኧረ! በሕግ አምላክ፤ ምን ዓይነት ምግብ እንደሆነ ብቻ ነው ማወቅ የፈለግኩት!›› ያቅሜን ጮኽኩ በድንጋጤ።

‹‹በነጭ ሽንኩርት፣ በሎሚ እና በዝንጅብል ያበደ ቲማቲም ለብለብ፤ በዳጣ!›› አለች በጥድፊያ።

‹‹ምን!?›› በመገረም ጠየቅኩ። ዙሪያዬን በዐይኔ ቃኘሁ። አብዛኛው ሰው ኢሳት ላይ ተጥዶ በፍቅር እያነከተው ነው።

‹‹ኖርማሉስ?›› ስል ጠየቅኩ ለመሄድ ጥድፊያ ላይ የነበረችውን አስተናጋጅ።

‹‹ነጭ ሽንኩርት እና ዝንጅብል ያልገባበት ቲማቲም ቁርጥ በአረንጓዴ ዳጣ!›› አለች ትዕዛዝ ለመቀበል ወደ ሌላ ጠረጴዛ ለመሄድ አቆብቁባ።

ጠረጴዛው ላይ ወደተነጠፈው ሜኑ ዐይኔን መለስኩ፡ ፡ አዎ! ስድስተኛው እና ሰባተኛው ተራ ቁጥር ላይ ያለው ምግብ ኢሳት ‹ስፔሻል› እና ኢሳት ‹ኖርማል› ነው። ዋጋቸውም ኪስ የሚጎዳ አይደለም። … መደነቁ በረታብኝና ፈገግ አልኩ።

‹‹ማን ነሽ!?›› አልኩ ድምፄን ዘለግ አድርጌ።

‹‹አቤት!›› አለች አስተናጋጇ ጆሮዋን አቁማ።

‹‹እዚህ ጋ አንድ ኢሳት ስፔሻል አምጪልኝ!›› አልኩ እግረ መንገዱን ሆዴን ለተጣላኝ ነገር፣ መድኃኒት እንደሚሆነኝ በማሰብ። (የጨጓራዬን ነገር ለእግዚሃር መስጠቴ አልቀረም!) …

(ማሳሰቢያ፡- ይኽ ምግብ ቤት፣ የት ሰፈር እንዳለ ለማወቅ የፈለገ የሁለት ኢሳት ‹ስፔሻል› ሒሳብ ኪሱ መኖሩን ያረጋግጥ። ተናግሬያለሁ፤ እኔ ቀን እንደጣለው ጋዜጠኛ ማስታወቂያ በነፃ የምሠራ ሰው አይደለሁም። ከአራት ኪሎ ሽቅብ ወደ ፈረንሳይ ሌጋሲዮን የሚወስደውን ታክሲ መያዝ ስለሚያስፈልግ የትራንስፖርትም ገንዘብ መያዝ ግድ ይላል)

‹ስፔሻል› ኢሳቱን እዚህ ጋር ተወት እናድርገውና ወደ ኋላ ደግሞ እንመለስ። ያኔ፣ ‹‹በአንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች›› ስም፣ የኢሕአዴግ አባላት ከወረዳ የወጣት ማኅበራት እና ከሴቶች ሊግ እየተመለመሉ በቴሌቪዥን ለቃለ መጠይቅ በመቅረብ ኅብረተሰቡን ያዝጉት በነበረበት ወቅት፤ ያኔ፣ ደም ደም የሚሸት፤ የእልቂት ነጋሪት የሚጎሰምበት፣ በሣምንት ሁለት እና ሦስት ዘጋቢ ፊልም ይሠራ በነበረበት ወቅት፤ በተለይ ያኔ፤ ገዢው ፓርቱ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክልል በተካሄደው የፖለቲካ ምርጫ ከተሸነፈ ከ1997 ዓ.ም ወዲህ…

በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በሚቀርቡ ፕሮግራሞች ከመጠን በላይ የተሰላቸ አንድ ሰው፣ «እኔስ ይኼን ቴሌቭዥን ምን እንደማደርገው ነው ግራው ግብት ያለኝ!» ሲል በምሬት ተናገረ አሉ ለጓደኛው።

«ምነው ይህን ያህል?» ጠየቀ ጓደኛው።

«እንዴ! ምን ማለትህ ነው? ማታ ማታ እኮ ደህና ነገር ማየት አልቻልንም። ፀረ ሰላም፤ ፀረ ልማት ምናምን እያሉ፣ አንዴ በጋዜጣዊ መግለጫ፤ አንዴ በአቋም መግለጫ፤ አንዴ በዘጋቢ ፊልም አደከሙኝ እኮ፤ ምን ላድርግ? ቴሌቭዥኑን ብዘጋው ደግሞ ቤቱ ጭር ይልብኛል። ...ውይ! ውይ! በዚሁ ከቀጠለ አንድ ቀን ሳያሳብደኝ አይቀርም...»

«አይ ወንድሜ!›› አለ የጓደኛውን ምሬት ያዳመጠው ሰው ፈገግ እንደማለት ብሎ፤ ‹‹አይ ወንድሜ፤ ለዚሁም እግዚአብሔርን አመስግን!»

«ለምን?» አለ የሚማረረው ሰው ግራ ተጋብቶ።

«የቴሌቭዥንህ ‹ሪሞት› /መቆጣጠሪያ/ በመንግሥት እጅ ቢሆን ኖሮ ምን ይውጥኽ ነበር!?»

(ይኽቺን አጭር ጨዋታ ያመጣነው በ2004 ዓ.ም ካሳተምነው፣ ‹‹ኑሮ እና ፖለቲካ ቁጥር አንድ›› ከተሰኘው መጽሐፋችን ነው።)

እውነት ነው፤ እንደ ዛሬ ከሰላሣ በላይ የቴሌቪዥን ጣቢያ ሳይኖር፤ እንደ ዛሬ ቀኑን ሙሉ ሙዚቃ እየለቀቁ የሚያዝናኑን ጣቢያዎች ባልነበሩበት ዘመን፤ እንደ ዛሬ አሸባሪና አክራሪ ኃይል ተብለው በረሃ የከረሙ ታጋዮችን ቃለ መጠይቅ ለማድረግ የሚሽቀዳደም ጣቢያ ሳይበዛ፤ እንደ ዛሬ ቤተልሔም ታፈሰ የምትባል ጋዜጠኛ ድንገት ተከስታ ግራ ሳታጋባን፤ እንደ ዛሬ ኢሳትን ያለ ከልካይ ማየት ሳንጀምር፤ እንደ ዛሬ ‹ቃና› የተባለ ቴሌቪዥን ሳይመጣ… የቀድሞ ኢቲቪ (ኢቴቪ) አልባሌ ፕሮግራም በግላጭ አግኝቶን መጫወቻ ሲያደርግን፣ የቴሌቭዥናችን ‹ሪሞት› በመንግሥት እጅ ቢሆን ኖሮ የምር ምን ይውጠን ነበር!? …እንጃ። (ይኼን ይኼን ሳስብ ነው አሮጌውን ኢሕአዴግ ገለል በማድረጉ ሂደት ላይ የእግዚሃር ተሳትፎ እንዳለበት የምጠረጥረው)

ወደዛው ዘመን ተመልሰን አንድ ጨዋታ እንምዘዝና ወደ ጉዳያችን እንግባ፤ ሁለት ባልንጀራሞች አንደኛው ቤት ውስጥ ቁጭ ብለው እየተጫወቱ ነበር አሉ። እንግዳው ታዲያ በጨዋታ መሃል በእንግድነት የገባበትን ቤት በዐይኑ ከገረመመ በኋላ እንዲህ ጠየቀ፤ ‹‹ቤትህ ውስጥ ሁሉ ነገር የተሟላ ነው፡ ፡ ነገር ግን ቴሌቪዥን አለመኖሩ ግርም ይለኛል። ምንድን ነው ምክንያቱ?››

የቤቱ ባለቤት በመንገሽገሽ እንዲህ በማለት መለሰ አሉ፤ ‹‹ወይ ጉድ! በገዛ እጄ ካድሬ እቤቴ አስገብቼ ጉድ ልሁንልህ እንዴ!?››

ዛሬ ‹ሪሞቱ› የሚጠቅመው፣ ድምፅ ለመቀነሻና ቴሌቪዥኑን ለማጥፊያ ብቻ አይደለም። ጣቢያ ለመቀየሪያም ጭምር እንጂ። ይህን ጽሑፍ እየጻፍን በነበርንበት አጋጣሚ፣ የሳተላይት ቴሌቪዥናችንን ከፍተን፣ ‹ሪሞት ተጭነን፣ በአገራችን ቋንቋዎች የሚሠሩ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ስንቆጥር ከሰላሣ በላይ ደርሰዋል። (…ተመስገን! ተመስገን! ከአሮጌው ኢቴቪ እስራት ያወጣኸን አምላክ ተመስገን። በነገራችን ላይ ይኼ ቁጥር የሃይማኖት ጣቢያዎችን አያጠቃልልም።)

ልብ በሉ፤ የለውጡ መሞገቻችን የቴሌቪዥን ጣቢያዎቹ ቁጥር መብዛት አይደለም፤ በጭራሽ! አቀራረባቸው የካድሬ መፈንጫ ከነበረው፣ ከያኔው ኢቴቪ የተሻለ በመሆኑ እንጂ። ለጋዜጠኞቹም ቢሆን ከቀድሞው በተሻለ የሥራ ነፃነት የተሰጣቸው በመሆኑ እንጂ። (አንዳንድ የክልል ቴሌቪዥኖች ይህን ነፃነታቸውን እርስ በእርስ ለመካሰስ፤ ለመናከስ፤ ለመወነጃጀል፤ አንዱ ያንዱን ስም ለማጥፋት እየተጠቀሙበት ቢሆንም) ይህ እንዲመጣ ታዲያ ብዙዎች ዋጋ ከፍለዋል፤ እጅግ በጣም ብዙዎች።

ለዛሬ ማንሳት የፈለግነው እሳቱን ኢሳት ነው። ‹ኖርማል› እና ‹ስፔሻል› በሚል የምግብ ሜኑ ላይ ስለገባው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት)።

ኢሳት አየር ላይ መዋል ከጀመረ ዘጠኝ ዓመቱን ይዟል። በዚህ የዘጠኝ ዓመት ጉዞው የመንግሥት የፈረጠመ ጡንቻ እያረፈበት ከሃያ ጊዜ በላይ ሲዘጋ እና ሲከፈት ቆይቶ እነሆ ዛሬ ላይ ደርሷል። በዚህ ጉዞው ውስጥ ተቋሙ እንደ ተቋም ከደረሰበት ፈተና ውጪ፣ ብዙ ሰዎቹ ብዙ በደልን ተቀብለዋል። አዘጋጆቹ ላይ ከሚያርፈው፣ ‹‹ለምን አሰራጫችሁ›› ክስ እኩል ተመልካቹ ሕዝብም ኢሳትን በማየቱ ብቻ እንደ ወንጀለኛ ታይቷል፤ ብዙ መከራም ደርሶበታል፡ ፡

ስለኢሳት ባሰብኩ ቁጥር ትዝ የሚለኝ አንድ የሰፈሬ ዲሽ ሠሪ ነው። ይኽ ዲሽ ሠሪ የኢሳትን ጣቢያ እየገጠመ ነው ተብሎ ሁለት እና ሦስት ጊዜ ከደንበኞቹ ጣሪያ ላይ በፖሊሶች ተወስዷል።

ታዲያ አንድ ቀን ምርር ብሎት እንዲህ እንዳለ ዛሬም ድረስ በመንደራችን ውስጥ ይነገራል። ‹‹እንደ ጦጣ ከጣራ ጣራ ዘልዬ እንጀራ በበላሁ ምን አድርግ ነው የሚሉኝ?››

ዛሬ የካቲት ዘጠኝ ቀን 2011 ዓ.ም የኢሳት የዝግጅት ክፍል ቁልፍ አባላት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው፣ በሚሌኒየም አዳራሽ አድናቂዎቻቸው ጋር ይገናኛሉ።

ኢሳት አማራጭ የመረጃ ምንጭ በሌለን ጊዜ ከእነጉድለቶቹም ቢሆን አብሮን የዘለቀ ጣቢያ በመሆኑ የዛሬ አምዳችንን በክብር ልንሰጠው ግድ ብሎናል።

በነጭ ሽንኩርት፣ በዝንጅብል እና በዳጣ ባበደ የቲማቲም ቁርጥ የተመሰለው ‹ስፔሻሉ› ኢሳት ይበልጥ ወደ ሕዝብ ለመግባት ከዚህም በላይ ሊበረታ፤ በሰው ኃይል ሊጠነክር፤ የአቀራረብ ስልቱንም ሊያስተካክል ይገባዋል… የምትል ምክር እዚች ላይ ጣል ብናደርግ ነውር የለውም።

ከስምንት እና ከዘጠኝ ወር በፊት እንዲህ የሚባል ዋዛ ነበር። ሦስት ዓይነት ኢትዮጵያ ነበረች፤ የኢሷቷ ኢትዮጵያ፤ የኢቴቪዋ ኢትዮጵያ፤ እና ዓለም ላይ ያለችው እኔ የምኖርባት እውኗ ኢትዮጵያ።

የኢሳቷ ኢትዮጵያ፣ ሞት፣ እሥራት እና እንግልት የበረታባት ኢትዮጵያ ናት፤ የኢቴቪዋ ኢትዮጵያ ደግሞ ጥጋብ የሚጫወትባት፣ ለምለም እና ኢኮኖሚዋ ሽቅብ እደጎነ የሚነገርላት ኢትዮጵያ፤ እውኗ ኢትዮጵያ ደግሞ ከኢሳቷም፤ ከኢቴቪዋም የተለየች። አሁንስ? ይህን ለአንባቢያን እንተወው።

‹‹እስኪ ማነሽ አንድ ‹ስፔሻል› ኢሳት! …ሃሎ! ሰማሽኝ!? ጨጓራዬ ስለማይችል፤ ነጭ ሽንኩርቱን፤ ዝንጅብሉንና ዳጣውን ቀነስ አድርጊው እሺ!? አደራ!››



## ኢሳት አዲስ አበባ ላይ እየተጠበቀ ነው

የካቲት 9 በርካታ የኢሳት ወዳጆቹ የኢሳትን ቀን በአዲስ አበባ ለማክበር ወደ ኢትዮጵያ ይሄዳሉ፤ ከወዲሁ መልካም መንገድ እመኝላቸዋለሁ፡፡ኢሳት ቢያስተካክላቸው ብዬ የምጠቅሳቸው አስተያየቶች ቢኖሩኝም አሁንም ጥሩ ኢትዮጵያዊ ተቋም እንደሆነ አምናለሁ። ወደፊት ኢሳት መናገር ብቻ ሳይሆን መስማትንም አክሎ የሚሰጡትን ገንቢ አስተያየቶች ሰምቶ እና ተጠቅሞ ለመላው ኢትዮጵያ አለኝታ የሆነ ተቋም እንደሚሆን አልጠራጠርም፡፡

**አቤ ቶኪቻው**



## ኢሳት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐይና ጆሮ ሆኖ ይቀጥላል!!

ፍትሕ፣ ነጻነት፣ አንድነትና ኢትዮጵያዊነትን በቀዳሚነት አንግቦ ላለፉት ስምንት ዓመታት በሀገራችን ውስጥ በተደረገው እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ ግንባር ቀደም አስተዋጽኦ ያደረገው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ጋዜጠኞችና የቴክኒክ ሙያተኞች በቡድን ለመጀመሪያ ጊዜ ኦፊሴላዊ ጉዞ ወደ አገራችን ኢትዮጵያ እንደሚያደርጉ ብዙዎቻችሁ የሰማችሁ ይመስለኛል።

ገና ከጅምሩ ከ2010 እስከ 2012 የኢሳት ትልቁን የዋሽንገተን ስቱዲዮ ከመመስረትና ከመምራት፣ ከ2012 እስከ 2015 ደግሞ የኢሳት ዋና ዳይሬክተር ሆኜ ከስምንቱ ዓመታት አምስቱን አብሬያቸው በቅርበት በመስራቴ እንዲሁም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያ ርብርብ ያደረጉበት፤ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የኢሳት የድጋፍ ኮሚቴዎች ብዙ ድካምና ውጣ ውረድ ያዩበት ፤ በርካታ ጋዜጠኞች እንዲሁም በመስኮት ጀርባ እንጂ ከፊት ለፊት የማይታዩና ሕዝብ እምብዛም የማያውቃቸው የፋይናንስና የአስተዳደር ሙያተኞች፤ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪዎች፤ የአይቲ ባለሙያዎች፤ የኢሳት የቦርድ አባላትና ሌሎች የኢሳት ማገርና ምሰሶ ሆነው ያገለገሉ ጀግና ኢትዮጵያውያን ሁሉ፤ ቀን ከሌሊት የደከሙባቸው እነዚህ በርካታ ዓመታት ፣ኢሳት የነጻነትና የኢትዮጵያዊነት ቀንዲል የሆነ የሚዲያ ተቋም ሆኖ በመቀጠል እዚህ ደረጃ በመድረሱ የተሰማኝን የበኩሌን ኩራትና ደስታ ለመግለጽ እወዳለሁ።

አንዳንድ ልዩነቶች ቢኖሩም፤አንዳንዴም የማይጥሙን ጉዳዮች በሚዳያ ቢቀርቡም፤ሌሎች ተቋማዊ ችግሮች ሊኖሩ ቢችሉም፤ በፍጹም መረሳት የሌለብን ግን ዘር/ጎጥና ብሔር በተስፋፋበት በዛሬው የሀገራችን የፓለቲካ ድባብ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን መብትና ነጻነት፣ የሁላችንም መለያ ለሆነው ለኢትዮጵያዊነት ፍንክች ሳይል የቆመ አንዱና ዋነኛ ኃይል ኢሳት መሆኑ ፈጽሞ መዘንጋት የለበትም። ይህም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን የምናስቀድም ዜጎች ሁሉ መረባረብ የሚገባን እንጂ ቀበቶ የምናላላበት ወቅት ላይ አይደለንም ።

ኢትጵያዊነት ለዘላለም ይኖራል! ይለመልማል!

**ነአምን ዘለቀ**



## ኢሳት የነጻነት ቀንዲል

ኢሳት የተመሠረተበትን ሕዝባዊ አላማ ከፍ አድርጎ በማንገብ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከአንባገነናዊ አፈና ነጻ ለማውጣት በተደረገው ትግል ቁልፍ ሚና ተጫውቷል። ኢሳት የኢትዮጵያ ሕዝብ የነጻነት ድምጽ በመሆን በርካታ የአፈና መሰናክሎችን በመቋቋም መረጃ ለተነፈገው ሕዝባችን መረጃ በማድረስ፣ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶችን፣ የሥልጣን ብልግናን፣ አድሏዊ አሰራሮችና በሕዝብና አገር ላይ የተፈጸሙ መጠነ ሰፊ ዘረፋዎችን ከማጋለጡም ባሻገር የታፈኑ ድምጾች ጎልተው እንዲሰሙ በግንባር ቀደምትነት የድርሻውን አበርክቷል።

ዛሬ በኢትዮጵያ የፈነጠቀውን የነጻነት ጭላንጭል በመጠቀም ኢሳት በኢትዮጵያ ስቱዲዮ ከፍቶ በስፋት ለመንቀሳቀስ እቅድ ተልሞ በመስራት ላይ ይገኛል። ይህንን እቅድ ለማሳካት ከዋሺግንተን ዲሲ፣ ለንደን እና አምስተርዳም ስቱዲዮዎች የተውጣጣ የአልኡካን ቡድን ወደ ኢትዮጵያ በመጓዝ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሕዝባችን ጋር በመገናኘት የተመሰረተበትን ዘጠነኛ አመት በሚሌኒየም አዳራሽ ያከብራል። በቀጣይነትም በተለያዩ ከተሞች በመዘዋወር ከሕዝቡ ጋር ውይይት ይደረጋል።

**ጴጥሮስ አሸናፊ**



## የጭቁን ኢትዮጵያዊያን ዐይንና ጆሮ

የጭቁን ኢትዮጵያዊያን ዐይንና ጆሮ ፣ የማንነት ትግላችን ቀኝ እጅና አጋር የሆነው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን (ኢሳት) የካቲት 9 በሚሊኒየም አዳራሽ ልዩ ዝግጅት እንደሚኖረው እየተገለጸ ነው። ኢሳትና ጋዜጠኞቹ አገራችን አሁን ላለችበት የተስፋ ጭላንጭል እና መልካም የፖለቲካ ጅምር የበኩላቸውን የተወጡ ምርጥ ኢትዮጵያዊያን ናቸው። ሌሎች እንደ ውሻ ፣ትርፍራፊ አጥንትና ርካሽ ፖለቲካን ተከትለው ዘመኑን ባልዋጀ ፣ የትላንቱን በረሳና የነገውን ባላገናዘበ፣ እንዲሁም ሙያዊ ሥነ ምግባርን ባልተከተለ ሁኔታ ሲፏልሉ እያየን ያፈርነውን ያህል ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብና ኢትዮጵያዊነትን ማእከል አድርጎ የሚሠራ ኢሳትን የመሰለ የሚዲያ ተቋም በዚህ የግራ ዘመን ማግኘት ትልቅና መታደል ነው። በየትኛውም ሰዐት፣ በምንም አይነት ሁኔታ የነጻነት አጋራችን ከሆነው ኢሳት ጎን ቆሜ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ።

**አግዘው ህዳሩ**




## ኢሳት የመላው ኢትዮጵያን ዓይንና ጆሮ ነው

አንዳንድ ጠባብ ብሔርተኞች ኢሳትን ፀረ አማራ ነው እያሉ ሲያልጎመጉሙ ለመታዘብ ችያለሁ፤ በዚያኛው በኩል ደግሞ ኢሳት ፀረ ኦሮሞ የነፍጠኞች ሜዲያ ነው ይላሉ። የትህነግ/ህወሓት የሥጋና የመንፈስ ልጆች ደግሞ ኢሳት ፀረ ትግሬ ሜዲያ ነው ይሉሀል። ሁሉም ግን ኢሳትን እኛ በሰፋነው ልክ ካላወራህልን የሚሉ መናጆዎች ናቸው። ኢሳት የመላው ኢትዮጵያን ዓይንና ጆሮ ነው። አሁን በኢትዮጵያ ያለው ለውጥ እንዲመጣ ከሜዲያ በላይ በርካታ ተግባራትን በመፈፀም የአምበሳውን ድርሻ የሚወስደው ኢሳት ነው።

**ብሩክ አበጋዝ**

# "የምርጫ 97 ሰቆቃ ከውስጤ አልጠፋም"



## ጋዜጠኛ አፈወርቅ አግደው

**ግዮን፡- ከአገር የወጣኸው እንዴት እና መቼ ነበር?**

አፈወርቅ፡- ከኢትዮጵያ የወጣሁት መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ.ም ነው። የእንቁጣጣሽ በዓል ያከበርኩት አውሮፕላን ውስጥ ነበር። አፈወርቅ ኢትዮጵያዊ የአርባ ምንጭ ልጅ ነው፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተምሮ የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ውስጥ አገልግሏል። ለትምህርት ወደ አምስተርዳም መጥቼ ነበር። ለስደት ያበቃኝ እና በዚያው ልቀር የቻልኩበት ምክንያት ከኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ጋር በተያያዘ በሰጠሁት አስተያየት ነው።

የቀድሞው አፈ ጉባኤ ዳዊት ዮሐንስ አምስተርዳም መጥተው የጦርነቱን ትክክለኛነት በሚያስረዱበት ጊዜ ተቃውሜ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስፈልገው ዳቦ መግዣ እንጂ ጥይት አይደለም፤ ዳቦ ያልጠገበ ሕዝብ ወደ ጦርነት መክተት ፍትሃዊ አይደለም ብዬ ሃሳብ በመስጠቴ ለትምህርት የሚላክልኝን ገንዘብ ከለከሉኝ። ት/ቤቱ ግን በነፃ አስተማረኝ።እኔም ከዚህ ክስተት በኋላ በስደት እዛው ለመቅረት ችያለሁ።

ለትምህርት የሚላክልኝን ገንዘብ በወቅቱ የኮሚሽኑ ኃላፊ የነበሩትን ባለሥልጣን ብጠይቅም ገንዘብ ለአንተ መላክ የማይታሰብ ነው፤ በወጪ ያሉትን የመንግስት ተቃዋሚዎችን ማበረታት ነው፤ የሚል ምላሽ ሰጡኝ። እኔም ምርጫ ሳጣ ለመሰደድ ወስኜ እዚህ ለመቅረት ወሰንኩ።በኋላ ሆላንድ ካሉ ኢትዮጵያውያን ጋር ግፈኛውን ስርዓት ለመጋፈጥ እንቅስቃሴ ጀመርን፤ ኢሳት ሲመሰረትም በ2010 መስራች ሆኜ በጋዜጠኝነት መስራት ጀመርኩ።

**ግዮን፡- የኢሳት ቆይታህን በአጭሩ እንዴት ትገልፀዋለህ?**

አፈወርቅ፡- በኢሳት ያለኝ ቆይታ ከፍተኛ የሆነ ደስታ ያሳደረብኝ ነው። ታላቅ የህሊና እርካታ ነው። የምፈልገውን እየሰራሁ ነው። አንባገነኑን ጨቋኙን አገዛዝ ለመታገል በተደረገው ሂደት ውስጥ በማለፌ እና ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል ውስጥ አስተዋፅኦ በማድረጌ ደስተኛ ነኝ።

በኢሳት ውስጥ ያለነው ባልደረቦች ተመካክረን እና ተናበን የምንሰራ በመሆናችን ውጤታማ ሥራ ሰርተናል። በአገር ውስጥ የሚደረገውን አፈናና በደል ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በመሰብሰብ እና አየር ላይ በማዋል የአገዛዙን ማንነት ለማጋለጥ በመቻላችን እደሰታለሁ። መስራት የምፈልገውም ይህንን ነበር፤ በዚህ የተነሳ ደስታዬ የተለየ ሊሆን ችሏል።

**ግዮን፡- ኢሳት ውስጥ ከሌሎች የሙያ አጋሮች ጋር ውይይት ብምታደርግበት ጊዜ አንተ ላይ የተለየ እልህ እና ቁጭት ይስተዋላል፤ ይሄ ከምን የመጣ ነው?**

አፈወርቅ፡- ዜና ሳነብም ሆነ ከሌሎች የሙያ አጋሮቼ ጋር ውይይት ሳደርግ እልህና ቁጭት የሚሰማኝ ምክንያት በውስጤ የተዳፈነ ስሜትን ስላዘልኩ ነው፤ ምርጫ አለ ሲባል ድምፅ ሰጥተው ድምፃቸውን ተሰርቀው ባዶ እጃቸውን ወደ ቤታቸው የገቡት ሰዎች ድምፅ ያንገበግበኛል።የምርጫ 97 ሰቆቃ ከውስጤ አልጠፋም።በ1997 ዓ.ም በአገሪቱ በተካሄደው ምርጫ የድምፅ ኮሮጆ ተሰርቶ ከ197 በላይ ሰዎች እንደሚታደኑ አውሬ ሲገደሉና ሕይወታቸው ሲያልፍ ይቆጨኛል። የ14 ዓመት ልጅ ሳይቀር ባንክ ሲዘርፍ ነው የተገደለው ተብሎ ሲነገር፤ ኅብረተሰቡ በሙሉ ወደ ወህኒ ቤት ሲታጎር፤ አገራችን ምን ጉድ ፈላባት በሚል ውስጤ ይንገበገባል። የወገኖቼ ሞት ሰቆቃ መከራ ያመኛል፤ ይሄ ወደ ውስጤ እየገባ ቁጭት ያጭርብኛል፤ ለዚህ ነው እልህና የሚተናነቀኝ፤ከዚህ ውጪ ግን ሰውን በማንነቱ አልኮንንም።

ለሕዝብ የሚቆም ፤የወገኖቼ ችግር መከራ የሚሰማው መንግስት በኢትዮጵያ ባለመኖሩ፤ ዘወትር ውስጤ ይንገበገባል ይሄ ያስቆጣኛል። ከዚህ ውጭ የምቆጭበት የምናደድበት ነገር የለም። አሁን ትንሽ የለውጥ ብልጭታ ታይቷል ይሄ እንዳይቀለበስ መጠበቅ ይኖርብናል።

**ግዮን፡- የሕወሓት ኢህአዴግ ሥርዓት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በሚመራው የለውጥ ሥርዓት ሲተካ ምን ዓይነት ስሜት ተሰማህ?**

አፈወርቅ፡- እኔ በዚህ ደረጃ ለውጥ መጥቶ የኢትዮጵያን ምድር ረግጬ፣ አፈሯን እንካለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም። ይሄ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚሆን ነው። በርግጥ ሕዝባችን ታግሏል፣ ብዙ መስዋዕትነት ከፍሏል። በኢሕአዴግ ውስጥ ያሉ አካላት ለውጥ ፈላጊ ሆነው መጥተው፣ ለዚህ መብቃት አስገራሚ ነው። ከውስጥ እና ከውጭ በተቀናጀ ለውጥ ሕወሐት ኢህአዴግ ወደዚህ ደረጃ ይሸቀነጠራል ብሎ ያሰበ አልነበረም። አሁን ነጻነት ነጻነት የሚሸት አስተዳደር አለ፤ ገና አልተጠናቀቀም። ነገሩ የሚያስደስት ነው። ሞት የተፈረደባቸው፣ ፓርላማ ላይ የተወገዙ፣ እስር ቤት የታጎሩ ተቃዋሚዎች ተፈተው ፣ለዚህ መብቃታቸው እና የነፃነት አየር ለመተንፈስ መቻሉ ቀላል አይደለም። መስዋዕት የሆኑትን አምላክ እንዲያስባቸው ከመለመን ውጪ ምን ልንል እንችላለን? እነሱን ለማስታወስ ደማቸው የትም ባክኖ እንዳልቀረ ለማሳየት ለአገር ሲባል የተከፈለ መሆኑን ለማሳየት የምንዘክርበት ጊዜ አሁን ነው። በሕወሓት ኢሕአዴግ ጥቂት የሞቱት ሰዎች ካሳ ተሰጥቷቸው፣ ቤተሰቦቻቸው እንዲቋቋሙበት የሚያደርግ መንግስት እንደሚሆን እገምታለሁ።

በአገራችን ብዙ መስዋዕትነት ከፍለው የዛሬውን ለውጥ እንድናይ ያደረጉ በርካቶች ናቸው። በተለይ በ1997 ዓ.ም የተደረገውን ግድያ በማጋለጥ አኩሪ ሥራ የሠሩ ዳኞች ኃይለሚካኤል መሸሻ እና ፍሬ ህይወት ሊመሰገኑ ይገባል።

ደማቸው የፈሰሰ ፤አካላቸው የጎደለ ኢትዮጵያውያን የሚታሰበቡበት፤ ሞታቸው ለኛ ሕይወት መሆኑን የምንዘክርበት ጊዜ በመሆኑ ደስታዬ ወሰን የለውም።

**ግዮን፡- ከ20 ዓመት በኋላ ወደ አገር ቤት ለመምጣት በዝጅግት ላይ ነህ ምን ተሰማህ?**

አፈወርቅ፡- ኃይላችሁ ኃይላችን ሆኖ በሁለት እግራችን እንድንቆም ያደረጋችሁን እናንተ ናችሁ፤ ለእኛ የጀርባ አጥንታችን ናችሁ። ልክ እንደ አከርካሪ አጥንት ባትደግፉን ኖሮ ኢሳት ኢሳት ሆኖ ወደ አየር አይወጣም ነበር። ለበርካታ ጊዜ ከአየር ሳንወርድ፣ አይዟችሁ እያላችሁ የእኛን ዓላማ ጠንቅቃችሁ በመረዳት ፣ሁለንተናዊ ድጋፍ ያደረጋችሁልን ሁሉ ለእናንተ ክብር ይገባችኋል። አሁንም ድጋፋችሁ አይለየን ከጎናችን ሁኑ። የተሳሳትነውን እያረምን፣ በተሻለ አቀራረብ እየሰራን ወደ እናንተ እንደርሳለን፤ በዚህ አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ።



# “በጋዜጠኝነት ቅንጦት ውስጥ አይደለም ያለሁት”

## ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና

**ግዮን፡- በነጻው ፕሬስ ዘርፍ ለበርካታ ዓመታት ስታገለግል ከቆየህበት ኢትዮጵያ በምን አጋጣሚ ነው የወጣኸው?**

ሲሳይ፡- ፔን ኢንተርናሽናል የተባለው የጋዜጠኞች ተቋም ያበረከተልኝን ሽልማት ለመቀበል ነው ከኢትዮጵያ ወጥቼ አሜሪካ የገባሁት። እኔ በወጣሁበት ወቅት ደግሞ የኢሳት ዋሽንግተን ስቱዲዮ በከፊል ሥራ የጀመረበት ጊዜ ነበር፤ በሀገር ቤት መድረክ ተነፍጌ ስለነበር የተገኘው አጋጣሚ ለእኔ ትልቅ ነገር ነበር፤ በወቅቱ በዚህ ስራ ላይ በኃላፊነት የነበሩ ሰዎች እኔ አሜሪካ እንደገባሁ ፍላጎቴን ጠየቁኝ።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ የማያሰራ በመሆኑና ያገኘሁትም መድረክ ትልቅ ስለሆነ ጥያቄውን ተቀብዬ በደስታ ኢሳትን ልቀላቀል ችያለሁ። ከሀገር የወጣሁት በታህሳስ ወር 2003 ዓ.ም ነው። በአጠቃላይ እንግዲህ ኢትዮጵያን ከለቀቅኩም ሆነ ኢሳት ውስጥ ስራ ከጀመርኩ ስምንት ዓመት አለፈኝ ማለት ነው።

**ግዮን፡- ኢትዮጵያ ውስጥ በነበርክበት ጊዜ የሰራህባቸው ሚዲያዎች እነማን ነበሩ?**

ሲሳይ፡- በሀገራችን ነፃው ፕሬስ በተጀመረበት ወቅት የመጀመሪያዎቹ አንድና ሁለት ዓመታት ውስጥ ለተለያዩ ጋዜጦች መጣጥፎችን እና ዜናዎችን እጽፍ ነበር።ከጥቂት ጊዜ በኋላ ተሳትፎዬን የገመገሙ ሰዎች በአዘጋጅነት እንድሰራ በጋበዙኝ መሰረት መጀመሪያ ዛጎል የተሰኘ ጋዜጣ ላይ በዋና አዘጋጅነት መሥራት ጀመርኩ፤ ከዛ በኋላ ኢትኦጵ ጋዜጣ ላይ እንዲሁ የአዘጋጅነት ዕድል አገኘሁ።

ያኔ በወቅቱ ከጋዜጣ ጋር በተያያዘ አዘጋጆችና አሳታሚዎች የሚታሰሩበት አጋጣሚ ስለነበር በጅምላ ተይዘን ወደ ወህኒ ተጋዝን። በወቅቱ የጋዜጣው ባለቤት የነበሩት አቶ ብሩክ ዶሚኒክ “ከዚህ በኋላ በእንዲህ ያለ ሁኔታ መሥራት አልፈልግም፤ ስለዚህ ጋዜጣውን ሙሉ በሙሉ ይዘህ መቀጠል ትችላለህ” በሚል ፍቃዱን ወደ እኔ አዞሩ። ቀደም ሲል ከእርሳቸው ጋር እንደዚሁ በጋዜጣ ስራ የተያዙ ሰዎች ሲታሰሩ “እኔ አይመለከተኝም እርሱ ነው” በሚል እሳቸው ላይ ኃላፊነቱን የማሸከም ነገር ስለነበር፤ እኔ ደግሞ

ስገባ እውነተኛውን ነገር በመናገር “እሳቸው አስተማሪ ናቸው፤ በባለቤትነታቸው ክፍያ ያገኛሉ፤ ከዛ ውጭ ምንም ነገር ውስጥ አይሳተፉም” በሚል ያልጠበቁትን ነገር ስለመሰከርኩ፣ ያንን የጋዜጣ ፍቃድ ወደ እኔ ሊያዞሩ ችለዋል፡

በዛ መሰረት ኢትኦጵ ጋዜጣን ይዘን ለረዥም ዓመታት (በኋላ መጽሔት ጨምረን) በፕሬሱ ላይ መቆየት ችለን ነበር፤ በኋላ ምርጫ 97 አካባቢ ነገሮችን መገምገም እንዳለብን ተወያይተን ወሰንን፤ በተለይም ምርጫ 97 ከመድረሱ በፊት የኢትዮጵያ ፖለቲካን በተመለከተ የየዕለቱን ጋዜጣ የምንገመግምበት ሁኔታ ነበር። ከሰኞ እስከ እሁድ ባሉት ቀናት ላይ የፖለቲካ ጉዳይ መሰራት አለበት የሚል አንደምታ በመያዝ ከኢትኦጵ በተጨማሪ “አባይ” የተባለ ቅዳሜ የሚወጣ ሳምንታዊ ጋዜጣን አቋቋምን። በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተነባቢነት እና ታዋቂነት ያገኘ ሆነ፤ በዛ መሰረት ሁለቱን ጋዜጦች እያሳተምን እስከ መጨረሻው ብንቆይም ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ በርካታ ጋዜጦች ሲታገዱ ሁለቱም የእኛ ጋዜጦች በተመሳሳይ ከህትመት ታገዱ።

በወቅቱ የኢትኦጵ እና አባይ ጋዜጠኞች ቃሊቲ ወርደን ነበር። አንድ ዓመት ከመንፈቅ በላይ ቆይተን ከእስር ስንፈታም በኢትዮጵያ ውስጥ ጋዜጣና መጽሔት ማሳተም መፃፍም የማይቻልበት ሁኔታ በመፈጠሩ ወደ ውጭ የመውጣቱን ዕድል ሳገኝ አሜሪካ ገብቼ ኢሳትን ልቀላቀል ችያለሁ።

**ግዮን፡- ኢሳት ላይ በምትሠራቸው ቃለመጠይቆች ብዙ ሰዎች ያደንቁሃል፤ እንግዶችህን ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ነው የምትመርጣቸው ወይስ በሌላ መንገድ?**

ሲሳይ፡- ዘወትር ረቡዕ በሚዘጋጀው “የሳምንቱ እንግዳ” በሚለው ፕሮግራም ላይ ነው ለቃለመጠይቅ የሚመረጡት ሰዎች፣ በተቻለ መጠን ታሪካቸው እና ልምዳቸው ለትውልድ ፋይዳ የሚኖረው፤ ከዚህም ባሻገር እንግዶቹ የሚያካፍሉት ቁምነገር የኢሳት ተመልካችን ያንጻል ተብለው የሚገመቱ ናቸው።

ከዛ ውጭ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ውይይቶች ይኖራሉ። ከተለያዩ ባለሙያዎች ጋር በወቅታዊ ጉዳይ ዙሪያ የሚደረገው ውይይት ከዚህ “ከሳምንቱ እንግዳ” ጋር አይገናኝም።ውይይቶቹ ራሳቸውን የቻሉ እና በተለያዩ ፕሮግራሞች የሚቀርቡ ናቸው። ግን እንግዶቹን በተመለከተ በተቻለ መጠን በተሰማሩበት የሙያ መስክ ወይም ኃላፊነት የተወሰነ ልምድና ታሪክ አላቸው የምንላቸውን ሰዎች ለማግኘት እየሞከርን የምናቀርብበት ፕሮግራም ስለሆነ እንግዶቹን ስንመርጥ ቀደም ሲል ያነሳነውን መመዘኛ ነው በዋናነት የምናስገባው።

**ግዮን፡- ሕወሓት/ኢሕአዴግ ሥልጣኑን እንዲያጣ የኢሳት ተፅዕኖ ምንያህል ነው ትላለህ?**

ሲሳይ፡- ኢሳት ትልቅ ሚዲያ ነው። ሚዲያ ያለውን ጉልበት ደግሞ ማንም የሚረዳው ነው።በተለይ ደግሞ ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ማንበብ መጻፍን የማይጠይቅ፤ ማንም ሰው በቤቱ ቁጭ ብሎ ሊከታተለው የሚችል፤ ከመሆኑ የተነሳ በተለይም ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ ሆኖ የሚሰራ፤ ወይም የሀገሪቱ ህግ የማያገዛው፤ በሕግ ሽፋን ሰዎችን ወይም ጋዜጠኞችን አልያም ሌሎች ወገኖችን ማሳደድ የማይቻልበት፤ በሙሉ ነፃነት የሚሰራበት ሚዲያ ስለሆነ ቢያንስ ላለፉት ስምንት ዓመታት ትልቅ ነገር ሰርቷል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ትልልቅ ሰቆቃዎች ሲፈፀሙ ፣ህዝቡ ተስፋ በቆረጠበትና ከፍተኛ ድብታ ውስጥ በገባበት ጊዜ፣ ያን ድብታ የሚሰብር፣ ኢትዮጵያን በተለያየ መንገድ ከመከራ ለመታደግ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ሰዎች እንዳሉ በመናገርና በማስረዳት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሰው እዛው እየኖረ የሚያያቸውን በሥርዓቱ ውስጥ ሆኖ የሚያጋልጥበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር።

በዚህም የተነሳ የሚደርስብን ተፅዕኖ ገሀድ እየሆነ መጣ፤እንደውም አንዳንዶቻችን ላይ ቤተሰቦቻችን ድረስ በመሄድ ጫና ለመፍጠር ሞክረው ነበር። ይሄ ደግሞ የሩቅ ጊዜ ክስተት ሳይሆን ከሁለት ዓመት በፊት በግልፅ የታየ ነገር ነው። ቤተሰቤ በእኔ የተነሳ እንግልት ደርሶበታል ። የእኔን ቤተሰብ ለማስፈራራት በሞከሩበት በእዛኑ ዕለት ደግሞ ወደ ጎንደር ተጉዘው በታማኝ በየነ ቤተሰብ ላይ ያደረጉት ነገር ይታወቃል። በወቅቱ የሆነውን አደባባይ ወጥተን ተናግረናል፤ ‹‹ያንን በማድረጋችሁ ለመብትና ለነፃነት የምናደርገውን ትግል አናቆምም›› ብለን መግለጫም አውጥተን ነበር።

ይሄ የሚያሳየው የኢሳት ተፅዕኖ ባይኖር ኖሮ እንዲህ ዓይነት እርምጃዎች ውስጥ እንደማይገቡ ነው። ተፅዕኖ ፈጣሪ ባይሆን ኖሮ ኢሳት ከሃያ አምስት ጊዜ በላይ ሳተላይት እንዲቀይር አይገደድም ነበር፤ ተፅዕኖው ለእነሱም ግልፅ ነው ለኢትዮጵያ ህዝብም ግልፅ ነው።

**ግዮን፡- ከለውጡ በኋላ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ በተከታታይ ለአንተ ያላቸውን አድናቆት ሲገልፁ ይሰማል፤ ይሄን እንዴት አገኘኸው?**

ሲሳይ፡- ለማንም ሰው በሀገር መሪ ደረጃ ስሙ በበጎ ሲነሳ በጣም ትርጉም ይኖረዋል። በሀገር መሪ ደረጃም ብቻ ሳይሆን በህዝብ ዘንድ በጣም ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ በሆኑት በጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ስሜ በመልካም ጎኑ መጠቀሱ እጅግ በጣም የሚያስደስት ነገር ነው።

በዚህ ላይ ልናገር የምችለው ምናልባት በተለያየ መንገድ ሲሳደድ እና ከሀገሩ ሲባረር ለነበረ ሰው፣ በህዝብም ዘንድ በጣም ተወዳጅ በሆኑ የሀገር መሪ ስሜን በአደባባይ አንስተው በዛ መልክ መጥቀሳቸው፣ ለእኔ ትልቅ ነገር ስለሆነ በዚህ አጋጣሚ እጅግ አድርጌ ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

**ግዮን፡- አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች የጠ/ሚ/ሩ አድናቆት ከመጣ በኋላ በውይይቱ ላይ የሲሳይ ትችቶች ቀንሷል ይላሉ። አንተ ለዚህ ምላሽህ ምንድን ነው?**

ሲሳይ፡- እንዲህ ያለውን አስተያየት የሚሰጡ ሰዎች ከምን ተነስተው እንደሚሰጡ አላውቅም፤ ጎሰኝነትን ፣ዘረኝነትን፣አድሎአዊነትን፣ኢዴሞክራሲያዊ የሆነ አሰራርን ስተች ነው የኖርኩት። አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ የመጣው ሁኔታ ከዚህ በተቃራኒ ዘረኞችን፣ኢዴሞክራሲያዊነት፣አፈናን እና ግድያን የሚያወግዝ፤የተሰደዱ ሰዎች የተመለሱበት፤የታሰሩ የተፈቱበት፤ በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ከመቃብር የወጡበት ሁኔታ ውስጥ ነው ያለነው። ይሄንን ልተች አልችልም።

ከዚህ ውጭ ይሄ በደል ደርሶ፣ ይሄ ሁኔታ ተፈጥሯል ብሎ የሚያነሳ ሰው ካለ በዛ ላይ ልንከራከር እንችላለን።ከምንም በላይ ኢትዮጵያን ጫፍና ጫፍ ዘረኞች እየጎተቱ አደጋ ውስጥ ሊጥሏት በሚጣደፉበት በዚህ ወቅት፤ ሥልጣናቸውን የተነጠቁ ሰዎች በተመሳሳይ አቅም መልሶ ለመያዝ በሚወራጩበት ሰዓት፤ ተጨማሪ ችግር፣ ተጨማሪ መከራ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማትረፍ አለብኝ ብዬ አላምንም።

ስለዚህ ትናንትም የማደርገው፣ ዛሬም በማደርገው ላይ ልዩነት የለውም። ልዩነቱ ትናንት ቤተ መንግስት የነበሩት ሰዎች ፀረ ኢትዮጵያ ፣ ፀረ ዴሞክራሲ እና ዘረኞች ነበሩ፤ በአንፃሩ አሁን ቤተ መንግሥት የገቡት ሰዎች የእዚህ ተቃራኒ ናቸው። እነዚህ ሰዎች የጀመሩት መስመር ስልጣን ላይ እየቆዩ ሲሄዱ ወደ አንባገንነቱ የሚያመሩ ከሆነ ፣ያኔ ያንን መስመር ተከትዬ አብሬ የምደግፋቸው ከሆነ ይሄ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። አሁን ባለው ሁኔታ ውስጥ ግን ትናንት የማደርገውና ዛሬ በማደርገው መካከል ልዩነት የለውም። እኔ በጋዜጠኝነት ቅንጦት ውስጥ አይደለም ያለሁት፤ ኢትዮጵያን ወደ መከራ ሊሰዱ የሚፈልጉ ኃይሎች በሙሉ አቅማቸው በሚወራጩበት ሰዓት መንግስት ላይ ትችት ማቅረብ ስራ አድርጎ የሚመለከት ካለ፣ ይሄ የጋዜጠኝነት ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም።የጋዜጠኝነት ተግባር እውነትን መሰረት አድርጎና ተመርኩዞ ከተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተነስቶ አስተያየትን በትንተና መስጠት ነው ብዬ ነው የማምነው።

**ግዮን፡- በጉጉት ለሚጠብቃችሁ የኢትዮጵያ ህዝብ የምታስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው?**

ሲሳይ፡-ከስምንት ዓመት በፊት እኔ ከሀገር ስወጣ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉ ነገር የተደፈነበት፣ ጨለማ ያረበበት ነበር። ከወጣሁ በኋላ ደግሞ ጨለማው በጣም የበረታ ሆኖ ነበር፤ አሁን ከስምንት ዓመት በኋላ ጨለማው ተገፎ ፣ሙሉ ለሙሉ ደግሞ እንዳይገፈፍ ኢትዮጵያውያንን ስጋት ውስጥ የሚከቱት ኃይሎች ዳርና ዳር ቆመው ችግር እየፈጠሩ ያሉበት ሁኔታም ቢኖር ከዚህ በኋላ ተመልሰን ወደ እዛ ፅልመት የማንመለስበት ትልቅ ተስፋ ሰጪ ሁኔታ ውስጥ ስላለን የኢትዮጵያ ህዝብ ከዛ መከራ ተፋትቶ፤በሀገሩ የባለቤትነት መብቱ ተረጋግጦ፤ የሚኖርበት መሰረት ስለተጣለ ከምንም በላይ የእኔ ወደ ሀገር መመለስ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ከመከራ ውስጥ በመውጣቱ ህዝብን እንኳን ደስ አለህ ማለት እፈልጋለሁ። እኔም በግሌ ከጓደኞቻችን ጋር በአጠቃላይ ተቋማችን ወደ ኢትዮጵያ መግባት የቻለበት አጋጣሚ በመፈጠሩ በጣም ደስተኛ ነኝ።

የእውነት ለመናገር እኔ ለውጡ ከመጣ በኋላ ከኢትዮጵያ ብዙ ሩቅ ያለሁ አይመስለኝም። በማንኛውም ቀን ተነስቼ መሄድ የምችልበት ሁኔታ እንደተፈጠረ ስለተገነዘብኩ፣ አንዳንዴ አራት ኪሎ ወይም ፒያሳ ያለሁ ያህል እስኪሰማኝ ድረስ ካለፉት ዘጠኝ ወራት ወዲህ ኢትዮጵያ ቅርቤ ነበረች። ስለዚህ ባለው ሁኔታ በጣም ደስተኛ ነኝ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ አሁንም ያ የጨለማና የመከራ ዘመን ተመልሶ እንዳይመጣ በጥንቃቄ ማድረግ የሚችለውን ነገር እያደረገ፣ ሁሉም በግሉ ኃላፊነቱን እንዲወጣ እጠይቃለሁ። እኔም በግሌ ከዚህ ቀደም እንደማደርገው ሁሉ በጋዜጠኝነት ሙያዬ ኢትዮጵያ ወዳላፈው አስከፊ ዘመን እንዳትገባ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ። በጣም አመሰግናለሁ።

**ግዮን፡- እናመሰግናለን።**

**ስለዚህ ትናንትም የማደርገው፣ ዛሬም በማደርገው ላይ ልዩነት የለውም። ልዩነቱ ትናንት ቤተ መንግስት የነበሩት ሰዎች ፀረ ኢትዮጵያ ፣ ፀረ ዴሞክራሲ እና ዘረኞች ነበሩ፤**

**ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌናን በግል ሕይወቱ፣ በሥራ ተሞክሮው እና በወቅታዊ ሀገራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያደረግነውን ቆይታ በቀጣይ ይዘን የምንቀርብ መሆኑን ከወዲሁ እንገልፃለን።**

# ቤት ለእምቦሳ!

## የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን



በጌታቸው ወርቁ




**መቅድምወ ዳራ፥- በዚያ በድቅድቅ ጨለማ!**

እነሆ የኢትዮጵያ ፖለቲካ፣ምጣኔ ሃብት፣ማኅበራዊ ሕይወት እና ሞራላዊ ኹኔታ (የፈለጉትን የማመን መብት) በኢ-ፍትሓዊ የአድሎ የመንደር አስተዳደር ተጠፍንጎ፤ የጥቂት ‹‹ምርጦች›› መቀማጠያና መጠቃቀሚያ በሆነበት በዚያ ጨለማ የእመቃ- ዘመን።

ገዢው ፓርቲ ህወሓት/ኢህአዴግ ባነበረው አፋኝ ሁሉን ጠቅላይ ሥርዓት፣ ኑሮ እያደር እየከፋ- እየከፋ፣ እንደገናም በብዙ እጥፍ እየከፋ በሄደበት በዚያ በድህረ-ዘጠና ሰባት ምርጫ- ማግስት።

በዚያ ነፃ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲፈርሱ፣ መሪዎቻቸው እንዲታሰሩ፣ እንዲሰደዱ፣ እንዲመክኑ እና በአድርባይ አስመሳይ ከርሳሞች እንዲተኩ በተደረገበት- ዘመን፤ በዚያ ሲቪክ ማኅበራት ምርጫ ዘጠና ሰባትን በነፃነት ታዘባችሁ ተብለው በ‹‹ሰባ ሠላሳ‹‹ እና በ‹‹አስር ዘጠና›› ‹‹ሕግ›› ተተብትበው እንዲከስሙ በተደረገበት- ዘመን፤ በዚያ የሃይማኖት ተቋማት በህወሓት ካድሬዎች ፈላጭ ቆራጭነት ከጀርባ- ከፊት በሚመሩበት- ዘመን።

በዚያ የገዢው አጠቃላይ ጠቅላይነት በበረታበትና ጫናውም ክቡድ በሆነበት የድቅድቅ ጨለማ- ዘመን፤ በሀገር ውስጥ የሚታተሙ ነፃ ወይም ህዝባዊ የኅትመት ብዙሃን መገናኛዎች በታሰሩበት፣ በተዘጉበት፣ በደኸዩበት እና በተጋዙበት ክፉ የመከራ- ዘመን።

በዚያ የግል ተብለው በመንግሥት ሳንባ የሚተነፍሱ ኤፍ ኤም ራዲዮ ጣቢያዎች እና ጥቂት የቴሌቭዥን ማሰራጫዎች በማዝናናት ሰበብ፣ በዜጎች ላይ ልቅ አደንዛዥ ዕፅ ሆነው ተጣብቀው የሕዝብ አመለካከት አቅጣጫን ወደ እርካሽ እንስሳዊ የደመነፍስ ፍላጎት የማውረድና የማስቀየር የ‹‹ላፕ ዶግ›› ሚና በሾርኒ በሚጫወቱበት- ዘመን።

በዚያ በቴአትር ቤቶቻችን የሚቀርቡ ቴአትሮች በመላ፣ በትዕይንቶቻቸውና በገቢሮቻቸው ላይ ሰላሳ ከመቶ የልማታዊና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አሻር ባሻር መረቅ እንዲመርቁ፣ በተመረቀላቸው የጥበብ ድርቀት- ዘመን።

በዚያ ህፃናት ተማሪዎች በምግብ እጥረት ክፍል ውስጥ እያዞራቸውና እያጥወለወላቸው በሚወድቁበት፤ ምስኪን የከተማ አረጋውያን አበው እና እመው በልማት ሰበብ ከቤታቸው፣ ከሥፍራቸው በሚፈናቀሉበትና ጎዳና በሚወጡበት- ዘመን።

በዚያ ዜጎች ያለምንም ጥፋታቸው ከዚህ ወገን ናችሁ ተብለው በማንነታቸው ብቻ ተነጥለው ለዓመታት ተጋብተው፣ ተዋልደው ጎጆ ቀልሰው፣ አርሰው እና ሀገር አቅንተው ከኖሩበት የሀገራቸው ሥፍራ ይጠለሉበት መጠጊያ ጥግ አጥተው ንብረታቸው ተዘርፎ በሚሳደዱበት- ዘመን።

በዚያ ብቸኛው አውራ (አውሬ) ፓርቲ ጉልበቱ በገነነበት፣ በዚያ አስፈሪ ፈርያናዊ- ዘመን፤ በዚያ ሠርክ 11 በመቶ የኢኮኖሚ እድገቱን የህዝቡ አስመስሎ እራሱ እያዜመ፣ እራሱ ከበሮ እየደለቀና እየተሸከረከረ አዳር በሚጨፍርበት የዛር- ዘመን።

በዚያ የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቭዥንና ጣቢያ (ኢቲቪ)፣ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ኢዜአ)፣ ራዲዮ ፋና፣ ዋልታ የመረጃ ማዕከል፣ አዲስ ዘመን፣ በሪሳ፣ ኢትዮጵያን ሄራልድ፣ ዓል-አለም ጋዜጦች የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ዲስኩር በሚሰብኩበት- ዘመን።

በዚያ ‹‹ዘመን መጽሔት››፣ ‹‹አዲስ ራዕይ መጽሔት›› ዜጎችን ልማታዊ መንግሥትን በሚያጠምቁበትና የኢህአዴግ አባልነትን በሚያሳልጡበት- ዘመን።

በዚያ ኤፍ ኤም 97፣ 98፣ 93፣ 63፣ 90፣ 100፣ 104 እና የየክልሉ ኤፍ ኤም ጣቢያዎችና የተወሰኑ የ‹‹ሃገረሰብ የራዲዮ ጣቢያ›› የተሰኙ፣ በተግባር የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ዲስኩር የሚቀነቀንባቸው የራዲዮ ጣቢያዎች ሁሉ በአንድነት ተቀናጅተው የእብድ ኦኬስትራ መሥርተውና አሰልጥነው ታላቅ የፕሮፓጋንዳ ሥራ በሚያጫፍሩበት የጨረባ- ዘመን ነበር።

እነሆ አንድ ብላቴና ብዙኃን መገናኛ፣ ዘሩ ከታማሚ እናቱ ማኅፀን ወጥቶ፣ በኪራይ ማህፀን ወደ ዚህች ምድር የተከሰተ።ስሙም እነሆ ‹‹የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን›› ተሰኘ፤ በትርጓሜም በይዘትም የኢትዮጵያ ዓይን- ጆሮ- አንደበት ማለት ነው፤ ሆነም።

እርሱም አንድ ለእናቱ ነበር።በወቅቱም፣ በሀገረ ኢትዮጵያ ብዙ ነገር ተስተጓጉሎ ነበርና ውልደቱም ከውጭ ወደ ውስጥ የተገላቢጦሽ- ነበር።

ይህ ሕዝባዊ ሚዲያ በውጭ አገር ምናልባትም አንድም በአውሮፓ- ሆላንድ፤ አንድም ►

በዋሽንግተን ዲሲ- አሜሪካ፤ አንድም በእንግሊዝ ሎንዶን- ሕጋዊ የልደት ሠርተፍኬቱን (ፍቃዱን) አግኝቶ፤ ለታፈነውና ድምጽ የለሽ ለሆነው መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተደማጭ ድምጽ ሊሆን፤ለተጠቁትና ለተበደሉት የአደባባይ መከታና እና ሞጋች ሊሆን፤ ለነገ (ለዛሬ) የታሪክ ሰነድ የሚሆን ኹነቶችን ዘግቦ ሊያስቀር፤ በውጭ በሚገኙ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን እውቀት፣ ጉልበት እና ገንዘብ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ሲባል ‹‹ማርያም- ማርያም›› ተብሎ ተወለደ፡፡እነሆም ከእናቱ ጉያ ውጪ፣ የእናቱኝ ጠረን እየናፈቀ አደገ፤ ተመነደገም፡፡

ይህ ከላይ የተዘረዘረው ሀገራዊ ኹነት፣አንድም ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን መቋቋምና አሁን የያዘውን ተክለ ሰውነት ይዞ ስለመወለዱ፤አንድም ተሟጋች አንደበት ስለመሆኑ፤ አንድም ተከላካይ ስለመሆኑ እነሆ ታሪካዊ ዓውዱ ምስክር ነው፡፡

በዜጎች፣ በማኅበረሰብ እና በተቋማት መካከል የሚከናወን ማንኛውም መሆን ከሚገባው ከትክክለኛው ተፈጥሯዊው መንገድ የአፈነገጠ ድርጊት፣ ጫና ሲከናወን፣ በአንፃሩ የሁሉንም ነገረ-ተፈጥሮ ባህርይና ድርጊት ወይም መዳረሻ እንደሚያዛባውና እንደሚለውጠው በማኅበረሰብ ሳይንስ ባለሚሎች የታወቀ እውነት ነው፡፡every new causes in everything, have every new effects- also እንዲሉ፡፡

**ኢሳት፥-**

‹‹የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን››ን ለመገምገም የሚነሳ የብዙኃን መገናኛ ባለሚል፤ ይህን ሀገራዊ ታሪካዊ ዳራ ሳይመለከት ሌጣውን የጋዜጠኝነት ኹነት ብቻ ነጥሎ ቢመለከት፤ ‹‹ወገናዊ ጣቢያ›› የሚል ችኩል ድምዳሜ ላይ ይደርሳል የሚል ምልከታ አለኝ፡፡

ምክንያቱም የጋዜጠኝነት ሙያ የተወለደው፣ በሃሳብ ነፃነት ልዕልና፣ በመደራጀት መብት መከበር፣ በመንቀሳቀስ መብት መረጋገጥ፣ በአጠቃላይ ዴሞክራሲያዊና ሰብኣዊ መብቶች መከበርን ተገን አድርጎ ነው፡፡የሚዲያ ነጻነት ትልቅ ቢሆንም ቅሉ፣ ብቻውን ምንም ነው፡፡

ስለሆነም፣ አጠቃላይ የሀገሪቱን ዓውድ በሙያዊ መንገድ ተመልክቶ ‹‹የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን›› ወገናዊ ነው ወይ? ለሚለው የገለልተኛ ባለሚል ጥያቄ- ‹‹አዎን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን ወገናዊ ነው፤ እርሱም ለሕዝብ መወገኑ ነው ወገናዊነቱ›› የሚል ነው-መልሴ፡፡

እንደማስታውሰው፣ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን የመገናኛ ብዙኃን ሥራውን የጀመረው ከሀገር ውጪ በድረ-ገጽ ላይ በጽሑፍና በምስል በሚያቀርባቸው ሀገራዊ ዜናዎች፣ ሪፖርታዥ፣ ዜና-ሃተታ፣ ዜና-ትንታኔ፣ ፊቸር፣ አርቲክል፣ ቃለ-መጠይቅ፣ የጣቢያው አቋም ወዘተ በማቅረብ ሲሆን፤ በሂደት የሳተላይት ራዲዮ ፕሮግራም በመጀመር፣ በድምጽ ተደራሽ ወደ መሆን ተሸጋግሯል፡፡

በመቀጠልም፣ በድምጽወ ምስል (ተንቀሳቃሽ ምስልና የድምጽ ኅባሬ) የሳተላይት የቴሌቭዥን ጣቢያ በመገንባት ተደራሽነቱን በቃላት ጽሑፍ፣ በድምጽ እና ተንቀሳቃሽ ምሥል ኅብረት አድርጎ ራሱን በ‹‹መልቲ ሚዲያ›› ቅርጽ አጎልብቷል፡፡

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን የሀገር ውስጥ ዘጋቢዎች በመላ ኢትዮጵያ በነጻነት ተንቀሳቅሰው መረጃ፣ ድምጽ እና ምስል የሚሰበስቡበት፣ የሚተነትኑበትና የሚያሰራጩበት ሀገራዊ ምኅዳር ባለመኖሩ፤ ከቀበሌ ካድሬ እስከ የገዢው ፓርቲ የሀገር ውስጥ ሰላዮች ድረስ በሚደረግ ‹‹የሌባና ፖሊስ›› አሰቃቂ ጫወታ ነፍሳቸውን አስይዘው ነበር ተሹለኩልከው የሚዘግቡት፡፡

ይህም፣ የሕይወት ቁማር፤ ከዘጋቢው እስከ ዓርታኢው ድረስ ቁጡ፣ ቆፍጣና እና የተቋቋሙለትን ረብ ወይም ዓላማ ፈላጊ ስለሚያደርጋቸው፤ የአድራጊውን ሳይሆን የተደራጊውን፤ የአጥቂውን ሳይሆን የተጠቂውን፣ የላይኛውን ሳይሆን የታችኛውን የኅብረተሰብ ክፍል ድምጽ ከፍ አድርገው እንዲጮኹ የ‹‹ዎች ዶግ›› ሚና እንዲወጡ አስችሏቸዋል እላለሁ፡፡

እንደ ጋዜጠኝነት ሙያ ሳይንሳዊ ወጉም፣ በመጀመሪያ አካባቢ የህወሓት/ኢህአዴግ የጀርባ አጥንት የሚባለውን የአቦይ ስብሃት፤ የኢህአዴግ ሁለተኛ ሰው የሚባለውን የአቶ በረከት እና የሌሎችንም ቱባ ባለሥልጣናት (የወቅቱ ጉልቤዎች) ድምጽ ለማካተት ጥረው ትንፋሻቸውን ለማስደመጥ የቻሉ ሲሆን፣ የብዙኃን መገናኛው ማንነት (ህዝባዊነት) በገዢዎቹ በኩል ‹‹ሞኒተር ተደርጎ›› ሲታወቅ ግን፣ ስልክ ተጠርቅሞባቸዋል፡፡ዕድል ተዘግቶባቸዋል፡፡ዛቻ ተፈፅሞባቸዋል፤ በሀገር ውስጥ በሚከናወኑ አገራዊ ኹነቶች ላይ ምንም ዓይነት ቅርበት እንዳይኖራቸው ተገልለዋል፡፡ተሰደዋል፤ ተግዘዋል፤ ታስረዋል፡፡

ይህም፣ በሁኔታው የተቆጩ የሀገሪቱ ዜጎች ባሉበት አካባቢ ሁሉ፤ ያዩትን- የተመለከቱትን፤ የሰሙትን- ያደመጡትን፤ የቀመሱትን- ያጣጣሙትን መከራ ሁላ፤ የዳሰሱትን- የተገረፉበትን ሀገራዊ መረጃ ሁሉ፤ ራሳቸውን ዜጋ-ጋዜጠኛ አድርገው፣ የበጎ ፈቃድ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን ዘጋቢ፣ ፎቶ ጋዜጠኛ፣ ድምፅና ተንቀሳቃሽ ምሥል በስልካቸው ቀርጸው፤ እንደ አቅማቸው መጠን መረጃ ተንታኝ እና አሰራጭ እንዲሆኑ ሲቻላቸው ዐይተናል፡፡

## ሕዝባዊ ጋዜጠኝነት Vs ፕሮፓጋንዲስት!

በመንግሥት ብዙኃን መገናኛ በኩል ዘወትር ይደረግ የነበረውን ንቁ (ሆን ተብሎ) የሚፈጸም ሙያዊ ግድፈት፡- በተለይ ለመንግሥት ይጥቅማሉ የተባሉ ትንንሽ ኹነቶችን፣ ክስተቶችን፣ ሥራዎችን ሁሉ ማጋጋል፣ ማንቆለጳጰስ (over emphasize) ማድረግ፤ መንግሥትን ሊጎዱ ይችላሉ የተባሉ ትልልቅ ኹነቶችን፣ ክስተቶችን፣ሥራዎችን ሁሉ ደግሞ ጣል- ጣል ማድረግ፣ ማራከስ ወይም (under emphasize) ማድረግ፤ በሌላም በኩል ደግሞ የመንግሥትን ጥፋት ሁሉ መዝለል፣ አለማየት፣ አለማድመጥ፣ አለመዘገብ ወይም (special omit) ማድረግ፡፡

በአንፃሩ ደግሞ የተቃዋሚዎችን ስኬት ሁሉ መዝለል፣ አለመመልከት፣ አለማድመጥ፣ አለመዘገብ ወይም (special omit) ማድረግ፤ አሊያም፣ ‹‹አፓቼ ሳይለንት›› የመውሰድ የጋዜጠኝነት የሙያ ሥነምግባር ጉድለትና ግድፈት እንደሚታይባቸው የአደባባይ ሐቅ-ነበር፡፡

ይህን እውነት ወደ ‹‹ወመዘክር›› ቤተመዛግብት ጎራ ብሎ እና ሌላኛውንም ማንፀሪያ ኹነት ደግሞ ‹‹ዩ-ቲዩብ›› ውስጥ ገብቶ፣ የጊዜውን እውነት በሚዛናዊነት አጣርቶ በመረዳት የትኛው የሚዲያ ተቋም የቱን ኹነት እንዴት አድርጎ እንደዘገበው በማስተዋል የዘገባ ሂደቱን ሙያዊነት ወይም ሙያዊ ጉድለት ማስተዋል ይቻላል፡፡

በእኔ መረዳት፣ ከመንግሥት ብዙኃን መገናኛዎች የመረጃ ፍላጎትና የይዘት ትንተና በተቃራኒው የቆመው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን፣ በተግባቦት አጠቃቀም ቴክኒክ ግን የመንግሥት ብዙኃን መገናኛን ዘዬን አመሳስሎ ‹‹ፓራዲ›› አድርጎ፤ በኢትዮጵያ እንደ እውነት ማመሳከሪያነት እና የታሪክ ድርሳንነት በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

የ‹‹መንግሥት ብዙኃን መገናኛ›› (በተጨባጭ እውነታው ግን የህወሓት/ኢህአዴግ) እና ‹‹ነፃ ሚዲያ››ው መንግሥት አውቆ የሚያድበሰብሰውን እውነት የሚያጋልጡ ‹‹ሕዝባዊ›› ብዙኃን መገናኛዎች ከጅምሩ ጫፍ እና ጫፍ አጥናፍ ይዘው በሚያደርጉት የመረጃ መሰብሰብ (Information gathering)፣ የመረጃ ትንተና (information analyses)፣ የመረጃ ብያኔ (information category) እና የመረጃ ሥርጭት (information dissemination) አድማጭ ተመልካቹ አንዱን በአንዱ በርዞ የነፀረ እውነት (መረዳት) ላይ ለመድረስ የሚጠቀምባቸው ማባረጃ ሁለት አንፃሮች ሆነዋል ባይ ነኝ፡፡

እንደ ምሳሌም፣ ዘወትር ኢቲቪ-ን እና የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥንን እያባረዙ የሚመለከቱ አንዲት የቤት እመቤት ያዳበሩት ኹነትን የመረጃ መንገድ፣ በኢቲቪ በኩል የሚንቆለጳጰስ ምሁር ሲያዩ- ‹‹የመንግሥት ደጋፊ››፤ በኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን በኩል የሚንቆለጳጰስ ምሁር ሲመለከቱ- ‹‹አርበኛ፤ ታጋይ›› የሚል መረዳት ላይ እንደሚደርሱ፤ በግልባጩም፣ የመንግሥት ሚዲያው የሆኑ ሰዎችን ሲያንኳስስ- ‹‹የሕዝብ ወገን በመሆናቸው››፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን የሚያንኳስሳቸውን ባለሥልጣናት ‹‹ጸረ ሕዝብ ›› አድርገው እንደሚረዱ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በአንድ የዳሰሳ ጥናቱ ላይ ታዝቧል፡፡

ይህም በመሆኑ፣ ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥንን ጨምሮ 264 ብዙኃን መገናኛዎች (ድረ-ገፆች፣ ራዲዮ ጣቢያዎች፣ የቴሌቭዥን ቻናሎች በሀገሪቱ የስለላ መረብ እንዳይነበቡ፣ እንዳይደመጡ እና እንዳይታዩ ታግደው ‹‹ብሎክ›› ተደርገው እንደ ነበር የለውጡ ኃይል በአደባባይ ያሳወቀው ሀገራዊ ሃቅ- ነው፡፡

በመሆኑም፣የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን ከሕዝባዊ አገልግሎቱ ባሻገር፣ ለራሱም ከለውጡ ወዲህ ወደ እናት ምድሩ ተመልሶ ቢሮ ከፍቶ፣ ስቱዲዮ ገንብቶ እና ዘጋቢዎቹን ወደፈለገው ሀገራዊ ሥፍራዎች አሰማርቶ የሚዘግብበት ዕድል እንዲፈጠር የበኩሉን ተቋማዊ ሚናውን ተወጥቷል ባይ ነኝ፡፡

ሆኖም፣ አሁን ካለው ሀገራዊ ለውጥ ጋር የሚሄድ የተግባቦትና የጋዜጠኝነት ስትራቴጂና ቴክኒክ ነድፎ፣ ፍጹም ሙያዊ ወደ ሆነው እና የጋዜጠኝነት ሀሁ-ን እና ጋዜጠኝነት የሚያመራበትን የሙያ ሥነ-ምግባር መም ተልሞ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል፡፡የሚሰራቸውን ዘገባዎችም ሚዛናዊነትን በጠባቡ ትርጉሙ ሳይሆን፣ በምልዓት ትርጓሜው መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ቢተጋ፣ ያሰባሰበውን ብዝኃ-አድማጭ- ተመልካች ይዞ ረጅም የተግባቦት ጉዞ መሄድ የሚችል ይመስለኛል፡፡

ምክንያቱም ትላንት እርሱ እና መሰል የብዙኃን መገናኛ አውታሮች ብቻ በዘገባ የሚዳስሷቸውን አይነኬ ሀገራዊ ኹነቶች፣ ዛሬ በሀገር ውስጥ የሚገኙ የመንግሥትም ሆኑ የግል የኤሌክትሮኒክስ እና የኅትመት የሚዲያ አውታሮች ሁሉ ‹‹ጎመን በጤና›› የሚለውን ብሂላቸውን ለቀቅ እያደረጉ ሀገራዊ ኹነቶችን ለዘገባ የሚደፍሩት እየሆነ በመምጣቱ፤ በአድማጭ ተመልካች ዘንድ ፍላጎትና አቅርቦቱ በመሠረታዊ ደረጃ ሁሉም ጋር ተቀራራቢ ግልጋሎት እየሆነ መጥቷልና፡፡እነኾ! ኢሳት ወደ ሀገሩ፣ ወደ እናት- ምድሩ፣ ወደ ናፈቀው የእናቱ ጠረን ተመለሰ፡፡ሰላም!!!

# “ኢሳት የኢትዮጵያውያን ስቃይ በተከሰተበት ሁሉ ቀድሞ ይደርሳል”

## ጋዜጠኛ መሳይ መኮንን

**ግዮን፡- ከሀገር ከወጣህ ምን ያህል ጊዜ ሆነህ? በምን ምክንያት ወጣህ?**

መሳይ፡-ከሀገር የወጣሁት የ2002 የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምርጫ ከመደረጉ ከወራት በፊት ነው፡፡ ወደ አስር ዓመት ተጠግቼአለሁ፡፡ የወጣሁት ለጀርመን ድምጽ ራዲዮ የኢንተርንሺፕ እድል አግኝቼ ነው፡፡ በወቅቱ ከምኖርበት ሀዋሳ የዶቼቬሌ ዘጋቢ ለመሆን አስፈለጊውን ሂደት ጨርሼ ነበር፡፡ ሆኖም የህወሀት አገዛዝ የስራ ፈቃድ ሊሰጠኝ ባለመቻሉ የሬዲዮ ጣቢያው የአማርኛ አገልግሎት ሃላፊ ወደ ጀርመን በማቅናት ለተወሰነ ጊዜ እንድቆይ እድሉን ሰጠኝ፡፡ ወደቦን አመራሁ፡፡ በዚያም የጣቢያው ባልደረባ ሆኜ ለዓመት ከመንፈቅ ያህል አገለገልኩ፡፡

**ግዮን፡-በሀገር ቤት እያለህ ምን ትሰራ ነበር?**

መሳይ፡- የጋዜጠኝነት ፍቅሩ ከልጅነት ጀምሮ ውስጤ አብሮኝ የነበረ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ በሀዋሳ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚኒሚዲያ አዘጋጅ ነበርኩ፡፡ ወደ ዩኒቨርሲቲ ስገባ የቋንቋ ተማሪ ሆኜ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ሳምንታዊ የመዝናኛ ዝግጅት ላይ መጣጥፎችን አቀርብ ነበር፡፡ በተለይም የቅዳሜ ከሰዓት የመዝናኛ ፕሮግራም ላይ ለሶስት ዓመታት የተለያዩ ጽሁፎችን በመላክ በቋሚነት እሳተፍ ነበር፡፡ በተለይም እውነተኛ የፍቅር ታሪኮችን በመተርጎም፡ ዓለም ዓቀፍ ሳይንሳዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ መጣጥፎችን በማዘጋጀት ጥሩ ተቀባይነትን ያገኘሁበት ጊዜ ነበረኝ፡፡ የእኔን ጽሁፎች ጋዜጠኛ መሳይ ዓለማየሁ በጥሩ ሁኔታ በማቀናበር ለአድማጮች ተወዳጅ የሆነ የቅዳሜ መዝናኛ ቆይታ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ ከዩኒቨርሲቲ ከወጣሁ በኋላ ከኢትዮጵያ የሰላም አስከባሪ ሰራዊት ጋር ወደ ቡሩንዲ በአስተርጓሚነት ተጉዤ ነበር፡፡ የቡሩንዲ ቆይታዬ ከዋናው ስራዬ ይልቅ ለጋዜጠኝነት ግብዓት የሆኑ በርካታ ታሪኮችን እንድሰበስብ ያደረገ መልካም ጊዜ ነበር፡፡ ወደ ሀገር ቤት ስመለስም በቀጥታ ወደ ትውልድ ከተማዬ ሀዋሳ ገባሁ፡፡ የአጋጣሚ ሆኖ የደቡብ ኤፍ ኤም እየተቋቋመ ስለነበር ከቡሩንዲ እንደተመለስኩ በደቡብ ኤፍ ኤም 100.9 ተቀጠርኩኝ፡፡ ጣቢያውን በመመስረትም ሆነ ተደማጭ እንዲሆን በማድረግ ከሌሎች ባልደረቦች ጋር ውጤታማ ስራ የሰራሁበት ነው፡፡ በደቡብ ኤፍ ኤም በነበረኝ የአምስት ዓመታት ቆይታ የኢትዮጵያ ትንሳዔ የተሰኘው ፕሮግራሜ ምንጊዜም በአድማጩ እንድታወስ ያደረገኝ ነው ማለት እችላለሁ፡፡ ኢትዮጵያዊነትን የሚያጎላው ይህ ፕሮግራም ከጣቢያው እንድሰናበት ያደረገኝም ነበር፡፡ ለሁለት ዓመት ተኩል የዘለቀው ይህ ፕሮግራም በመንግስት ዘንድ በጥሩ የታየ ባለመሆኑ ስያሜውንና ይዘቱን እንዲቀይር የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጥር ስራዬን በገዛ ፈቃዴ ለቅቄ ወጥቼአለሁ፡፡ ከዚያም ከሀገር እስክወጣ ድረስ የራሴን የማስታወቂያ ድርጅት በመክፈት ከተለያዩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ዘጋቢ ፊልሞችንና የሬዲዮ ፕሮግራሞችን እየሰራሁ ቆይቼአለሁ፡፡



**ግዮን፡ ወደ ኢሳት ለመግባት ምን አነሳሳህ?መቼ ገባህ?**

መሣይ፡-ኢሳት የተቋቋመው እኔ በጀርመን ድምጽ ሬዲዮ እያለሁ ነበር፡፡ ምንም እንኳን የምሰራለት የጀርመን ድምጽ ሬዲዮ በሀብታሙ ሀገር ጀርመን መንግስት የሚደገፍ፡ በዚህም ከግል ህይወት አንጻር ጥሩ ተስፋ እንዲኖረኝ የሚያስችለኝ ተቋም ቢሆንም በሙያው አንጻር የምረካበት አልነበረም፡፡ ኢትዮጵያ አደጋ ላይ ናት፡፡ ኢትዮጵያ መዳን ካለባት በእኔ ሙያ ማድረግ የሚገባኝን ማድረግ እንዳለብኝ ይሰማኛል፡፡ ለእኔ በዚህ ዘመን ጋዜጠኝነት ሀገርን የምናድንበት አንዱ የሙያ ዘርፍ አድርጌ ወስጄዋለሁ፡፡ ህዝባችን በመረጃ ጨለማ ተጋርዷል፡፡ የህወሀት አገዛዝ በ21ኛው ክፍለዘመን ኢትዮጵያውያንን ነጻና ገለልተኛ መረጃ እንዳያገኙ በማድረግ የአፈና አገዛዙን ያጠበቀበት ወቅት ነበር፡፡ የሀገር ውስጥ ሚዲያዎችን በመዳፉ ውስጥ ስለነበሩ የሚተላለፉ መረጃዎችን ይቆጣጠራል፡፡ በልኩና በቁመቱ የተሰፋ ፕሮግራሞችንና ዜናዎችን ብቻ ለህዝብ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡ በውጭ የሚገኙትና ወደ ሀገር ቤት የሚተላለፉት ሚዲያዎችም በቂ የሆነ ነገር ማቅረብ አልቻሉም፡፡ የሚያስተዳድሯቸው ሀገራትን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ጠብቀው የሚያሰራጩ በመሆናቸው በመረጃ ረሃብ ለሚሰቃየው የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙም አልጠቀሙትም የሚል እምነት ነበረኝ፡፡ ኢሳት ሲቋቋም ይህንን ክፍተት እንደሚደፍን ከጅማሬው መረዳት ቻልኩኝ፡፡ ኢሳት ከመነሻው እስከ መዝጊያው የኢትዮጵያን ጉዳዮች ብቻ የሚያነሳ የመጀመሪያው ተቋም መሆኑን ስረዳ እረፍት አጣሁ፡፡ የእኔ ቤት ኢሳት ነው የሚል ስሜት ውስጤ ገባ፡፡ በሙያዬ የኢትዮጵያ ህዝብ ለነጻነት የሚያደርገውን ትግል የማግዘው ጀርመን ድምጽ ሬዲዮ ውስጥ ሆኜ አይደለም፡፡ አሜሪካን ሬዲዮም ያን እድል እንደማይሰጠኝ ይታወቃል፡፡ በኢሳት ግን ይቻላል፡፡ እናም ልቤ ሸፈተ፡፡ ኢሳት ለመግባት ማሰብ ጀመርኩ፡፡ እዚያው ጀርመን ሬዲዮ እያለሁ ከህዝብ ተልከው የሚገፉ መረጃዎችን አምስተርዳም ለሚገኘው ኢሳት አስተላልፍ ነበር፡፡ ከፋሲል የኔዓለም ጋር ጥሩ ግንኙነት በመፍጠር መረጃዎችን በማቃበል የኢሳት መንገዴን ጀመርኩ፡፡

ያን ጊዜ አቶ ነአምን ዘለቀ የአሜሪካው የኢሳት ቅርንጫፍ ሃላፊ ነበር፡፡ ከእሱ ጋር መጻጻፍ ጀመርኩ፡፡ ለኢሳት ማገልገል እንደምፈልግ ነገርኩት፡፡ የእሱ ስጋት የነበረው የጀርመን ድምጽ ሬዲዮ ባልድረባ ወደ ኢሳት ሲመጣ በገንዘብ ክፉኛ ይጎዳል የሚል ነበር፡፡ ኢሳት ጥሩ ክፍያ ለመክፈል የሚያስችል አቅም አልነበረውም፡፡ በእርግጥ አሁንም አለው ለማለት አይደለም፡፡ እናም የነአምንንን ስጋት ቀረፍኩለት፡፡ የሳንቲሙን ጉዳይ ተወው አልኩት፡፡ ለሀገር ከሚሰሩ ጀግኖች አጠገብ ሆኜ መስራት ለእኔ ከደምወዝም በላይ እንደሆነ አስረግጬ ነገርኩት፡፡ ታማኝ በየነ፡ ሲሳይ አጌና፡ አበበ ገላው፡ መኩሪያ ገብረሚካዔል፡ ብሩክ ይባስ የሚገኙበትን የአሜሪካንን የኢሳት ስቱዲዮ መቀላቀል አለብኝ ብዬ ጻፍኩለት፡፡ ደስተኛ ነበር፡፡ ወዲያውኑ የግብዣ ወረቀት ላከልኝ፡፡ የጀርመን ሬዲዮ ባልደረባ በመሆኔ ቪዛ ለማግኘት ▶

አልተቸገርኩም:: ኢሳት በተቋቋመ በዓመቱ ወደ አሜሪካ ሄጄ ተቀላቀልኩት::

በወቅቱ ኢሳት በቴሌቪዥን ብቻ የሚሰራጭ ነበር:: ከአበበ ገላው ጋር በመሆን ኢሳት ሬዲዮን ጀመርኩት:: ተወዳጅ ሬዲዮ ሆነ:: እኔም ፍጹም ደስተኛ ካደረገኝ፡ ለሀገር እንቅልፍ አጥተው ከሚያድሩ ሰዎች ጋር ታሪክ ከሚሰራበት ቤት ውስጥ በመገኘቴ ኩራት እየተሰማኝ መስራት ቀጠልኩኝ:: ይህው ዘጠነኛ ዓመት ላይ ደረስን::

**ግዮን፡-ኢሳት የገባኸው ጋዜጠኛ ስለሆንክ ነው ወይስ የራስህ የፓለቲካ አቋም አለህ?አቋምህ ምን ነበር?**

*መሳይ፡-እኔ ፖለቲከኛ አይደለሁም:: የምቃወመውም ሆነ የምደግፈው የፖለቲካ ድርጅት የለም:: ይህ ግን ህወሀትን አይመለከትም:: ህወሀት የፖለቲካ ድርጅት አልነበረም:: የፖለቲካ ድርጅት ሀሳብ ሊኖረው ይገባል:: ሀሳብ የሌለው፡ በድን የሆነ ድርጅት የፖለቲካ ቁመና አለኝ ቢል የሚቀበለው አይኖርም:: እናም የህወሀት ተቃዋሚ መሆን ከፖለቲካ አቋም ጋር መያያዝ የለበትም:: ህወሀት ኢትዮጵያን ሊያጠፋ የተፈጠረ እኩይ ድርጅት ነው:: አፈጣጠሩ ጸረ ኢትዮጵያ ነው:: ደደቢት ላይ ሲጸነስ የኢትዮጵያን አንድነት አደጋ ውስጥ የሚጥል አቋም በመቅረጽ ነው:: ህወሀትን ስለተቃወምኩ የፖለቲካ አቋም አለው ሊባል አይገባም::*

እናም የፖለቲካ አቋም ባይኖረኝም ህወሀትን ግን እቃወመው ነበር:: ህወሀትን በማጋለጥ ለውድቀቱ ጥሩ የትግል ቤት ለእኔ ከኢሳት ሌላ ትክክለኛ ምርጫ አልነበረም::

**ግዮን፡- ኢሳት ከገባህ በኋላ በጣም ያስደሰተህ ምን ስራ ሰርተሃል?**

*መሳይ፡-የቱን ነግሬህ የትኛውን እንደምተው አላውቅም:: ባለፉት 8 ዓመታት ኢሳት የኢትዮጵያ የፖለቲካ፡ የኢኮኖሚ፡ የማህበራዊና ሁለንተናዊ እንቅስቃሴዎች ላይ አሻራውን ያሳረፈ ተቋም ነው:: በኢሳት ውስጥ በርካታ ለውጥ የፈጠሩ ዘገባዎችን፡ ፕሮግራሞችን ሰርተናል:: ለነጻነት ራሱን ካቃጠለው የዳውሮው መምህር የኔሰው ገብሬ ጀምሮ እስቅርብ ጊዜው የሶማሌ ክልል ቀውስ የኢሳት ሚና ቀላል የሚባል አይደለም:: የኔሰው ገብሬ መስዋዕትነቱን ለማርከስ በጥፍሩ ቆሞ የተነሳውን የህወሀትን አገዛዝ አሳፍረን የማይደበዝዝ ስም በታሪክ እንዲኖረው በማድረግ የኢሳት ሚና ቀላል የሚባል አልነበረም::*

ኢሳት የኢትዮጵያውያን ስቃይ በተከሰተበት ቦታ ሁሉ ቀድሞ ይደርሳል:: ብሄራዊ ውርደት ሲገጥመን የኢሳት ድምጽ ጎልቶ ይሰማል:: ከሰሜን ዋልታ እስከ ደቡብ የመሬት ንጣፍ ድረስ ኢሳት ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሁሉ አይንና ጆሮአቸው ሆኖ ቀድሞ ይደርሳል:: ኢሳት ብሄር የለውም:: ኢሳት ብሄር ካለውም ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነው:: የዘር የቀለም የትኛውም ልዩነት ኢሳት ውስጥ ቦታ የለውም:: ኢትዮጵያዊ በደረሰበት የመሬት ቁራሽ ቦታ ኢሳት ይኖራል::

የአቶ መለስ ዜናዊን ህለፈት ይፋ ያደረኩት እኔ ነኝ:: የአቡነ ጳውሎስንም ሞት ለኢትዮጵያ ህዝብ ቀድሜ የነገርኩት እኔ ነኝ:: ከቤተመንግስትና ከቤተክህነት መሪዎቹ ተከታትለው ይህቺን ምድር በሞት ሲለዩ ዜናውን በቀዳሚነት የዘገበው ኢሳት ነው:: በኢሳት ውስጥ ደግሞ ሁለቱንም ሁነኛ ክስተቶች የዘገብኩት እኔው ነበርኩ:: እነዚህ ሁለት ወሳኝ ክስተቶች ለኢሳት ታዓማኒነት ትልቁን ስፍራ ይዘዋል:: በወቅቱ የአቶ መለስ ዜናዊን መሞት በብቸኝነት የዘገብነውና በዜናውም አቋም ይዘን ሳንቀይር የዘለቅነው እኛው ነበርን:: ከአቶ በረከት ስምዖን ጀምሮ በርካታ የሀገር ውስጥ ጋዜጦችና ሚዲያዎች የአቶ መለስ ዜናዊን ህልፈት ሲደብቁና አንዳንዶችም በህይወት እንዳሉ ሲዘግቡ ኢሳት ግን በዜናው ላይ አቋሙን ሳይቀይር ከአንድ ወር በላይ ቆይቶ የኢትዮጵያ ቴሊቪዥን እውነታውን ሲያፍረጠርጠው ሁሉ ነገር ለይቶለታል:: የኢሳትም ተቀባይነት የጨመረው ከአቶ መለስ ዜናዊ ሞት ዘገባ በኋላ ነበር::

ከዚያን በኋላም በርካታ ውጤታማ ስራዎችን ሰርተናል:: የጉራፈርዳና የቤንሻንጉል ጉምዝ መፈናቀሎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ትኩረት እንዲሰጠው ከማድረግ ባለፈ፡ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት መፍትሄ እንዲፈለግለት በማድረግ የአንበሳውን ድርሻ የያዘው ኢሳት ነበር:: በሳዑዲ አረቢያ ኢትዮጵያውያን ብሄራዊ ውርደት ሲገጥመን ሁኔታውን ቀድሞ ከማሳወቅ በተጨማሪ ኢትዮጵያውያን ከዳር እስከዳር ተነቃንቀው ለኢትዮጵያውያን የሚበጅ ተግባር እንዲያከናውኑ ኢሳት የሚቻለውን አድርጓል::በደቡብ አፍሪካ ኢትዮጵያውያን በዜኖፎቢያ ጥቃት ሲደርስባቸው ኢሳት አብሮአቸው ነበር:: የአኝዋኮችን የጅምላ ጭፍጨፋ ትኩረት እንዲሰጠው የኢሳት ሚና ትልቅ ነበር:: ከዚያም ባለፈ አኝዋኮች ሁለተኛ ዜጋ አለመሆናቸውንና ከማንም በላይ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ያላቸው መሆኑን በይፋ መግለጽ የጀመሩትም በኢሳት ባልደረቦች ጥረት ነው:: በሶማሌም ሆነ በደቡብ ኢትዮጵያ ኢሳት የታፈኑ ድምጾችን እንዲሰሙ አድርጓል:: የቅርብ ጊዜውን የሶማሌ ክልል አዲስ መስተዳድር ከተቃጣበት መፈንቅለ መንግስት የታደገውም ኢሳት ነው::

**ግዮን፡-ወደ ኤርትራ ስትሄድ በበረሃ ከነበሩት ወታደሮች ጋራ የነበረህ ቆይታ ምን ይመስላል?**

*መሳይ፡- ወደ ኤርትራ ያደረኩት ጉዞ ለሶስት ዓላማዎች ነበር:: አንደኛውና ዋናው የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በህወሀት ደህንነቶች ከየመን ታፍኖ መወሰድ የፈጠረብኝ እልህ ነው:: ቢያንስ አቶ አንዳርጋቸው በበረሃ የነበረውን ቆይታ እዚያው ካሉ የትግል አጋሮቹ ለመስማትና ዱካውን በአካል ተገኝቶ ለማየት ፈልጌ ነበር:: ሁለተኛው በህዝቡ የሚነሳ አንድ ጥያቄ የእኔም ጥያቄ ስለነበር ለእሱ ምላሽ ለማግኘት ነው:: ይኸውም በኤርትራ እውን የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴ አለ ወይ? በረሃ ወርደናል በሚሉ ሃይሎች የሚነገርው እውነት ነው ወይ የሚለው ጥያቄ በብዛት ይነሳ ነበር:: እኔ ውስጥም ይህ ጥያቄ እረፍት ይነሳኝ ነበር:: ምላሽ መገኘት አለበት የሚል እምነት ነበረኝ:: ሶስተኛው የኤርትራ መንግስት ባለስልጣናትን ቃለመጠይቅ ማድረግ ነው:: ስለኢትዮጵያና ኤርትራ ግንኙነት ምን ያስባሉ? ለምን የኢትዮጵያን ሃይሎች መርዳት ፈለጉ? የወደፊቱ የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት በየት አቅጣጫ እንዲጓዝ እቅድ አላቸው? የሚሉና መሰል ጥያቄዎችን በማቅረብ ምላሽ ለማግኘት ነበር::*

ሶስቱንም አላማዎቼን ከሞላ ጎደል አሳክቼ የተመለስኩበት ቆይታ ነበር:: በአስመራ ለተወሰኑ ቀናት ከቆየን በኋላ በቀጥታ ያመራነው ወደ በረሃ ነው:: የኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይሎች ከሚገኙበት ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፖች ጉብኝት አድርጌአለሁ:: በእርግጥም ስለኢትዮጵያ ነጻነት ውድ ህይወቱን ለመስጠት ከቀበሮ ጉድጓድ ውሎ የሚያድር የኢትዮጵያ ልጅ እንዳለ አረጋግጬአለሁ:: የመሳሪያ ትግል ለማድረግ ወስነው በረሃ የገቡ ሃይሎች እግር አውጥቶ የሚራመድ ወታደራዊ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን በቦታው ተገኝቼ አይቼአለሁ:: ከአውሮፓና ከአሜሪካ የተሻለ ኑሮአቸውን ትተው በበረሃ ለኢትዮጵያ ነጻነት የገረጡና የከሰሉ ውድ ወንድሞቼንና እህቶቼን ስመለከት የእኔ ድርሻ ኮስሶ አገኘሁት:: ለእኔም ለእነሱም ኢትዮጵያ የጋራችን ናት:: ለእነሱ ብቻ በእዳ ተላልፋ የተሰጠች አይደለችም:: ግን የአንዳንዶቹን መስዋዕትነትና ቁርጠኝነት ስመለከት እውን ኢትዮጵያ ለሁላችንም እኩል ነች? የሚል ጥያቄ ጭሮብኛል:: የኤርትራው በረሃ ቆይታ ትዕግስትን የተማርኩበት፡ ለሀገር የሚከፈል ዋጋ ወሰን የሌለው መሆኑን የተረዳሁበት፡ ከምንም በላይ ኢትዮጵያ ዛሬም ሞቶ የሚያድናት ውድ ልጅ እንዳላት ያረጋገጥኩበት ነበር ማለት ይቻላል::

**ግዮን፡-በኢትዮጵያ ውስጥ ስለተፈጠሩ ጉዳዮች ዜና ለመሥራት፤መረጃ ለማግኘት ምንያህል አድካሚ ነው?ተስፋ የመቆረጥ ነገር ተፈጥሮብህ ያውቃል?**

*መሳይ፡- ስራችን አድካሚ ነበር:: ተስፋ የቆረጥንበት ጊዜ እንደነበረ አስታውሳለሁ:: በተለይ መረጃ ለማግኘት እጅግ የማይቻል የሆነብን ወቅቶች ብዙ ናቸው:: የህወሀት አገዛዝ አፈና የእኛን መረጃ የማግኘት እድል ጠባብ አድርጎታል:: አንዳንድ ቆራጥ የሆኑ፡ የሚመጣ አደጋም ካለ ለመጋፈጥ የወሰኑ ኢትዮጵያውያን በየቦታው መኖራቸው ጨርሶ የመረጃ ድርቅ እንዳይመታን አድርገዋል:: እነዚህ በከፋው ጊዜ ከጎናችን ለመሆን የቆረጥ፡ በስም እኛም የማናውቃቸው ኢትዮጵያውያን የኢሳት የምንጊዜም ባለውለታ ናቸው:: እነሱ ባይኖሩ ኢሳት በዚህ ደረጃ ተቀባይኖት ኖሮት አይዘልቅም ነበር::*

በእርግጥ የእነዚህ ጥቂቶች አስተዋጽኦ በቂ ነበረ ማለት አይቻልም:: ከምንም የሚሻል ነው ካላልን በስተቀር እንደአንድ ሚዲያ በቂ መረጃ እያገኘን ሰርተናል ለማለት አያስደፍርም:: ለኢሳት መረጃ ለመስጠት ይቅርና ኢሳትን ለማየት አስፈሪ የሆነበትን ዘመን ነው የተሻገርነው:: ብዙውን ጊዜ መረጃም ሆነ ቃለመጠይቅ የሚሰጡንን ሰዎች ስም እንቀይራለን:: ድምጻቸውን እንለውጣለን:: የሚገርምህ መረጃና ቃለመጠይቅ ለኢሳት ለመስጠት የሚሸሹት በሀገር ቤት ያሉ ብቻ አይደሉም:: በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም ኢሳት ላይ ለመቅረብ አይፈልጉም ነበር:: ታማኝ በየነ ለመዝናኛ ዝግጅቱ አርቲስቶችን ለማግኘት የገጠመውን እጅግ አሰልቺ ፈተና በቅርበት አውቀዋለሁ:: ከፍርሃት ቆፈን ያልተላቀቁ አሁንም ይሸሹናል:: ከባድ ነው:: የህወሀት የግፍ አገዛዝ የማይለቅ ፍርሃት ውስጣቸው ያሰረጸባቸው እንዳሉ ትረዳለህ:: ለማንኛውም በእንደዚህ የአፈና ጊዜ ኢሳት በብርቱ ተፈትኗል:: የእኔ፡ የፋሲል የኔዓለም፡ የካሳሁን ይልማ ስሞች በፍርድ ቤት ክሶች ላይ እንደልብ ታገኛቸዋለህ:: በሽብርተኝነት የሚከሰሱ ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች መረጃና ቃለመይጠይቅ ለኢሳት ሰጥታችኋል ተብለው ሲከሰሱ በአባሪነት የሚያያዘው ከእኛ ጋር ያደረጓቸው ቃለመጠይቆች ነበሩ:: ይህ ሁኔታ በተወሰነ ደረጃ መረጃና ቃለመጠይቅ የማግኘት እድላችንን አጥቦታል::

የህወሀት አፈና ከአድማስ ወዲህም መጥቶ በኢንተርኔት ስለላ ተደርጎብናል:: ህወሀት በብዙ ሚሊዮን ብሮችን ከፍሎ የእኔን ጨምሮ የተወሰኑ የኢሳት ባልደረቦችን ኮምፒውተሮች ጠልፎ መረጃ ለመውሰድ ሙከራ አድርጓል:: በዚህ ምክንያት በአሜሪካ ትልቁ ጋዜጣ በሆነው ዋሽንግተን ፖስት ላይ የፊት ገጽ የሆነ ዜና ተሰርቶ የህወሀት ሴራ ተጋልጧል:: በእኔ ኮምፒውተር ላይ ከኢትዮጵያ መረጃ የሚሰጡን የበርካታ ሰዎች የስልክ ቁጥሮችና የኢሜይል አድራሻዎች ይገኛሉ:: ሲትዝን ላብ የተሰኘው ጸረ ጠለፋ ተቋም በቶሎ ደርሶ የእኔን ኮምፒውተር ከስራ ውጭ ባያደርገው ኖሮ የሀገር ቤት መረጃ ሰጪዎቻችን ህይወት

አደጋ ላይ ይወድቅ ነበር፡፡ እናም በኢሳት ያለፉ 8 ዓመታት በጽኑ የተፈተንበት ጉዳይ ቢኖር ይሄው ነው፡፡

**ግዮን፡- ብዙ ጊዜ ሰበር ዜናዎችን የማንበብ እድሎች ያጋጥሙሃል፤አንተ ፈልገህ ነው ወይስ ተረኛ ስለምትሆን?**

መሳይ፡- የአጋጣሚ ጉዳይ ነው ብል የሚቀል ይመስለኛል፡፡ ኢሳት ውስጥ በቋሚነት የምንሰራ የዜና ሰዎች ጥቂት ነን፡፡አብዛኞቹ በሳምንት ውስጥ የተወሰኑ ቀናት የሚሰሩ ናቸው፡፡ እኔ በሳምንት ሰባት ቀናት 24 ሰዓት ራሴን አዘጋጅቼአለሁ፡፡ ሌሊት ሰበር ዜና ቢመጣ ከእንቅልፌ ተነስቼ ወደ ቢሮ በመሄድ ራሴው ቪዲዮ ቀርጬ ሰበር ዜናውን የሰራሁባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው፡፡ ምን ለማለት ነው ባለሙሉ ጊዜ የኢሳት ሰራተኛ መሆኔና በየትኛውም ሰዓት ስራውን ለምስራት ዝግጁ መሆኔ በተደጋጋሚ በሰበር ዜና እንድቀርብ አድርጎኛል፡፡ እኔም ሰበር ዜናውን የመስራት ፍላጎቱ በሚገባ አለኝ፡፡ ትግል ውስጥ እንዳለሁ ስለማስብ ያ ዜና ለወዳጅና ለባለጋራ የሚፈጥረውን ስሜት በሚገባ እረዳዋለሁ፡፡ የነጻነት ታጋዩን ሞራል ሲገነባ፡ የጸረ ዲሞክራሲ ሃይሉን ደግሞ በፍርሃት ሲያርድ ይታውቀኛል፡፡ ምንም እንኳን በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ ብሆንም በተወሰነ ደረጃ ደርዙን ያለቀቀ ፕሮፖጋንዳም ያስፈልጋል፡፡ ለማንኛውም ሰበር ዜናዎቹ ላይ መብዛቴ የተለያዩ ምክንያቶች ይኖሩታል፡፡ አንዳንዶች ሰበር ዜናን "መሳይ ሾው" ሲሉም ሰምቼአለሁ፡፡

**ግዮን- ኢሳት በነበርክበት ጊዜ ፈታኝ የሆኑ ጉዳዮች የገጠሙህን እስቲ አጫውተኝ**

አንድ የኢሳት የገቢ ማስገኛ ዝግጅት ላይ ተገኝቼ የገጠመኝን ላካፍልህ፡፡ ለዝግጅቱ ሁሉም ይመጣል፡፡ ደጋፊውም ነቃፊውም አይቀሩም፡፡ ገንዘብ ሊሰጥ የሚመጣ፡ ተቃውሞውን ለማሰማት የሚታደም ሁሉም የሚሳተፍበት መድረክ ነው፡፡ እና ስለኢሳት የሚሰማችሁን ንገሩን ብለን መድረኩን ከፈትን፡፡ አንዱ ከዚያ ተነስቶ እናንተ ከኦነግ ጋር የምትሰሩ የኦሮሞ ጽንፈኞችን የምታበረታቱ ናችሁ ብሎ ወቀሰን፡፡ ሌላው ተነስቶ እናንተ የነፍጠኛ ሚዲያ ናችሁ፡ ከአማራ በቀር ኢትዮጵያዊ አይታያችህም ብሎ ተቀመጠ፡፡ እንዲሁ ሌላው ታዳሚ የኢህ አፓ ልሳን ሆናችሁ ሲል ይገልጸን ጀመር፡፡ አንደኛውም የደርግ ርዝራዦች ናችሁ በሚል ወረደብን፡፡ የሙስሊም ሚዲያ መሰላችሁ ያለንም ነበር፡፡ ሌላም ሌላም፡፡ መልሴ ምን እንደነበረ ታውቃለህ? "ይታያችሁ እኛ የሁላችሁም መሆናችንን እየነገራችሁን ነው፡፡ የሁላችሁም ድምጽ ከተሰማ ኢሳት የማንም ልሳን እንዳልሆነ እዚህቺው መድረክ ላይ ራሳችሁ አረጋገጣችሁ" ብዬ መልስኩላችው፡፡ ይሄው ነው፡፡ ይህ ሀቅ ነው፡፡ ኢሳት የማንም አይደለም፡፡

በግሌ ብዙ ስህተቶችን ሰርቼአለሁ፡፡ በተለይ አንድ ወቅት ላይ የትግራይን ህዝብ በተመለከተ ተገቢ ያልሆነ መልዕክት እንዲሰራጭ በማድረጌ የፈጠርኩት ስህተት መቼም የማልረሳው ነው፡፡ ሆን ብዬ የፈጠርኩት ግን አይደለም፡፡ በቅንነት የተፈጸመ ወዲያውኑ ከኢሳት ገጾች ላይ እንዲወርድ የተደረገ ስራ ነው፡፡ የትግራይ ወገኖቼ አሁን ድረስ በዚህ ጉዳይ ተቃውሞአቸውን ይገልጹልኛል፡፡ የምነግራቸው ግን ስህተቱ የተፈጸመው ፍጹም ታቅዶና ታስቦ እንዳልነበረ ነው፡፡ የትግራይ ወገንህን በዚያ መልኩ መግለጽ የለብህም፡፡ ብዙ የትግራይ ጓደኞች አሉኝ፡፡ ክፉና ደጉን ያሳለፍኩባቸው፡ ሰው መሆንን ትርጉም በሚገባ ያየሁባቸው የትግራይ ወንድምና እህቶች አሉኝ፡፡ በእነሱ ላይ መጥፎ ነገር ልመኝ የምችል ሰው አይደለሁም፡፡ የተፈጠረው ስህተት እኔነቴን አይገልጽም፡፡ እናም በዚህ አጋጣሚ ይቅርታ እጠይቃለሁ፡፡ በተረፈ ሌሎች ፈታኝ ነገሮች ገጥመውኛል፡፡ ግን ኢሳት በጽናት በተጓዘባቸው ዓመታት ሁሉ አብሬው ስላለሁ የድካሙም የብርታቱም ተቋዳሽ ነኝ ማለት እችላለሁ፡፡

**ግዮን፡-ኤርትራ በነበርክበት ጊዜ ከፕሬዝዳንት ኢሳያይስ የነበራችሁ ቆይታ ምን ይመስል ነበር?**

መሳይ፡- ስለኤርትራው ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየ ስሜት አልነበረኝም፡፡ በደርግ ዘመን ልጅ ስለነበርን የፖለቲካውን ነገር አላውቀውም፡፡ በህወሀት ጊዜ ግን በተለይ ከኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወዲህ ስለአቶ ኢሳያስ የሚነገርን ጥሩ ስላልሆነ ስለእሳቸው የነበረኝ ስሜት አሉታዊ ነበር፡፡ ጭራቅ አድርገን እንድንስላቸው ህወሀት የሚችለውን አድርጓል፡፡ በእርግጥ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ መለያየት በፊት መሪነት ስማቸው የሚነሱ እሳቸው መሆናቸውን ባውቅም ከአንድ ወገን የሚለቀቀውን ፕሮፖጋንድ ብቻ ይዞ መዝለቁ አልታየኝም፡፡ ስለእሳቸው የተለያዩ ሰዎች ጽፈዋል፡፡ የሜጀር ጄነራል ደምሴ ቡልቶ ልጅ ዶ/ር ደረጀ ደምሴ "አባቴ ያቺን ሰዓት" በተሰኘው መጽሀፉ አንድ ቦታ ላይ ስለአቶ ኢሳያስ የተጻፈው ምስክርነት አስገርሞኛል፡፡ እነሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ የጻፏቸው መጣጥፎችና መጽሀፍት፡ ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም አቶ መለስ ዜናዊንና አቶ ኢሳያስ አፈወርቂን አንጻጽረው ያቀረቡት ንግግር የህውሀትን ፕሮፖጋንዳ አላምጬ እንዳልውጠው አድርጎኛል፡፡ ስብሃት ነጋ በተደጋጋሚ "የኤርትራን ነጻነት ሻዕቢያዎች አደጋ ላይ ለመጣል የሞከሩባቸውን አጋጣሚዎች ያዳነው እኛ ነን" የሚል አሳፋሪ ቃለመጠይ ሲሰጡ ስሰማ ስለአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ሌላ ማንነት እንዳለ መረዳት ቻልኩኝ፡፡

አስመራ በነበረን ቆይታ በተለያዩ ሶስት አጋጣሚዎች ተገናኝተናል፡፡ የመጨረሻው አጋጣሚ የቃለመጠይቅ በመሆኑ ሰፊ ጊዜ ወስደን አውርተናል፡፡ አቶ ኢሳያስ ከጠበኳቸው በላይ ሆነው ነው ያገኘኋቸው፡፡ በቅድሚያ የሚፈጠርብህ ስሜት እውን እኚህ ሰው የሀገር መሪ ናቸውን? ትላለህ፡፡ አለባበሳቸው፡ የአጃቢ ጋጋታ አለመኖሩ፡ የጀበና ቡና በባቄላ አሹቅ አብረውህ እየዘገኑ ሲበሉና ሲጠጡ ስታይ ትደነቃለህ፡፡ ፕሬዝዳንት ኢሳያስ ቀለል ያሉ፡ እንደጓደኛ የሚያቀርቡህ ናቸው፡፡ አማርኛ ብዙም ባይችሉ ለቀላል ግንኙነት የሚከብዳቸው አይመስለኝም፡፡

አቶ ኢሳያስ ስለኢትዮጵያ ያላቸው አመለካከት ስለእሳቸው ስንሰማ የነበረውን እንድንፈትሸው የሚያደርግ ነው፡፡ ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም "ከአቶ መለስ ኢትዮጵያዊነት የአቶ ኢሳያስ ይበልጥብኛል" ሲሉ ምክንያት ነበራቸው ለካ?! እኔ አቶ መለስ ዜናዊ አንድ ቀንም ለጨረፍታ መሪዬ ናቸው ብዬ አስቤም አላውቅም፡፡ እንዲሁ የአንድ አካባቢ ተወካይ እንደሆኑ ነው ይህቺን ምድር የተሰናበቷት፡፡ አቶ ኢሳያስ ስለኢትዮጵያ መልካም ያስባሉ፡፡ ስለእሳቸው የሚነገረው በማስረጃ የተደገፈ እንዳልሆነ ይገልጻሉ፡፡ እንደውም የህወሀት መሪዎች የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፈው በሚሰጡበት ወቅት እሳቸው ጥብቅና ቆመው ስለኢትዮጵያ ይከራከሩ እንደነበረ አንድን አጋጣሚ አስታውሰው ነግረውናል፡፡ ለማንኛውም ፕሬዝዳንት ኢሳያስ እንደሚባለው ዓይነት ጸረ ኢትዮጵያ ሆነው አላገኘኋቸውም፡፡

**ግዮን፡- ኢሳት የተነሳበትን አላማ ግብ መቷል ትላለህ?በቀጣይ የኢሳት ጉዞ ምን ይመስላል?**

መሳይ፡- ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ኢሳት የተነሳለትን ግብ በግማሽ መንገድ አሳክቷል፡፡ ስለፍትህ ጮህናል፡፡ ፍትህ ባይረጋገጥም ፍትህን ለማስከበር ቃል የገባ መንግስት አራት ኪሎ ገብቷል፡፡ ስለዲሞክራሲ ታግለናል፡፡ ዲሞክራሲ ባይሰፍንም በሂደት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት የሚያስችል መስመር ላይ የቆመ ስርዓት ስልጣን ይዟል፡፡ ስለኢትዮጵያ ቀን ከሌሊት ሰብከናል፡፡ ኢትዮጵያዊነትን ያነገሰ፡ ኢትዮጵያውያንን የሚያከብር መሪ ቦታውን ይዟል፡፡ ጅምሩ ጥሩ ነው፡፡ ቢያንስ አንድ እርምጃ ወደፊት ተጉዘናል፡፡ ይበልጥ ስራ የሚጠብቀን አሁን ነው፡፡ የፍትህ፡ የዲሞክራሲና የእኩልነት ጠንቅ የሆነው የህወሀት አገዛዝ ማዕከላዊ መንግስቱን ተነጥቋል፡፡ ኢትዮጵያን ከአደጋ የታደጋት የዶ/ር አብይ መንግስት የማይቋረጥ ህዝባዊ ድጋፍ ከተቸረው ኢትዮጵያችንን ለመለወጥ ጥሩ መንገድ የጀመርን ይመስለኛል፡፡

ኢሳትን በተመለከተ አዲስ ምዕራፍ ጀምረናል፡፡ እስከአሁን የነጻ አውጪ ሚዲያ ዓይነት ባህሪ ተላብሰን ዘልቀናል፡፡ ከጋዜጠኝነቱ ይልቅ የመብት ተሟጋችነቱ ላይ ያደላ የሚዲያ ስራ ስንሰራ ቆይተናል፡፡ አሁን በነበረን መንገድ የምንቀጥል አይመስለኝም፡፡ አሁን እንዲወድቅ የምንታገለው ስርዓት ሳይሆን እንዲስተካከል አብረን የምንሰራው መንግስት ነው ኢትዮጵያን የሚመራው፡፡ ስራችንም ኢትዮጵያን መታደግ እስከሆነ ድረስ አሁን የተጀመረውን መልካም አጋጣሚ ታሳቢ ያደረገ የሚዲያ ሚና ሊኖረን ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡ ኢትዮጵያ ገብተናል፡፡ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ችግሩንም ደስታውንም አብረን አጠገቡ ሆነን እየተጋራን ስራችንን ይበልጥ አጠናክረን እንቀጥላለን፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

**ግዮን፡ ወደ ሀገር መምጣት ስትወስን ምን ስሜት ተሰማህ?**

መሳይ፡- የህውሀት አገዛዝ እየተዳከመ መምጣቱን ብረዳም በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የአራት ኪሎን ቤተመንግስት ይነጠቃል ብዬ አልጠበኩም፡፡ በፍጹም፡፡ ከአንድ ዓመት በፊት የነበረኝ ስሜት ብትጠይቀኝ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ እሄዳለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም፡፡ ሀገሬ ብትናፍቀኝም በህወሀት አገዛዝ የተነሳ ላያት ሳልችል መቆየቴ ያንገበግበኛል፡፡ የመስዋዕትነቱ አንዱ መገለጫም ይሄው ነው፡፡ ሀገርህን መነጠቅህ፡፡ ኤርትራ የሄድኩ ጊዜ በአጭር ርቀት ሁመራን ያየሁ ጊዜ ሆዴ ተረብሿል፡፡ ህወሀትን ይበልጥ የረገምኩትም ያን ጊዜ ነው፡፡ ከኡምናህጅር ሆኜ የሁመራን ማርያም ቤተክርስቲያንን ስመለከት የህወሀት ጭካኔ ጥርሱን አግጦ ታየኝና ረገምኩት "እድሜህ ይጠር"!

ያልተጠበቀው ሆኗል፡፡ በአጭር ጊዜ ይታያል ያላልኩት ታይቷል፡፡ እነበረከት ስምዖን እስር ቤት ገብተው፡ እነዚያ የህወሀት ጨካኝ መሪዎች መቀሌ ተደብቀው እኔ ወደ ምወዳት ሀገሬ መግባቴ መቼም ተአምር ነው፡፡ ህልም እንጂ እውነት አይመስለኝም፡፡ እንደዚያ የራቀችኝን ውዲቷን ሀገሬን በዚህ ፍጥነት ለማየት በመብቃቴ ሃያሉን ፈጣሪን አመሰግነዋለሁ፡፡ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምንም የምለው የለኝም፡፡ ስለእናንተ እኔ ለመናገር ድፍረት ይሆንብኛል፡፡ ያ ሁሉ መዓት ሲወርድባቸው ከአጠገባቸው አልነበርኩም፡፡ በደል ስቃያቸውን ሰምቶ ከማስተጋባት ያለፈ የረዳኋቸው አይመስለኝም፡፡ ሆኖም ይህን ሁሉ ተሻግራችሁ ለዚህ ጊዜ በመብቃታችሁ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ፡፡ ኢትዮጵያ የቃልኪዳን ሀገር ናት፡፡ ጠላቶቿን በእግሯ ስር ያንበረከከች ታሪከኛ ምድር ናት፡፡ በኢትዮጵያ አላፍርም፡፡ በወገኔ አንገቴን አልሰብርም፡፡ አኩሩቶኛል፡፡ ግን አሁንም ብዙ ይቀራል፡፡ አንድነቱን የሚነቀንቅ የጎሳና የብሄር ልዩነት የተዘራበት ህዝብ ፈተናው ብዙ ነው፡፡ ስንቱን መከራ የተወጣ፡ አያሌ ዳገትና ቁልቁለትን የተሻገር ህዝብ አሁንም ለገጠመው ፈተና እጅ ሳይሰጥ ታላቋን ሀገሩን እንዲታደጋት ጥሪ አቀርባለሁ፡፡

# ኢሳት በፍርሃትና ተስፋ መካከል



ሁሴን ከድር

በደርግ የሥልጣን ዘመን የአሜሪካን ድምጽ ሬዲዮ ጣቢያን /ቪኦኤ/ ማዳመጥ የሚቻለው በፍርሃትና ሥጋት ተወጥሮ ነበር። ምናልባት እያዳመጡ ሳለ ፀጉረ ልውጥ ከመጣ ለእስርና ከዚያም ለከፋ አደጋ ያጋልጣል የሚል ሥጋት እንደነበር በወቅቱ ነገሮችን ብዙም ልብ ለማንል ታዳጊዎች ታላላቆቻችን ይነግሩን ነበር።

‹‹ነግሬሃለሁ እኛ ቤት ማታ ቪኦኤ ሲደመጥ ነበር ብለህ ለጓደኞችህ ተሳስተህ እንኳ ብታወራ እገድልሃለሁ።ትንፍሽ ካልክ ሁላችንም ነው ከርቸሌ የምንወርደው ዋ!›› እያሉ ማስፈራራቱ ጥርኘ ብርኘ እያለ ትዝ ይለናል።

ኢሳት ከተመሰረተ ስምንት ዓመት እንደሞላው ፣ስምንተኛ ዓመቱንም ነገ የካቲት ዘጠኝ 2011 በሚሊኒየም አዳራሽ እንደሚያከብር ሰሞኑን በተደጋጋሚ ነግሮናል።ዴሞክራሲን አራምዳለሁ ይል የነበረው ሕወሓት ኢሕአዴግ ከደርግ ባልተናነሰ ኢሳት እንዳይደመጥ ከፍተኛ አፈና ሲያደርግ ኖሮ አፋኙ ወደ መቃብር ታፋኙ ወደ ነፃነት መጥቷል። በሚሊዮን የሚቆጠር ከሕዝብ የተሰበሰበን ግብር ኢሳትን ለማፈኛም አውሏል። የአፈና መሳርያዎችን በድብቅ በመግዛት ጣቢያው ወደ ሕዝብ ጆሮ ደርሶ ጉዱ እንዳይጋለጥ ብዙ ለፍቷል። ያ ሁሉ ጥሮ ግን ሳይሳካለት ገመናው ሁሉ በኢሳት ተጋልጦ፣ የበላ የጠጣው ሁሉ ተዘርግፎ በውርደት ከመንበሩ ተፈንግሏል።

የዲሽ ሳህን ጣርያ ላይና በኮንዶሚኒየም ቤቶች ይሰቅሉ የነበሩ ጠጋኞች በኢሳት ምክንያት ብዙ ዋጋ እንደከፈሉ ሲናገሩ ሰምተን ይሆናል። በአንድ ኮንዶሚኒየም ኢሳትን ለማግኘት የዲሽ አቅጣጫ እንዲያስተካክልላቸው አግባብተው ደህንነቶች ወደ ቤታቸው ያስገቡት ታዋቂ ዲሽ ሠሪ ከፍተኛ ፍዳውን እንደቀመሰ በአንድ ወቅት ያደባባይ ወሬ ሆኖ ነበር። ይህ ዲሽ ሠሪ ደህንነቶቹ የዲሽ ሳህን አቅጣጫውን ካስተካከለና ሪሲቨር ላይ ቁጥሩን ካሳያቸው በኋላ እጅና እግሩን ሰባብረው ሁለተኛ ለሌላ ሰው ቢሰራ ሕይወቱን እንደሚያጣ ዝተው ቤቱ በር ላይ እንደጣሉት በሰፊው ሲወራ ቆይቷል።

ኢሳት በደርግ ዘመን ይደመጥ ከነበረው ከቪኦኤ ያልተናነሰ ዋጋ አድማጮቹን አስከፍሏል ራሱም ከፍሏል። የመሥራቾቹ ጥንካሬና የቀደመ ስማቸው አግዟቸው ከብዙ ወድቆ መነሳት በኋላ ዛሬ ላሉበት የአብርሆት ዘመን ደርሰዋል። ኢሳት በተከለከለ ቁጥር በሕዝብ ዘንድ ተፈላጊነቱ ይጨምር ነበር። በተለይም በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መሠራጨት ሲከለከል በማኅበራዊ ሚዲያ በመከሰት አቅጣጫውን ቀይሮ ወጣቱ ትውልድ የበለጠ እንዲተዋወቀው መሆን ችሎ ነበር።

## የኢሳት ጠንካራ ጎን

ኢሳት በፖለቲካ ኢኮኖሚ በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ አተኩሮ ፕሮግራሙን የሚሰራ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ፕሮግራም ነው። ይህ እኔ እስካለኝ መረጃና ዘወትር የምከታተለውን መሠረት በማድረግ ነው። የተለየ ጥናትና መረጃዎችን አገላብጬ እንዳልሆነ ይመዝገብልኝ።

## ዕለታዊ

ከኢሳት ጠንካራና ቀዳሚ ፕሮግራሞች አንዱ ዕለታዊ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠሩ ዕለታዊ ጉዳዮችን የመወያያ አጀንዳ በማድረግ አጀንዳውን ከተለያዩ ታሪካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጎኖች በመመልከት በበሳል ጋዜጠኞች ይዳሰሳሉ። ነገሮች እንደ ተናጋሪያቸው በጥልቀትና




በዝርዝር መታየታቸው አድማጭ ተመልካቹ ስለነገሮች ሰፊ አመለካከት እንዲኖረው ያደርጋሉ። በእውቀትና በሙቀት የሚናገሩ ጋዜጠኞች የተለያየ የኅብረተሰብ ክፍሎችን አመለካከት ይወክላሉ። በተለይም ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ተሳትፎ የነበራቸው፣በጋዜጠኝነት መንግሥትን ሲያገለግሉ የነበሩ ተወያዮች በዕለታዊ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡት ትንታኔ ከልምድና በእውቀት ላይ የተመሠረተ ነው። በዚህም ስለጉዳዮች ከተራ ግለሰብ አስተያየት ከፍ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህ ፕሮግራም ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው የኢሳት ተወዳጅ ፕሮግራም ነው።

## ዜናዎች

የኢሳት ዜናዎች በሌሎች መገናኛ ብዙኃን ከምናዳምጠው በተለየ አቅጣጫ የሚቀርብ በመሆኑ በመረጃና በአፈተለኩ እውነታዎች የተሞሉ ናቸው። ብዙውን ጊዜ የመንግሥት ምስጢሮች የሚደመጡት ኢሳት ላይ ነው። አልፎ አልፎ ‹‹ምንጮቻችን›› በሚል የሚገልጿቸው ማንነታቸው ለደህንነታቸው ሲባል የሚደበቁ መረጃ አቀባዮች አንዳንዴም አሳሳች ሆነው ይገኛሉ። በርግጥ ወሬ አቀባዮቹ አንዳንዴ ሆን ብለው የተፈበረኩ ወሬዎችን በማስነዛት የኢሳት ታማኝነት አጠያያቂ እንዲሆን ሊያደርጉት የታቀደ ሊሆን ይችላል። ኢሳቶች ባለፉት ስምንት ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐይንና ጆሮ ሆነው መዝለቃቸው አሌ አይባልም። ይህ የሚያበግናቸው፣ በኢሳት ወሬዎች ሱቃቸው የሚዘጋባቸውና ገበያቸው የሚቀዘቅዝባቸው ቦናፖርቲስቶች የኢሳት ታማኝነት እንዲጠፋና ንግዳቸው እንዲያተርፍ አይጥሩም አይባልም። ከዚህ በኋላም ሊመጡ ይችላሉና ጣቢያው ጥንቃቄ ሊለየው አይገባም።

ዛሬ ለ27 ዓመታት በኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ላይ ተዘፍዝፎ የነበረው ሕወሓት ሰራሹ ኢሕአዴግ በመንበሩ የለም። ነገ ኦሕዴድ ሰራሹ ኢሕአዴግ አይመጣም ማለት የዋህነት ነው። መንበር እስኪረጋጋ ጨዋ የሚመስል ባለሥልጣን ሲደላደልና የዘረፋ ሴሉን ሲዘረጋ ‹‹ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል›› ብሂሉን መዘዝ ማድረጉ አይቀርም። ኢሳት ዛሬ ያለው አየር ጥሩ ቢሆንለትም በዚህ አያያዙ ከቀጠለ ነገ በጠላትነት ሊታይ ይችላልና በጥንቃቄ መጓዝ ነው የሚኖርበት። ዶ/ር ዐቢይ እውነተኛ ሀገር ወዳድ ቢሆን ዶ/ር ዐቢይ ብቻ አገር ሊመራ አይችልምና ነቃ ብሎ መጠበቁ አይከፋም። የኢሳት ዜናዎች ምስጢር በማውጣትና ግራ ቀኝን በማሳተፍ ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል።

## ፖለቲካችን

ከኢሳት ታላላቅ ፕሮግራሞች መካከል ሌላው ፖለቲካችን ነው። በፖለቲካ ጉዳይ የሚያጠነጥነው ይህ ፕሮግራም በቅርቡ በሃብታሙ አያሌውና በኤርሚያስ ለገሰ በመቅረብ ላይ ነው የሚገኘው። በፕሮግራሙ አብይ ነጥቦች ከመተንተናቸው ባሻገር እንግዶች ሃሳብ እንዲሰጡባቸው ይደረጋሉ። ይህም ፕሮግራሙን አሰልቺ እንዳይሆን ያደርገዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን በዚህ ፕሮግራም የኢህአዴግን ደካማ የፖለቲካ እሳቤ ከመተቸት ባሻገር ትክክለኛው አካሄድ የቱ እንደሆነ ሲጠቁም አላጋጠመኝም።

የኢሕአዴግ ተፎካካሪ ፓርቲዎችም /ተፎካካሪነቱ አጠያያቂ ሆኖ/ ምን አርመው በየትኛው አቋማቸው ገፍተው መሄድ እንደሚገባቸው አቅጣጫ ጠቋሚ ፕሮግራም ቢሆን የኢሳትን ለአገር ተቆርቋሪነት በደንብ ባየን ነበር። ከሌሎቹ ፕሮግራሞች ይልቅ እዚህ ላይ ኢሕአዴግ በጣም ሲብጠለጠል ስለሚያጋጥመኝ ነው። በሥህተቱ አይኮነን ለማለት ሳይሆን አገሪቱን በመምራት ላይ ያለ ፓርቲ እንደመሆኑ እሱ ሲወድቅ አገሪቷንም ይዞ እንዳይንከባለል ‹ባይሰማም› ምክር ቢሰጠው መልካም ነው። ምናልባት ሌላ ፓርቲ ቢመጣ ከኢሕአዴግ ስህተት ሊማር ይችላልና።

ኢኮኖሚያችን፣ የኢሳት እንግዳ፣ ፍልስፍና፣ ከደራሲያን፣ አልፎ አልፎ ተቦርነ የሚያቀርበው የታማኝ ፕሮግራም ከምከታተላቸው ዝግጅቶች መካከል ናቸው፡፡ የተቦርነ ዝግጅት በአጋጣሚ ካልሆነ ለመከታተል የሚመቸኝ ጊዜ ባለመሆኑ አቃቂር ላወጣበት አልችልም፡፡ /አቃቂርን በአሉታዊ ትርጓሜ አትውሰዱብኝ/ ኢኮኖሚያችንና ፍልስፍና የሙያው ሰዎች የሆኑ ተባባሪ አዘጋጆች ወይም አማካሪዎች ያሉት ፕሮግራም በመሆናቸው በትኩረት ነው የምከታተላቸው፡፡ እንዲያመልጡኝ፣ በወሬ መሃል እንዳዳምጠውም አልፈልግም፡፡ ፕሮግራሞቹን ከመውደዴ የተነሳ ይሁን ወይም በዘርፎቹ ላይ የመናገር አቅሙ ስለሌለኝ ባላውቅም እንከን መምዘዝ አልቻልኩም፡፡ እንዴት መሻሻል እንዳለበት የምጠቁመው ነጥብም የለም፤ በተለይም በኢኮኖሚያችን ፕሮግራም፡፡ አክዬም የሲሳይ አጌና የኢሳት እንግዳ ፕሮግራምም ቀልብን ማራኪ፣ እውቀትን መጋቢ ፣አሳዋቂና መረጃን የሚሰጥ በመሆኑ ልዩ ክብር እሰጠዋለሁ፡፡


አንዳንድ መገናኛ ብዙኃን ጥንካሬያቸው የሚነገረውን ያህል ቀርነት የሚታይባቸው በሴት ጋዜጠኞች አናሳነት ሆኖ ይታያል፡፡ ኢሳት ላይ ይህ ችግር የጎላ አይደለም፡፡ የሴት ጋዜጠኞች የወንዶችን ያህል በዝተውና ፖለቲካንም ሆነ ማኀበራዊ ሕይወትን በመተንተን ረገድ የወንዶቹን ያህል ጠንክረው ባይታዩም የጎላ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

ርእዮት ዓለሙ፣መታሰቢያ ቀጸላ፣እየሩሳሌም እና ገሊላ ከሌሎቹ ሴት ጋዜጠኞች በጥንካሬያቸው ጎልተው ይወጡብኛል፡፡ በአንድ ወቅት በዕለታዊ ፕሮግራም ላይ ርዕዮት ባቀረበችው ሃሳብ ልልነት ውይይቱን ማለዘቡን ገልጬ በማኀበራዊ ገጽ ጽፌ ነበር፡፡በወቅቱ ጥቂት የተቃውሞ በርከት ያሉ የድጋፍ ሃሳቦችንም አስተናግጃለሁ፡፡ ከዚህም አልፎ ከርእሷ የወጡ ሰዎች የየራሳቸውን ስሜት በመግለጽ ርእዮትን ኮንነው ጽፈውም ነበር፡፡ የማኀበራዊ መገናኛ መጥፎ ጎኑ ይኸው ነው፡፡ ለጽሑፍ የተሳለ እርሳስ ለመውጋት የሚጠቀሙ ሰዎች እጅ ይወድቅና ይጎዳል፡፡ የሆነ ሆኖ ርእዮት አሁን እያቀረበችው ያለው የፍልስፍና ፕሮግራም አያያዝ ማለፊያ በመሆኑ በርቺ እላለሁ፡፡ በይበልጥ የመናገር እድሉን ለእንግዶቿ በመስጠት እንግዶቿ ወደ ምትፈልገው አቅጣጫ እንዲፈሱ ብታደርግና የሷ ትንታኔ አነስ ቢል የበለጠ የተዋበ ይሆናል፡፡

## የኢሳት ውስንነት

ኢሳት ወጣቶችን ታሳቢ የሚያደርግ ፕሮግራም ሲያቀርብ ብዙም አላጋጠመኝም፡፡ ምናልባት እኔ ፕሮግራሙን የምከታተልበት ወቅት በምሽት መሆኑ ለወጣቶች የተዘጋጀው ፕሮግራም አምልጦኝ ሊሆን ይችላል፡፡ የኢሳትን ፕሮግራም የምከታተለው አብዛኛውን ጊዜ ከምሽቱ 2-5 ባለው ሰዓት ነው፡፡

በኢሳት ቅርጽና ይዘት ወጣቶችን ታሳቢ ማድረግን ሳስብ ወደ አእምሮዬ የሚመጣው አገር ተረካቢ ወጣት ፤የአገር ፍቅር እንዲያድርበት የሚደረግ ወጣት፤ ባንዲራውን የሚወድ ወጣት፤ የመሳሰሉትን ነው፡፡ ምክንያቱም ኢሳት ቆፍጠን ያለ ጎልማሳ ጣቢያ የሚመስል ቅርጽ በጭንቅላቴ ስለፈጠረ ነው፡፡ እግረ መንገዴን ሸገር ፎልፏላ ማራኪ ሽማግሌ፣ ኢቢሲ መንቻካ ነጭናጫ ሽማግሌ፣ ፋና እምቡር እምቡር ባይ ጎረምሳ፣ የድሮዋ ዛሚ በስጡም በቡቱቶውም የምትነዛነዝ አሮጊት፣ አዲስ አበባ መስተዳድር መገናኛ ብዙሃን መኖሩም መምጣቱም ሳይታወቅለት የሞተ ጎረምሳ ይመስሉኛል፡፡




ወደ ኢሳት ስመለስ ወጣቱን ማእከል ያደረገ፣ ወጣ ብሎ ነገሮችን ማየት የሚቻልበት፤ በተዘዋዋሪ መንገድ አገሩን የሚወድ ወጣት መፍጠር የሚቻልበት ፕሮግራም ቢታሰብ መልካም ነው፡፡

በትምህርት ውጤታቸው የላቁ ወጣቶችን በእንግድነት በማቅረብ /ፕሮግራሙም በእድሜ አቻዎቻቸው ተሰርቶ/ በስፖርት፣ በኪነ ጥበብ፣ በውትድርና፣ በጋዜጠኝነት፣ በግብርና፣ በፈጠራ ሥራ፣ በኮምፕዩተር ኢንጂነሪንግ፣በንግድ፣ በኃላፊነት ቦታ ላይ የተቀመጡ ወጣቶችን / እድሜያቸው ከ20-30/ ከሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ፈላልጎ እንግዳ በማድረግ ቢቀርቡ፤ ስለ የወጣቶች የመዝናኛ ቦታዎች ተከታታይ ፕሮግራም ቢሠራ፣ የዓለም ዝነኛና ታዋቂ ተጽእኖ ፈጣሪ ወጣቶች ቢቀርቡ፣ የፈጠራ ክህሎት ማዳበሪያ ስልቶችን ማሳየት ቢቻል፣ በእነዚህና በሌሎችም ፕሮግራሞች ወጣቶችን መያዝ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ በተረፈ ኢሳት የወጣቱን ስሜት ከመግዛት ይልቅ የጎልማሳውና የአዛውንቱ ጣቢያ ብቻ ሆኖ እንዳይቀር ያሰጋኛል፡፡

በኢሳት ዘገባዎች ብዙውን ጊዜ የሚሰሙት የተበዳዮች፣የግፉኣን ድምጽ ነው፡፡ በዳይ ተብለው የሚኮነኑ ባለሃብቶች ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት በመደበቅም ይሁን መልስ ለመስጠት ባለመፈለግ ድምጻቸው አይሰማም፡፡ ይህን ማስተካከል የሚቻልበት መንገድ ቢሞከር የተሻለ ነው የሚሆነው፡፡

የኢሳት የዜና ምንጮች ወሎ፣ትግራይ ፣ቤኒሻንጉል፣ አርሲ፣ኢሊባቡር፣ጂማ የመሳሰሉት አካባቢዎች ላይ ብዙም ትኩረት አይሰጥም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የጎንደር ወረዳዎች በዘገባ ይዳሰሳሉ፡፡ ይህ መልካም ሆኖ ሳለ የወሬ ምንጮች በየክልሉ ቢኖሩ የበለጠ የተሟላ ያደርገዋል፡፡

ኢሳት በጥንቃቄ ከሚሰራቸው ሥራዎች አንዱ የዘርና የሃይማኖት ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም ሃይማኖትን በፍራቻ ነው የሚያየው፡፡ በክርስትና ሃይማኖት ነክ ዘገባዎች ላይ ብዙም እንከን አላየሁም፡፡ ጋዜጠኞቹ እስልምናን በተመለከተ ያላቸው እውቀት ከማኀበራዊ ሕይወትና ከውስን ንባብ ባሻገር የሰፋ መስሎ አልታየኝም፡፡ ይህም በመሆኑ በተለይም እስልምናን የተመለከተ ሃሳቦች ሲነሱ ዳርዳሩን ሲሄዱ አይቻለሁ፡፡ ይህ የኢሳት ብቻ ሳይሆን ከሸገርና ፋና ውጪ ያሉ መገናኛ ብዙሃን ችግርም ነው፡፡ ቪኦኤ ጭራሽ የባሰበት ነው፡፡

ኢሳት ይህን ለማስተካከል የእስልምና ሃይማኖት ግንዛቤ ያለውና የጋዜጠኝነት ሥነምግባርን ጠንቅቆ የሚያውቅ ጋዜጠኛ ቢኖረው ችግሮችን ማቃለል የሚቻል ይመስለኛል፡፡ በተለይም በእለታዊ ወሬዎች ወቀት ጉዳዩ እስልምና ላይ ያመዘነ ከሆነ ከዚህ ጋዜጠኛ ወይም የኢሳት የእስልምና ሃይማኖት ዘገባዎች አማካሪ በቂ ግብአቶች ቢወሰዱ ከበዛ ጥንቃቄና ፍርሃት መላቀቅ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

## እንደመውጫ

የኢሳት ስምንት ዓመታት ለጋዜጠኞቹ በውጣ ውረድ የተሞሉ ቢሆኑም ለኢትዮጵያ ሕዝብ የለውጥ ቀንዲል የለኮሱና ከሁሉም የኀብረተሰቡ ተቃውሞዎች ፊት የነበሩ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በታላቅ ባለውለታነት ሊመለከታቸው ይገባል፡፡ ኢሳት፡- ድምጻችን ይሰማም፣ቁሮም፣ ፋኖም፣ዘርማም ሆኖ ነበርና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሲታገል የኖረው፣ ዛሬ መላው ሕዝብ ከጎኑ ሊሆን ይገባል፡፡

በአረብ አብዮት ወቅት የግብጽ ሕዝብን የጭቆና አገዛዝ ገርስሰው የጣሉት የግብጽ ወጣቶች ብቻ ሳይሆኑ አልጀዚራም ጭምር ነበር፡፡ በተለይም የአረብኛው ፕሮግራም፡፡ በዚህ ተጋድሏቸው የአልጀዚራ ጋዜጠኞች ከፍተኛ ዋጋ ከፍለውበታል፡፡ ታስረዋል፣ ተደብድበዋል፣ ፓስፖርት ተቀምተዋል የሞቱም ነበሩ፡፡ ምንም እንኳ የግብጽ አብዮት በአልሲሲ ቢቀለበስም እንደ ግብጻውያን ገለጻ የቀድሞው ፍጹም ጨቋኝ መሪ ሆስኒ ሙባረክና ግብራበሮቹ ዛሬ መንበሩ ላይ የሉም፡፡ በኢትዮጵያም ሕወሓት ኢሕአዴግ በሕዝቡና በኢሳት ያላሰለሰ ተቃውሞ ከቦታው ተወግዷል /የአበበ ገላው መለስ ላይ ያዘነበው የቃላት ክሩዝ ሚሳኤል እንደ መጀመርያ ጥይት ትቆጠራለች/፡፡

ነገ የኢትዮጵያ የለውጥ አየር ተቀልብሶ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአውሬዎች እጅ ላይ ስላለመውደቁ ዋስትና የለምና ኢሳት ዘመቻዬ ተጠናቀቀ ብሎ ትጥቁን ፈትቶ ሊዘናጋ አይገባም፡፡ በሕዝብ የተጣለበትን አደራ ትክክለኛ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ እስኪመጣ ድረስ ሊታገል ይገባዋል፡፡

**መጪው ዘመን የተሻለ ስኬት የሚጎናጸፍበት እንዲሆን እመኝለታለሁ።**

# “ኢሳት በአገሪቱ ያለው የሰብዓዊ መብት ረገጣ እንዲጋለጥ ከፍተኛ ሥራ ሠርቷል”

**ጋዜጠኛ ወንድማገኝ ጋሹ**

**ግዮን፡ - ከአገር ቤት በምን ሁኔታ እና መቼ ነበር የወጣኸው?**

ወንድምአገኝ፡- ከአገር የወጣሁት በ1998 ዓ.ም ነው፡፡ ቅንጅት በሕዝብ ድምፅ ምርጫውን አሸንፎ እንደነበር ይታወሳል፡፡ በዚህ ወቅት ሕወሐት ኢህአዴግ አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ የሰብዓዊ መብት ጥሰትና ግድያ ፈፅሟል፡፡ ከሰኔ 1 ቀን ጀምሮ ችግሮች ባሉበት ስፍራ ድረስ በመገኘት የምርመራ ስራ ከባልደረባዬ ጋር እሠራ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ከመንግስት የደህንነት ኃይሎች የአፈና ሙከራ በተደጋጋሚ ለመፈጸሞ ይሞክሩ ነበር፡፡ በ1998 ዓ.ም ሁኔታው ከበድ ያለ ነበር፡፡ የተለያዩ ወከባዎች እና ፍተሻዎች እየተጠናከሩ በመምጣታቸው የተነሳ በቀና ኢትዮጵያዊያን ትብብር ድጋፍ ተደርጎልኝ በኬንያ በኩል ከአገር ልወጣ ችያለሁ፡፡

**ግዮን፡ - ከኬንያ በኋላስ ወዴት ሄድክ?**

ወንድም አገኝ፡- ኬንያ በቆየሁበት ስምንት ወር ውስጥ ከአምነስቲ ኢንተርናሽናልና ከአንድ ሌላ የኬኒያ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተቋም ጋር ስሰራ ቆይቼ የእንግሊዝ መንግስት ወደ እንግሊዝ እንድገባ በዩኤን ኤች አር በኩል ፈቃድ በመገኘቱ ወደ እንግሊዝ አገር ልገባ ችያለሁ፡፡

**ግዮን፡ - ወደ ኢሳት ለመግባት ያነሳሳህ ምክንያት ምንድን ነው? መቼስ ነበር ኢሳትን የተቀላቀልከው?**

ወንድም አገኝ፡- ከዛሬ ስምንት ዓመት በፊት ነው ኢሳት ላይ መስራት የጀመርኩት፡፡ ከሀገሬም ከመውጣቴ በፊት የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ላይ የምርመራ ሥራ ኢሰመጉ ውስጥ እሰራ ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ በዜጎች ላይ የሚደርሰውን የመብት ጥሰት በተመለከተ ብዙ መረጃዎችን አውቃለሁ፡፡ 97 ዓ.ም ምርጫውን ተከትሎ መንግስት በወሰደው እርምጃ በርካታ ግድያዎች ተፈጥመው ነበር ፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች አስከሬኖችም አይቼ ስለነበር ለእነዚህ ሰዎች ድምፅ መሆን አለብኝ፤ ይህንን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ማሳወቅ አለብኝ የሚል ሀሳብ ይገዤ ነበር፡፡ ካለኝ መረጃ ተነስቼ ለንደን ላይ ካሉ አገር ወዳድ ወገኖች ጋር በተለይ ከሲቪክ ማህበራት ጋር መስራት ጀመርኩኝ ከዚያ በኂላ ኢሳት ሲከፈት የበለጠ ሰብዓዊ መብት ችግሮች ላይ ትኩረት ሰጥቼ መስራት ስለፈለኩ ነው ወደ ኢሳት ልገባ የቻልኩት፡፡

**ግዮን፡ - የለንደን የኢሳት ቢሮ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

ወንድምአገኝ፡-ሥራ ስንጀምር አንድ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ልጅ ቤት ነበር የጀመርነው፡፡ ይህ ልጅ ዘላለም ይባላል፡፡ ኤዲቲንግም ፕሮዲዩስም ማድረግ የሚችል ነው፡፡ እርሱ ቤት ነው ቀረፃ የጀመርነው፡፡ ቤቷ ጠባብ ብትሆንም በጊዜው በቂ አገልግሎት ሰጥታለች፡፡ አሁንም በጎ ፈቃደኛ ሰው በሰጠን ስቱዲዮ ውስጥ ነው ሥራችንን እየሰራን የምንገኘው፡፡

**ግዮን፡ - የለንደን የኢሳት አባላት እነማን ናቸው? እስኪ አስተዋውቀን**

ወንድምአገኝ፡- መታሰቢያ፣ ዶ/ር ታደሰ ብሩ፣ እኔነበርን፤ ከዚ ቀደም ደግሞ አቤ ቶኪቻው እንዲሁም ፍስሃ ተገኝም በስፖርቱ በኩል ከኛ ጋር ይሰራ ነበር፡፡ ወደ ፊት ደግሞ ኢሳት ሲስፋፋ የበለጠ ተጨማሪ ነገሮች እንሰራለን፡፡ በኤዲቲንግ በኩልም ያሬድ እና ቴዲም አብረውን ይሰራሉ፡ ፡ ሌሎች በጎ ፈቃደኞችም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ቅን ከሆኑ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡

**ግዮን፡ - አብዛኛው ነገር በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው ፤በዚህ ሁኔታ እስከ መቼ መቀጠል ይቻላል?**

ወንድምአገኝ፡- ላለፉት ስምንት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው አፈና



ላይ ትኩረት ተደርጎ ርብርብ ነበር የሚደረገው፡፡ የሥራ ሠዓት አይወስነንም፤ ሁሉም ባለው አቅም ይተጋ ነበር፡፡ አሁንም በተቋም ቅርፅ ልክ እንደ አንድ ትልቅ ሚዲያ ወደ ተሻለ አደረጃጀት ለመሄድ እየተሰራ ነው ፡፡ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ የመጣውን ለውጥ ተከትሎ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የኢሳት አመራር እና ሌሎችም አካላት ኢሳትን የበለጠ አጠናክሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይንና ጆሮ ሆኖ እንዲቀጥል እየታሰበበት ነው፡፡ ወደ ፊት አብረን የምናየው ነው የሚሆነው፡፡

**ግዮን፡ - እስካሁን ትኩረት አድርገህ እየሰራህ ያለኸው በሰብዓዊ መብት ላይ ነው፤ ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው? ወደ ፊትስ ምን ለመስራት አስበሃል?**

ወንድምአገኝ፡- አብዛኛው የሥራ ልምዬና ተሞክሮዬ ከሰብዓዊ መብት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈፀሙ የመብት ረገጣዎች ከግድያ ጀምሮ ታፍነው የደረሱበት ቦታ የማይታወቅ ዜጎች በርካታ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰለባ የሆኑት ሰዎች በስም፤ በማንነት፤ ቤተሰቦቻቸውን ጭምር በሥራ ላይ በነበርንበት ጊዜ እናውቃለን፡፡ የመብት ጥሰቶች፤ መፈናቀል፤ ስቃዮች ሲደርሱ ነበር፡፡ ዜጎች ስለ መብቶቻቸው እንዲያውቁ፤ ስለዴሞክራሲ እንዲረዱ ለማነሳሳትም ይጠቅማል ከሚል እሳቤ የተነሳ ነው እዚህ ስራ ውስጥ የገባሁት፡፡



አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ የመብት ጥሰት ባይኖርም ዜጎች መብታቸውን ለማስከበር በዕውቀትና በእውነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ ወሳኝ ድርሻ የሚጫወተው ሚዲያ ነው፡፡ ሌላው ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው ሲቪክ ማህበራት፤ መንግስታዊ ያልሆኑ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብት ተቋማት ናቸው፡፡ በተለይ ሚዲያ በሌላው ዓለም እንደ አራተኛ መንግስት የሚቆጠር ጠንካራ ተቋም ነው፡፡ ሚዲያ በመንግስትና በሕዝብ መካከል ሆኖ የህዝብን ጥቅም መሰረት አድርጎ ለሕዝብ የሚሟገት ተቋም ነው፡፡ ሚዲያ ከመምረጥ እና የመመረጥ ሥራዎች ጋር ግንዛቤ የማስጨበጥ ተግባር የሚፈፅም ለዲሞክራሲ ለሰብዓዊ መብት መጠበቅ ወሳኝ ሚና ሊወጣ የሚችል አንድ መሳሪያ ነው፡፡ ስለዚህ ወደፊት በዚህ ላይ አጠናክሬ ለመስራት ነው ያሰብኩት፡፡

**ግዮን፡-በዚህ ስራ ላይ በቆየህበት ጊዜ የሰብዓዊ መብት ጥሠት የደረሰባቸውን አካላት ለማግኘት የመረጃ ችግር አልገጠመህም? በተለይ ለንደን ከመጣህ በኋላ?**

ወንድምአገኝ፡-በሰብአዊ መብት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት አስቸጋሪ ነው ሰዎች በፍርሀት ውስጥ ሆነው መረጃ ማቀበል ያስፈራቸዋል፡፡ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ ሆነውም ግን መረጃዎች በተለያየ መንገድ ያደርሱናል፣ በስልክ፣ በኢሜይል፣ በሰዎች ጥቆማ ይመጣሉ፡፡ ጥቆማው በመረጃ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማጣራት ተገቢ በመሆኑ በደንብ ምርመራ እናደርጋለን፤ በጣም ብዙ አድካሚ ስራ እንሰራለን፡፡

ለምሳሌ በ1998 ዓ.ም የተፈፀመ የሰራሁት የዶክመንተሪ ፊልም ነበር ፡፡ ፊልሙ ወደ 55 ደቂቃ ይፈጃል፡፡ አገር ቤት በነበርኩበት ሰዓት የነበሩ መረጃዎች ስለነበሩኝ ያንን ነው የተጠቀምኩት፡፡ መርካቶ ላይ የተገደሉ ወንድማማቾች ነበሩ፡፡ ከነሱ ጋር የወደቀ ልጅ ነበር፡፡ በጊዜው ይን ልጅ ፎቶ አንስቼዋለሁ፤ ዶክመንተሪው ሲተላለፍ ይሄ ልጅ ያያል፤ ክንፈ ገ/ሚካኤል ነው የሚባለው፡፡ ፊልሙን ካየ በኂላ ኢሳትን አገናኙኝ ብሎ ይደውላል፡፡ በኂላ ተገናኘን፡፡ "ኢሳት ላይ የኔን ፎቶ ሳየውና ወደ ኂላ ተመልሼ ስመለከት ደስታም ሀዘንም ይሰማኛል፤እኔ ካሉት በታች ከሞቱት በላይ ነኝ፤ ጓደኞቼ ሰርተው ራሳቸውን ለውጠዋል፤ እኔ ግን እጅና እግሬ ሽባ ስለሆነ ያንን ማድረግ አልቻልኩም" አለኝ፡፡ እኔም ሚዲያ ላይ አቅርቤው ሕዝቡ ተረባርቦ አሳክሞ ከህመሙ ሊድን ቻለ፡፡ እንዲህ ዓይነት ነገሮች ብዙ አሉ፡፡ አካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች በምታገኝበት ሰዓት በጣም ታዝናለህ ልብህን ይሰብረዋል፤ ማኀበረሰቡም ደግሞ ለመርዳት የሚያደርገውን ተነሳሽነትና አጋርነት ስታይ ደግሞ ትደሰታለህ፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ሥራ ውስጥ ልብን የሚያሳሳ ነገር ቢኖርም ውጤቱ ደግሞ ያስደስታል፡፡

**ግዮን፡- የአንተ ሥራ በሌሎች ላይ የሚደርስን ግፍና በደል ማሳወቅ ላይ ያተኮረ ነው፤ በአንድ ወቅት ባለቤትህ ላይ እና ልጆችህ ላይ የደረሰን የመብት ጥሰት በተመለከተ አጫውተን?**

ወንድምአገኝ፡- በቅድሚያ በዚህ አጋጣሚ ባለቤቴን ማመስገን ቢፈቀድልኝ ደስ ይለኛል፡፡ ባለቤቴ ወ/ሮ አበባ መልሰው ትባላለች፡፡ ከኔ በስተጀርባ ሆና ለምሰራው ሥራ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጋለች፡፡ በተለይ በስደት አገር ልጆች ይዞ መኖር አስቸጋሪ ነው፡፡ እርሷ ግን ይህ ሁሉ ሳይከብዳት ወደዚህ ስራ እንድገባ ገፋፍታኛለች፤ ለዚህ ደግሞ እርሷን ከልብ ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡

ባለቤቴ ከአራት ዓመት በፊት ልጆቻችንን ይዛ ለእህቷ ሠርግ አዲስ አበባ ሄዳ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ለሰርጉ እንዳትደርስ ለማድረግ ነበር የሞከሩት፤ ነገር ግን ለጊዜው ያለችበትን ቦታ ማወቅ ስላልቻሉ ከሰርጉ ፍፃሜ በኃላ ማታ ቤቱን ከበው አደሩ፤ ጠዋት ላይ የ3 ዓመት የ9 እና የ11 ዓመት ልጆቹን ጨምሮ ከቤት ወስደው ማንገላታት ጀመሩ፡፡ እዚህ አገር ለመኖር ከፈለግሽ ባለቤትሽ ከኢሳት እንዲለቅ ማድረግ አለብሽ አለበለዚያ እኛ እርምጃ ልንወስድ እንችላለን በማለት አስፈራርተዋት ነበር፡፡የህውሓት ደህንነቶች የእነ ጌታቸው አሰፋ እጅ እንዳለበት ለማወቅ ችያለሁ፡፡ ሕፃናቱን ምግብ ከልክለው ለማሰቃየት ሙከራ አድርገዋል፡፡

**ግዮን፡- ባለፋት ስምንት ዓመታት አሁን በኢትዮጵያ ለመጣው ለውጥ የኢሳትን አስተዋፅኦ እንዴት ትገልፀዋለህ?**

ወንድምአገኝ፡- የኢሣትን አስተዋፅኦ ማህበረሰቡ ቢመሰክር ይመረጣል፡፡ ኢሣት በአገሪቱ ያለው የሰብዓዊ መብት ረገጣ እንዲጋለጥ ከፍተኛ ሥራ ሠርቷል፡፡ ሀሳብ ያላቸው የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ዕድል በመስጠት ሀሳባቸውን ለህዝብ እንዲገልፁ ማድረግ ተችሏል፡፡ ለበርካታ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እና ድምፅ ለሌላቸው ዜጎች ድምፅ በመሆን በአገሪቱ ውስጥ ሲካሄዱ የነበሩ የመብት ረገጣዎችን በማጋለጥ የሕወሐት መራሹ መንግስት እንዲዳከም እና የለውጡ ኃይል ብርታት እንዲያገኝ አስተዋፅኦ በማድረግ ውጤታማ ሥራ ተሰርቷል ብዬ መናገር እችላለሁ፡፡

ይህ ሁሉ ሲሰራ ግን ብዙ ውጣ ውረድ ታልፎ መሆኑን መረሳት የለበትም፡፡ ኢሣት ከ22 ጊዜ በላይ በሕወሐት መንግስት ሲዘጋ ሲታፈን እንደነበር የኢትዮጵያ ሕዝብ በደንብ የሚያውቀው ሀቅ ነው፡፡

**ግዮን፡- ከረጅም ዓመት ቆይታ በኋላ ወደ አገር ቤት ለመግባት በዝግጅት ላይ ነህ ምን ተሰማህ?**

ወንድምአገኝ፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፈለው መስዋዕትነት ዛሬ ለደረስንበት ቀን መድረስ ችለናል፡፡ ከ13 ዓመት በኂላ አገሬ ለመግባት እያኮበኮብኩ ባለሁበት ሰዓት ደስታዬ በጣም የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም የወጣሁበት ሁኔታ የሚታወቅ ነው፡፡ ለዴሞክራሲ መረጋገጥ፤ ለሰብዓዊ መብት መከበር፤ ለህግ ልዕልና መስፈን የሚዲያው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነበር፡፡

እኔም ባለኝ አቅም በምችለው ደረጃ ለአገሬ እና ለህዝቧ የተሻለ ለመስራት ቃል የምገባበት ጊዜ ነው፡፡ በመሆኑም የተለኮሰውን የነፃነት ችቦ እስከ ተራራው ጫፍ ለማድረስ ጠንክረን መስራት ይጠበቅብናል የሚል እምነት አለኝ፡፡



# ዳግማዊቷ ሲልቪያ ፓንክረስት

# ታታሪዋ ዲፕሎማት ማዳም አና ጎሜዝ

**ስለ ራሳቸው ብዙም ማውራት የማይወዱት የአውሮጳ ፓርላማ አባል ማዳም አና ጎሜዝ፣ ከስድሳ አራት ዓመት በፊት እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር ፌብሯዋሪ 19 ቀን 1954 በፖርቱጋል ዋና ከተማ ሊዝበን ውስጥ ነው የተወለዱት፡፡አና ጎሜዝ የብዙዎችን ቀልብ መሳብ የጀመሩት ገና በአፍላ እድሜያቸው በትምህርት ቤት ቆይታቸው ነበር፡፡ በሃያ አምስት ዓመታቸው ከሊዝበን ዩኒቨርስቲ በሕግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙ ሲሆን በቀጣዩ ዓመት በፖርቱጋል የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥረው መሥራት ጀመሩ፡፡የትዳር ሕይወታቸውን በተመለከተ ባለትዳርና  የሶስት ልጆች እናት ናቸው፡፡**

በፖርቱጋል ውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ውስጥ በጀማሪ ዲፕሎማትነት ሥራቸውን አሀዱ ብለው የጀመሩት አና ጎሜዝ ፣ብዙም ሳይቆዩ  ከአንድ ዓመት በኋላ የፖርቱጋል ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት፣ የጄነራል አኔሞሮ አናንስ የዲፕሎማቲክ ጉዳዮች ልዩ አማካሪ በመሆን ለአራት ዓመታት በከፍተኛ ኃላፊነት ተመድበው ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡

አና ጎሜዝ በሊዝበን ዩኒቨርስቲ በሕግ ፋክልቲ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ እያለ በዩኒቨርስቲው የተማሪዎች  ምክር ቤት ውስጥ በነበራቸው ንቁ ተሳትፎ፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የቀዝቃዛው ጦርነት የፖለቲካ ውጣ ውረድ ውስጥ በየትኛውም የዓለም ክፍል ያለው የሠራተኛው መደብ ድምፁ እንዲሰማ እና መብቱ እንዲከበር በሚደረጉ የዓለም አቀፋዊ አጋርነት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ነበሩ፡፡

ከ1982 ጀምሮ የፖርቱጋል ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት ጽህፈት ቤት ባልደረባ በመሆን ለአራት ዓመታት የሰሩት ማዳም አና ጎሜዝ፣ በዓለም አቀፉ መድረክ የፖርቱጋል መንግሥት ልዑካን ቡድን አባል በመሆን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስር ባሉ ልዩ ልዩ ተቋማት የፖርቱጋል መንግሥት ቋሚ መልዕክተኛ አንደኛ ፀሐፊ በመሆን ተመድበው፣ በኒውዮርክና በጄኔቫ በመዘዋወር ከ1986 እስከ 1989 ያሉ ሦስት ዓመታት የሀገራቸው ዲፕሎማት በመሆን ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡

በቀጣይም ከ1989 አንስቶ እስከ 1991 በቶኪዮ ጃፓን የፖርቱጋል ኤምባሲ ቆንስላ ጄነራል በመሆን ሲያገለግሉ ቆይተው ወደ ብሪታኒያ በመዘዋወር፣ ለሶስት ዓመታት በለንደን የፖርቱጋል ኤምባሲ የፖለቲካ ጉዳዮች ጄነራል ቆንስላ ሆነው እስከ 1994 ድረስ በከፍተኛ

*በኢትዮጵያውያን ዘንድ ማዳም አና ጎሜዝ ልክ እንደ ኢትዮጵያዊ የሰብአዊ መብት ታጋይ ስማቸው ገኖ እንዲታወቅ ያደረጋቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለነጻነት በተደረገ ትግል ውስጥ ዘወትር ከሚዘከሩት የሀገር ባለውለታ ከነሲልቪያ ፓንክረስት ተርታ ስማቸው እንዲሰፈር የሚያደርግ ተግባር በመፈፀማቸው ነው።*



ዲፕሎማትነት ሀገራቸውን አገልግለዋል።

በለንደን ከነበራቸው የሶስት አመት ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ ሥራ ኃላፊነት በተጨማሪ ሀገራቸውን በመወከል በአውሮጳ ሕብረት ስር የመካከለኛው ምሥራቅ የሰላም ሒደትን በተመለከተ የሚከታተል ግብረ ሃይል ውስጥ በጄኔቭ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ውስጥ የፖርቱጋል ልዑካን ቡድን መሪ ሆኖ ሠርተዋል።

የሰብአዊ መብት እና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ እውቀና ካለው የዩንቨርስቲ ኦፍ ስትራስበርግ በኢንተርናሽናል ሂዩማን ራይትስ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ያገኙት አና ጎሜዝ፣ በሊዝበን በሚገኘው የፖርቱጋል ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የአውሮጳ ጉዳዮች ዴስክ ዋና ተጠሪ በመሆን እስከ 1996 ለሦስት አመታት ለመሥራት ችለው ነበር።

በፖርቱጋል የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የሥራ ኃላፊዎች የዲፕሎማት አና ጎሜዝን የሥራ ክህሎት እንዲሁም በዘርፉ የሚያካሂዱትን እንቅስቃሴን በቅርበት ይከታተሉ ስለነበር በ1997 መጀመሪያ ላይ በኒውዮርክ የተመድ የፀጥታ ምክር ቤት ውስጥ የፖርቱጋል ልዑካን ቡድን መሪ ሆነው እንዲሠሩ ተመደቡ። በኒውውዮርክ በዚህ ከፍተኛ ኃላፊነት እያገለገሉ በተደራቢም በጊዜያዊነት የፖርቱጋል ጉዳዮች ክፍል ውስጥ በኃላፊነት ተመድበው ለሁለት ዓመት ሲሠሩ ነበር።

በ2000 ዓመተ ምህረት መጀመሪያ ላይ በኢንዶኔዥያ ጃካርታ የፖርቱጋል አምባሳደር በመሆን የተሾሙት አምባሣደር አና ጎሜዝ በወቅቱ በኢንዶኔዥያ የነበረው የኢኮኖሚ ቀውስ እንዲሁም የፖለቲካ ሽኩቻ ተረጋግቶ ኢንዶኔዥያውያን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መረጋገጥ እና ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲሰፍን ለማድረግ ሲካሄድ የነበረውን ትግል በቅርበት የመመልከት ዕድል እንዳጋጠማቸውም ይናገራሉ።

የዲፕሎማትነት ሥራቸውን እንዲሁም የመንግሥት ኃላፊነት ቦታቸውን በመልቀቅ ማዳም አና ጎሜዝ በፖርቱጋል ብሎም በአውሮጳ ሕብረት ውስጥ እየተጫዋቱት ያለውን ጉልህ ሚና ለመወጣት የሚያስችላቸውን ታሪካዊ ውሳኔ በመወሰን ከማርች 18 ቀን 2002 ጀምሮ የፖርቱጋል ሶሻሊስት ፓርቲ አባል ሆኑ። ማዳም አና ጎሜዝ በፖርቱጋል የሶሻሊስት ፓርቲ የፓርቲው ብሔራዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ኮሚቴ አባል በመሆን ለፓርቲው የዋና ፀሐፊነት ለመብቃት ብዙም አልተቸገሩም። በዚህ የተነሳ በአውሮጳ ሕብረት ሀገሮች የጋራ ፓርላማ አባል ሆነው ተመረጡ።

ማዳም አና ጎሜዝ በአውሮጳ ፓርላማ የፖርቱጋል ተወካይ በመሆን ከ2004 ጀምሮ በንቁ የሰብአዊ መብት ተከራካሪነት በዓለም ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ወገኖችን በመደገፍ እንዲሁም አንዲት የተባበረች አውሮጳን ለመገንባትና የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች በማስተዋወቅና በመላው ዓለም ዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ የሚደረጉ ትግሎችን በመደገፍ ከፍተኛ ተግባራትን ፈፅመዋል። በዚህም የተነሳ የተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች ያዘጋጇቸውን ሽልማቶች ለመሸለም የቻሉ ታዋቂ ዲፕሎማትና ፖለቲከኛ በመሆን በፖርቱጋል ሪፐብሊክ ፓርላማ የሂዩማን ራይትስ አዋርድ፣ የሩት ፐርሲን አዋርድ በማግኘት በ2008 አክቲቪስት ኦፍ ዘ ይር በሚል የፓርላሜንት ሜጋዚን ሽልማት አሸናፊ አድርጓቸዋል።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ማዳም አና ጎሜዝ ልክ እንደ ኢትዮጵያዊ የሰብአዊ መብት ታጋይ ስማቸው ገኖ እንዲታወቅ ያደረጋቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለነጻነት በተደረገ ትግል ውስጥ ዘወትር ከሚዘከሩት የሀገር ባለውለታ ከነሲልቪያ ፓንክረስት ተርታ ስማቸው እንዲሰፈር የሚያደርግ ተግባር በመፈፀማቸው ነው። ኢትዮጵያውያን ለእኚህ ታላቅ አውሮጳዊ ዲፕሎማት ያላቸው ፍቅር እና አክብሮት ከፍተኛ ያደረገው በ1997 ዓ.ም የተካሄደውን ብሔራዊ ምርጫ ለመታዘብ የአውሮጳ ሕብረትን የምርጫ ታዛቢ ቡድን መሪ በመሆን በምርጫው ሂደት ውስጥ ተፈፅሟል ያሉትን ስህተትና ማጭበርበር በማጋለጥ በፈፀሙት አኩሪ ተግባር ነው።

ማዳም አና ጎሜዝ በዚህ ዘመን ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማካሄድ የግድ ነው፤ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባት በሂደት ላይ ያሉ ሀገራት በሚያካሂዱት ምርጫ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎችም ገለልተኛና ነጻ ታዛቢዎችን በመላክ ምርጫዎች ምን ያህል ነፃና ትክክለኛ መሆናቸውን ከቀጣዮቹ ምርጫዎች በተሻለ መልኩ የሕዝብ ፍላጎት የሚያንፀባርቁ መሆን እንዳለባቸው ያሳስባሉ። የዴሞክራሲ ምርጫ ውጤቱ ሀገራዊ የተረጋጋ ስሜት መፍጠር፤ የሲቪልና የፖለቲካዊ መብቶች መከበር የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል፤ ተብሎ እንደሚታመን በመግለፅ ዓለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች ካሉ ምርጫዎች ግልፅና አስፈፃሚዎችና የተወዳዳሪዎች ሚና ተጠያቂነት የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ያስቻለው ብለው ከሚያምኑ ወገኖች ተርታ የሚመደቡ ፖለቲከኛ ናቸው።

በኢትዮጵያ የምርጫ 97 የቅድመ ምርጫው ሂደት ዴሞክራሲያዊነት ለአፍሪቃ ምሳሌ ይሆናል ተብሎ ነበር፤ የሲቪል ማኅበራት የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቭዥን ድርጅት የሕትመት ውጤቶች ሌሎች መገናኛ ብዙኃን ዘገባዎች በጣም ሚዛናዊ የመሆን ታሪካዊ ለውጥ ያሳዩበት ተስፋ የፈነጠቀበት ነበር። በማዳም አና ጎሜዝ የተመራው የአውሮጳ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን በመላው ሀገሪቱ በመንቀሳቀስ የምርጫውን ነጻ፣ገለልተኛና ፍትሐዊ የመሆን ሂደት ለመታዘብ ቢሰማራም በመንግሥትም ሆነ በተፎካካሪ ወገኖች ዘንድ ሁለንተናዊ ትብብር ተደርጎላቸው እንደነበር እና ጎሜዝ ያስታውሳሉ። ሁኔታዎች ተቀይረው ገዥው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫው ድምፅ ተጭበርብሯል፤ በሚል ውዝግብ ውስጥ ሲገቡ ገዥው ፓርቲ በአና ጎሜዝ የተመራው የአውሮጳ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን በኢትዮጵያ የቀለም አብዮት ለማካሄድ ተንቀሳቅሷል፤ ለዚህ ተልዕኮም ለማስፈፀም ግንባር ቀደም ተዋናይ ማዳም አና ጎሜዝ ናቸው፤ በሚል ክስ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፍቶባቸው ነበር።

በወቅቱ በገዥው ፓርቲ በኩል የመንግሥት ተወካይ የነበሩት አሁን በባህር ዳር ወረዳ 9 ፖሊስ ጣቢያ በተከሰሱበት የሙስና ወንጀል በእስር ላይ ያሉትን አቶ በረከት ስምዖንን ጨምሮ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ባልተለመደ ሁኔታ በኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣ ላይ የታዋቂዋን የቲና ተርነርን “whate is love get to do” የተሰኘ ዘፈን ርዕስን በመጠቀም፣ የአውሮጳ ኅብረት የምርጫ ታዛቢዎች ሪፖርት መሰረተ ቢስ መሆኑን በመግለፅ፣ ባለ ብዙ ገፅ ሃቲት አትመው በማዳም አና ጎሜዝ ላይ ሰፊ የስም ማጥፋት ዘመቻ አካሂደውባቸዋል።

አና ጎሜዝ ግን ይህን የስም ማጥፋት ዘመቻ እና በተለያዩ የዲፕሎማቲክ ተቋማት በኩል የገገርው ፓርቲ ዲፕሎማቶችና “ሎቢስቶች” ሲያካሂዱት የነበረው የስም ማጥፋት ዘመቻ ኢትዮጵያውያን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለውጥ፣ ለሰብአዊ መብቶች መከበር የሚያደርጉትን ትግል ከመደገፍ ፣ድምፅ ለሌላቸው ድምፅ ከማሰማት አልገታቸውም።

በተደጋጋሚ የአውሮጳ ሕብረት ኢትዮጵያውያንን እያየ እንዳላየ እየሆነ ለፍትህና ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ወገኖችን እየሳዘነ ነው በሚል በተለያዩ መድረኮች ላለፉት አስራ ሁለት አመታት ድምፃቸውን ከማሰማት አልገታቸውም።

ማዳም አና ጎሜዝ በኢትዮጵያ እየተካሄዱ የነበሩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ፣የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት መገደብን፤ የፖለቲካ እስረኞችን መታሰር መሰወድን፤ ከገዥው ፓርቲ የተለየ አቋም የሚያራምዱ ወገኖች ላይ ሲፈፀም የነበረው የመብት ጥቃትን፤ ከእውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች ጎን ቆመው ሲያጋልጡ እና ሲታገሉ ቆይተዋል።

በቀጣዩ በአውሮጳ ፓርላማ የሚደረገው ምርጫ ላይ እንደሚሳተፉ የተናገሩት እውነተኛዋ የኢትዮጵያ እና የሕዝቦችዋ ወዳጅ ማዳም አና ጎሜዝ፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን፣ ነጻ ምርጫን ፣ፍትህና ርዕትን፣ በሀገራቸው ለማስፈን የታገሉ፤ ለዚህም ሲባል የታሰሩ ፣የተሰደዱ አካላቸውን የቤተሰባቸው አባልን የገበሩ ኢትዮጵያውያን የጠሩት የምስጋና የናፍቆት ዝግጅት ላይ በክብር እንግዳነት ለመገኘት አዲስ አበባ ይመጣሉ። እንኳን ደህና መጡ ማዳም አና ጎሜዝ ዳግማዊትዋ ሲልቪያ ፓንክረስት።

# ከ አና ጎሜዝ አንደበት



አና ጎሜዝ በ1997 ዓ.ም የተካሄደውን የኢትዮጵያ አገር አቀፍ ምርጫ ለመታዘብ ወደ ኢትዮጵያ የተላከውን የአውሮጳ ኅብረት ቡድን የመሩ የአውሮጳ ፓርላማ አባል ናቸው። ምርጫውን ተከትሎ ከተነሳው ውዝግብ ጋር በተያያዘ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ዕውቅናን እና ተወዳጅነት አትርፈዋል። አና ጎሜዝ ወደ ኢትዮጵያ በተለያየ አጋጣሚ በመጡባቸው ወቅት ለአገር ውስጥ ሚዲያ የተለያየ ሐሳቦችን አንጸባርቀዋል።

**ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን እወዳቸዋለሁ**

የኢትዮጵያ ጉዳይ ከልብ ያሳስበኛል። በምርጫ 97 ወቅት በአገሪቷ የነበረኝ የአጭር ጊዜ ተሞክሮ የሚያሳምም ቢሆንም፤ አገሪቷን ሁሌም እንዳልረሳት አድርጎኛል። ሕዝቦቿን በጣም እወዳቸዋለሁ። ብዙ ኢትዮጵያውያን ጓደኞች አሉኝ። ከመለስ ሞት በኋላ የአገሪቷ ፖለቲካ እየተለወጠ ለመምጣቱ ምልክቶች አሉኝ።

አንዳንዶቹ አመራሮች የፖለቲካ ምህዳሩ ከፈት እንዲል የሚፈልጉ ሲሆን የተቀሩት ባለሥልጣናት ደግሞ እንደ ቀድሞው አመራር ዝግ የሆነ አካሄድ እንዲኖር የሚፈልጉ ናቸው። አገሪቱን ባለፈው ሥርዓት መስመር መምራት አስቸጋሪ ነው። ሕዝቦቿ እየተማሩ ሲመጡ የማኅበራዊ ድረ ገጽ ተጠቃሚ ቁጥር እየጨመረ እንዲመጣ ያደርገዋል። ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ትስስሩ እየዳበረ ሲመጣ 85 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብን ማፈንና ማስቆም የማይቻል ይሆናል።

**የመለስ አለመኖር ለአገሪቱ የተሻለ ዕድል ይፈጥራል**

የመለስ አለመኖር ለኢትዮጵያውያን ትልቅ ዕድል ነው። ነገሮች የቱንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆኑ እንኳን የፖለቲካ ምህዳሩን ለመክፈት የተሻለ አጋጣሚ ይፈጥራል ብዬ አስባለሁ። መለስ በጣም ጎበዝ መሪ ቢሆንም አጭበርባሪ መሆኑንም መዘንጋት የለብንም። የእርሱ ገለል ማለት በሩን በተሻለ መንገድ ለመክፈት እድሎችን ያሰፋል።

ባለሥልጣናቱ ወደዱም አልወደዱም የለውጥ ማዕበሉን የሚቀበሉበት ጊዜ ይመጣል። አሁንም ግን ሁሉንም የመወሰን ዕድሉም ይሁን ሀላፊነቱ ያለው በኢትዮጵያውያን እጅ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

**ኢትዮጵያውያን የተሻለ አመራር ያስፈልጋቸዋል**

ኢትዮጵያውያን የተሻለ አመራር ያስፈልጋቸዋል የሚል ሀሳብ አለኝ። ኢትዮጵያውያን ልዩ ሕዝቦች ናቸው። የታላቅ ሥልጣኔ ባለቤትም መሆናቸውን ሁሌም አወሳለሁ። መኖሪያዬ ምንም ያህል ሩቅ ቢሆንም የኢትዮጵያን ጉዳይ እንደመከታተል የሚያረካኝ ሥራ የለም። እንደኔ ሁሉ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ አውሮጳውያንም አሉ። አንዳንዶቹ እንደውም ከኔ የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ቢሆንም መንግሥት ፈጥሮ በሚነግራቸው የሀሰት መረጃ የሚደለሉ ሆነው ይገኛሉ።

አውሮጳውያኑ ለምን ራሳቸውን ያታልላሉ ካልን ብዙ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። አንዳንዶቹ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት ይኖራቸዋል ብዬ አስባለሁ። ሌሎች ደግሞ አገሪቷ ያላትን የጂኦ ፖለቲካ ጥቅም የሚያስቡ ይመስለኛል። ኢትዮጵያ በአፍሪቃ ቀንድ አካባቢ ያላት አቀማመጥ ወሳኝ አገር እንድትሆን አድርጓታል። የሽብርተኝነት ስጋት ያንዣብባታል በሚባለው የቀንዱ ክፍል መገኘቷ የሁሉንም ቀልብ ለመሳብ እንድትችል አድርጓታል።

መለስ ለምዕራባውያን በተለይ ለአሜሪካ መንግሥት የፀረ ሽብር ዘመቻ ረዳት መሆኑ ለዝምታው አንድ ምክንያት ነው። በሶማሊያ ጦሩን አዝምታ ያሳየው አጋርነት ሌሎች የሰብኣዊ መብት ጥሰቶች ቦታ እንዲያገኙ አድርጓቸዋል። ሌሎች  በአገሪቷ ላይ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያላቸው ግለሰቦች የገነቧቸው ፋብሪካዎች (አላማው ለመልካም ቢሆንም) በፖለቲካ ምክንያት ለችግር እንዳይጋለጥባቸው ይፈልጋሉ። ከዚህ የተነሳ በኢትዮጵያ ያለውን ነባራዊ እውነት እያዩ እንዳላዩ ሲሆኑ ይታያል።

**ገበሬዎች መሬታቸውን እየተነጠቁ ነበር**

ባለፉት ዓመታት የአውሮጳ ዜጎችን ጨምሮ የተለያዩ አገራት ኢንቨስተሮች መዋዕለ ንዋያቸውን በዚህች አገር ላይ ማፍሰሳቸውን ተረድቻለሁ። በተመሳሳይ መንገድ የመሬት ቅርምቱ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰውም በዚህ ወቅት መሆኑን መርሳት የለብንም። በዚህ ረገድ የህንድ እና ሳውዲ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ መሬት ቅርምት በሰፊው እንደተስፋፉ አውቃለሁ። በራሳቸው አገር ቁራጭ መሬት የሌላቸው ደሃ ገበሬዎች በሞሉበት አገር መሬትን ገንዘብ ላቀረቡ የውጭ ባለሀብት ማከፋፈል ከፍተኛ በደል ነው።

**ስለ ሰብኣዊ መብት ምን አገባሽ ተብያለሁ**

ምርጫው ከተጠናቀቀ ሁለት ቀናት በኋላ ባወጣነው ሪፖርት ትክክለኛ ቆጠራ ሳይደረግ ተዓማኒነት ያለው ምርጫ ማድረግ እንደማይቻል አሳውቀናል። ሪፖርቱን በበረከት ስምዖን በኩል ለኢትዮጵያ መንግሥት አቅርቤያለሁ። ሪፖርቱን አለማውጣታችን ሁሉት ቀናት በፊት መለስ ዜናዊ ደውለው ‹‹ተጠንቀቂ›› ብለውኛል። እኔ ግን በጽሕፍ ያሰፈርነው እሱኑ ነው በአደባባይ የምናገረውም እሱኑ ነው አልኳቸው።

ከመለስ ጋር ቀጠሮ ይዘን የአውሮጳ ኅብረት አምባሳደር ከነበሩት ቲም ክለርክ ጋር ሄጃ አገኘኋቸው። ከባድ ስብሰባ አደረግን። በእጄ የያዝኩት ጋዜጣ ላይ ኢሕአዴግ “አሸንፌያለሁ” ያለባቸውን ቦታዎች በቢጫ አስምሬ ፊታቸው ላይ አስቀመጥኩት። “እነዚህ ውሸቶች ናቸው መቼ በተደረገ ቆጠራ ነው እነዚህ ቦታዎች ያሸነፋችሁት?›› ብዬ አፋጠጥኳቸው። በጣም ተናደዱብኝ “ትልቅ ሸፍጥ ነው እየተፈፀመ ያለው›› አልኳቸው።

ከዚህ በኋላ ከበረከት ስምዖን ጋር ምርር ያለ ስብሰባ ተቀመጥኩኝ መግለጫም አወጣን። በዚያ መግለጫ መንግሥት በጣም ተበሳጨን። ስለ ሰብኣዊ መብት ምን አገባሽ? አሉኝ። ከዚያ በኋላ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ውርጅብኝ አወረዱብኝ። አምባገነኑ መንግሥት የሕዝቡን ተስፋ በኃይል ጨፍልቆታል። ይሄ ነው እውነታው። በአዲስ አበባ ግን ሸፍጥ ሊሰራበት የሚችልበት  ቀዳዳ ሊያገኙ አልቻሉም። ሳይወዱ ተቃዋሚዎች ማሸነፋቸውን ተቀብለዋል።

**የብርሃኑ ነጋ ብቃት ነው የታየኝ**

ከሁሉም መካከል ብቃት ያለው ሆኖ የታየኝ ብርሃኑ ነጋ ነው። ግልፅ የሆነ ዓላማ የነበረውና ያንንም ዓላማ ለሕዝብ በአግባቡ ማስረዳት የቻለ ነበር። ገጠር ሄጄ ሰዎችን ሳነጋግር ሁሌም በሚባል ደረጃ የብርሃኑ ነጋን ስም በጥሩ ያነሱልን ነበር። ይህ የሆነው ገዢው ፓርቲ ሕዝብን በብሔር ለመከፋፈል ብዙ ሰርቶ በነበረበት ሁኔታ ውስጥ ነው። ብርሃኑ ከዋና ዋናዎቹ ብሔሮች ባይወለድም ይህ ግን ድጋፍ እንዳያገኝ ተግዳሮት አልሆነበትም። ክፍፍሉን ማሸነፍ ችሎ ነበር። ሌሎችም ነበሩ ብርቱካን ሚዴቅሳ አንዷ  ነበረች።

**ለዐቢይ የብሔር ነገር ትልቅ ፈተና ነው**

አሁን የሚታዩት ለውጦች አስደማሚና አስገራሚ ናቸው። ማንም ያላሳበው ነው የሆነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ አንድ የኢትዮጵያ አምባሳደር እነ ግንቦት ሰባት ወደ አገር ቤት ገብተው በ2007 ምርጫ እንዲሳተፉ የበኩሌን ጥረት እንዳደርግ ጠይቀውኝ ነበር። ግን የትም አልደረሰም።

ኃይለማርያም ያንን የመለስ ነገር ለማድረግ ኃይሉ አልነበራቸውም። አንድ ስብሰባ ላይ ተገናኝተን ሊያናግሩንኝ ፈቃደኛ አልነበሩም። የፈሩ ይመስለኛል። ለውጥ ያላመጡት ለዚህ ነው። በዚህ ሁኔታ ሕዝቡ ገንፍሎ ወጥቷል። ከኦሮሞ ወገን የተገኙ ወጣት ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ሥልጣን መምጣታቸው ጥሩ ነው አገሪቷን አረጋግቷታል። ትልቅ ተስፋ እንደፈነጠቀ ነው የሚሰማኝ ቀላል ሁኔታ ውስጥ እንዳልሆኑ ግን ይሰማኛል። ከውስጥም ከውጭም ተቃውሞ አለባቸው። ጥቅማቸው የተነካባቸው ብዙዎች አሉ። ድፍረትና ወኔ የሚጠይቁ በርካታ ነገሮች ፈጽመዋል። ጠላቶቻቸው እንዳደቡባቸው የሚጠፋባቸው አይመስለኝም። በአጠቃላይ ይሄ የብሔር ነገር ትልቅ ፈተና ነው።

ልዩ ዕትም

# "እና ጎሜዝ- የእውነትና የፍትህ ጠበቃ"

## ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ

የአውሮጳ ሕብረት አባል የሆኑትና በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በታዛቢነት ያገለገሉት አና ጎሜዝ የመለስ ዜናዊ መንግሥት ምርጫውን በማጭበርበርና የሕዝብን ድምፅ በመንጠቅ በአንባገነንነት የቀጠለበትን መንገድ ለዓለም ኅብረተሰብ በማጋለጥ ላለፉት አስራ ሶስት ዓመታትም በተመሳሳይ ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲካሄድ ግፊት በማድረግ ይታወቃሉ።

በግፍ የተቀማ የሕዝብ ድምፅን በማጋለጣቸው በኢህአዴግ ሹማምንት በጠላትነት የተፈረጁትና የኢትዮጵያ ህዝብ ባለውለታ የሆኑት አና ጎሜዝ ቅዳሜ የካቲት 9 ቀን 2011 ዓ.ም በግለሰቦች በጎ ፈቃድ በተቋቋሙ የኮሚቴ አባላት በተደረገላቸው ግብዣ መሰረት አዲስ አበባ ይገባሉ። የዚህ ኮሚቴ መስራች የሆነው ጋዜጠኛ እና አክቲቪስት እስክንድር ነጋን በጉዳዩ ዙሪያ አነጋግረነው የሰጠንን ምላሽ ይዘን ቀርበናል።

**ግዮን፡- አና ጎሜዝን ወደ ኢትዮጵያ ለመጋበዝ መነሻ ምክንያታችሁ ምንድን ነው?**

እስክንድር፡- ኮሚቴ አቋቁመን ነው እርሳቸውን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ የጋበዝነው። ይሄንን ያደረግንበት ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ከመንግሥትም ከተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሆነ በማንኛውም ወገንተኛ በሆነ አካል መምጣት የማይፈልጉ በመሆናቸው፤ በፍቃዳቸውና በፍላጎታቸው መሰረት ጥቂት ሰዎች ተሰባስበን ገለልተኛ ኮሚቴ አቋቁመን ወደ ሀገር ቤት እንዲመጡ ጋብዘናቸዋል።

ወደ እዚህ እንዲመጡ ሀሳቡን ያቀረብንላቸው እኛ ብንሆንም በሶስትና አራት ምክንያቶች ነው ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት፤ ከእነዛ ውስጥ በቀዳሚነት በ1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ ቃል ተገብቶለት ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ድምፁን ሰጥቶ ያ የተገባለት ቃል ታጥፎ ድምፁ ተሰርቆ የምርጫው ውጤት ተቀልብሷል። በዛን ጊዜ በታዛቢነት የመጡት ሁሉም ማለት ይቻላል (ከአውሮጳ ህብረት ውጭ) እውነቱን ለመናገር ፍቃደኛ ባልሆኑበት ጊዜ ለእውነቱ የተከራከረው የአውሮጳ ኅብረት ባልደረባ ነበሩ።

ይህ እንዲሆን ደግሞ የአና ጎሜዝ ሚና ወሳኝነት አለው፤ በ2002 ዓ.ም ምርጫ ሌላ ታዛቢ መጥቶ ነበር። የእዛን ጊዜ ምርጫው በሽፍጥ ሲታለፍ በምርጫ 97 እንደተሰማው ዓይነት ድምፅ አልተሰማም። ይሄ የአና ጎሜዝ ሚና ምን ያህል የጎላ እንደሆነ ያመለክታል። አና ጎሜዝ የእውነት እና የፍትህ ጠበቃ ስለሆኑ ይሄ መልካም ስራቸውን እውቅና ሊያሰጣቸው ይገባል የሚል አቋም ስላለን ነው ወደ ሀገር ቤት እንዲመጡ ያደረግነው።

**ግዮን፡- ግብዣውን ተቀብለው መምጣታቸው የሚኖረው እንደምታስ እንዴት ይገለፃል?**

እስክንድር፡- እሱ ሁለት እንደምታ ይኖረዋል። በምርጫ 97 ወቅት የታዘቡትን ለህዝብ



እንዲያካፍሉ ነው ዋነኛው፤ እሁድ ዕለት የካቲት 10 ቀን በኢትዮጵያ ሆቴል ከታዳሚዎች ጋር ተገናኝተው ያንን ምስክር የሚሰጡበት መድረክ ተዘጋጅቷል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በሚቀጥለው ምርጫ ላይ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከዚህ በፊት በአፍሪቃም ሆነ በየትኛውም ዓለም አስቀድሞ አድርጎ በማያውቀው ደረጃ ታዛቢ ሀይል (ቡድን) እንዲልክ ቅስቀሳ መደረግ አለበት፤ እርሳቸው ደግሞ በዛ ውስጥ የሚጫወቱት ሚና አለ ብለን እናምናለን። የሚቀጥለው ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ የማይሆን ከሆነ ሀገራችን ከፍተኛ ችግር ውስጥ ነው የምትገባው። ዴሞክራሲው ብቻ ሳይሆን አንድነቱም ትልቅ ፈተና ላይ ይወድቃል።

**ግዮን፡- የአቀባበል ፕሮግራሙ ከኢሳት የሚሊየነሙ አዳራሽ ዝግጅት ጋር የተቆራኘበት ምክንያት ምንድን ነው? ለእሳቸው ለብቻ ማዘጋጀት አይቻልም ነበር?**

እስክንድር፡- አና ጎሜዝ በምርጫ 97 ወቅት ከወሰዱት አቋም ሌላ ምርጫው አልቆ ወደ ሀገራቸው ከሄዱ በኋላ ባለፉት 13 እና 12 ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ምርጫ እንዲደረግ ፤ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲጠበቁ፤ ድምፃቸውን ሳይሰስቱ ሽንጣቸውን ገትረው እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ሲከራከሩ ነው የኖሩት። እኚህ ባለውለተኛ ኢትዮጵያ ድረስ ከመጡ በኋላ ከህዝብ ጋር መገናኘት አለባቸው። ልፋታቸውና ጥረታቸው ዋጋ እንደነበረው ለህዝብ ልንገልፅላቸው ይገባል የሚል አቋም አለን።

በዚህ መልክ ለእሳቸው ክብር የሚሆን ትልቅ አዳራሽ ሚሊኒየም ስለነበረ እርሱ ደግሞ ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት አስቀድሞ የተያዘ ስለሆነ በሁለተኛነት የነበረው አማራጭ ሌላ ፕሮግራም መፈለግ ነበር። እንደ አጋጣሚ ሆኖ የኢሳት ፕሮግራም በዚህ ቀን ስለነበረ ሁለቱም ለዴሞክራሲ ከህዝብ ጋር እንዲገናኙ ስንጠይቅ ኢሳት ፈቃደኛ ሆኖልናል። ስለዚህ መድረኩን እኚህን ባለውለተኛ ከህዝብ ጋር ለማገናኘት ነው የምንጠቀምበት፤ መድረኩን ላለመጠቀም ብንወስንና ከህዝብ ጋር ሳይገናኙ ቢመለሱ ይሄ ነገር በህዝብ ያስወቅሰናል። በዚህ አጋጣሚ ኢሳቶች ጥያቄያችንን ስለተቀበሉ ከልብ እናመሰግናለን።

**ግዮን፡- እንደ ሙያተኛ ኢሳት በጨለማው ዘመን ካደረገው እንቅስቃሴ አኳያ እንዴት ይገለፃል?**

እስክንድር፡- ለኢሳት ጥሩ መገለጫና ብራንድ የወጣለት ይመስለኛል፤ ‹‹ኢሳት የኢትዮጵያ ህዝብ ዐይንና ጆሮ ነው›› የሚለው። ይህ ሚዲያ በተለይ በጨለማው ዘመን የተጫወተው ሚና ትልቅ ነው። ኢሳት በዛን ዘመን ባይኖርስ ኖሮ የሚለውን በመጠየቅ ነው እኔ የኢሳትን ውለታ የምገልፀው። ድቅድቅ ያለው ጨለማ ውስጥ ኢሳት በትንሹ የሚንጨለጨል ብቸኛ ብርሃን ነበር፤ ምናልባትም ኢሳት ባይኖር ኖሮ አሁን የተገኘው ለውጥ በዚህ ጊዜ ላይገኝ ይችል ነበር ብዬ ነው የማስበው። ኢሳት ከሰራው ስራ ባሻገር በአሁን ሰዓት ለተፈጠሩ ብዙ ሚዲያዎች መንገድ የጠረገ ነው፤ ሁሉም እሱን አርአያ አድርገው ነው የተፈጠሩት።

**ግዮን፡- ከፀጥታ አኳያ መንግሥት ለአዘጋጅ ኮሚቴው ያደረገው ድጋፍ እንዴት ይገለፃል?**

እስክንድር፡- ጥበቃን በሚመለከት መንግሥት ሙሉ ኃላፊነት ወስዷል። እሳቸውም መንግሥት ሙሉ ኃላፊነት ስለወሰደ ነው ወደ እዚህ የሚመጡት። የፀጥታውን ጉዳይ እኛ ልንወጣው የምንችለው ኃላፊነት አይደለም። እሳቸውን ብዙ የሚፈልጓቸው ፀረ ለውጥ ኃይሎች አሉ። ስለዚህ ከመንግሥት ጋር ስንነጋገር የጥበቃቸው ጉዳይ ቀዳሚ አጀንዳ ነበር።

በነገራችን ላይ እሳቸው ግለሰብ አይደሉም የአውሮጳ ህብረት አባል ናቸው። ስለዚህ መንግሥት ዞሮ ዞሮ ኃላፊነት ይኖርበታል። “የፀጥታውን ጉዳይ ኃላፊነት እወስዳለሁ” ብሎ አረጋግጦልናል። የመንግሥት ጥበቃና ዋስትና አላቸው። ልክ አውሮፕላን ማረፊያ ከደረሱ ጊዜ አንስቶ እስኪወጡ ድረስ የሚጠብቃቸው መንግሥት ነው። በእኛ በኩል ግብዣው ቀርቦላቸው ተቀብለዋል፤ ህዝብ ደግሞ እኚህን የኢትዮጵያና የህዝቧ ባለውለታ የሆኑ ታላቅ ሰው በፍቅር ተቀብለን በፍቅር እንድንሸኛቸው ነው መልዕክቱን የማስተላልፈው።

**ግዮን፡- እናመሰግናለን።**

# ግዮን መጽሔት

## በአጭር ጊዜ ገበያ ውስጥ ለመግባት የቻለችው ግዮን የእርስዎ መፅሔት

መጽሔታችን ከተጀመረች ጀምሮ የእናንተ ውድ አንባቢያን አቀባበልና አስተያየት ሳይለየን ቆይተናል። በአዲስ ዓመት በአዳዲስ አምዶች

**ትምህርት፡-** በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ያሳያል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ፍኖተ ካርታን በተመለከተና ከትምህርት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች

**ኢትዮጵያዊነት፡-** አገራችን የአንድነት ጉዞ በምትጀምርበት ወቅት ኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው? በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በተከታታይ እናቀርባለን።

በእነዚህ አምዶች ላይ ባለሙያ የሆናችሁና የተለየ ሀሳብ አለን የምትሉ ተሳታፊዎች በኢሜል ፅሁፍ መላክ ትችላላችሁ።

በልዩ አቀራረብ፣ በአዳዲስ አምዶችና በሳል ፀሃፊያን በመታገዝ

## በየሳምንቱ ቅዳሜ ከእጅዎ ትደርሳለች።

ቢጨመር ፣ ቢሻሻል የሚሉትን ከወዲሁ ይጠቁሙን!





+251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 122333

www.facebooook.com/enqu2013
Facebook
Gihon-meg Fekadu

ኢ-ሜይል:
enqu2013@gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com